# በኢትዮጵያ ሕግ የቡድን ክስ የስፋት ወሰንና ጠቀሜታ፤ ንጽጽራዊ ጥናት

በጌታቸው አበራ*

የቡድን ክሶች[1] ኮመን ሎው በመባል የሚታወቀው የሕግ ሥርዓት የተለመዱ ገጽታዎች ናቸው። በታሪክ ረገድ ለልደትና ዕድገታቸው መሠረት የሆኑት ከሕግ ይልቅ በርትዕ ለመዳኘት ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ቢሆኑም በአሁኑ ጊዜ ግን በሕግ ላይ የተመሠረቱ ክርክሮችንም በተመለከተ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ወደ አገራችን ስንመጣም፥ የቡድን ክሶች በ1957 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዕውቅና አግኝተዋል። እንዲሁም አዲሱ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 37(2) (ለ) ላይ ፍትሕ ለማግኘት ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ መሆናቸውን ነጥሎ ስለሚያመለክት የቡድን ክሶች ከበፊቱ ይልቅ በአሁኑ ወቅት የላቀ ግምትና ደረጃ ያገኙ ይመስላል።

ከእነዚህም ምክንያቶች የተነሳ፥ ስለቡድን ክስ ባሕርይ፤ የአፈጻጸም አድማሱና ዓላማው የሚቀርብ ትንታኔ ወቅታዊም አስፈላጊም ይመስለናል። ይህም ጽሑፍ፤ የቡድን ክስ አጀማመሪ፥ ዕድገቱና በአሁኑም ወቅት የተፈጻሚነት አድማሱ ምን እንደሚመስል ለማሳየት፤ እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችንን ድንጋጌዎች በመገምገም ጉድለቶች ካሉባቸው እነዚህኑ ለመጠቆም የቀረበ ውሱን ሙከራ ነው። የቡድን ክስ አጠቃቀመ ልማድ በእጅጉ ዳብሮ የሚገኘው በአሜሪካ በመሆኑና ይኸውም ሁኔታ መሠረተ ሀሳቦቹን በተሻለ ለመረዳት እንደሚያስችለን በመገመት፤ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በአመዛኙ በዋቢነት የተጠቀምነው የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች የሚመሩባቸውን ደንቦችና በልማድም የሚከተሏቸውን አሠራሮች ነው።[2]

---

* ረዳት ፕሮፌሰር፥ ሕግ ፋክልቲ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

[1] የቡድን ክስ "ሬፐሬዘንታቲቭ ሱትስ" በመባልም ይታወቃሉ  የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 383 ይመልከቱ። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በእንግሊዝኛው "ክላስ አክሽን" በአማርኛው "የቡድን ክስ" በሚለው ሐረግ እንጠቀማለን። ከቡድን ክስ ጋር በተያያዘ በእንግሊዝኛው "መደብ" ማለት ደንበኛ ማኀበራዊ መደብ ሳይሆን የአንድ ክስ የመጨረሻ ውጤት በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት የሚነካቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎችን የያዘ ቡድን ማለት ነው። የቡድን ክስ በመሠረቱ የጣምራ ክስ ማቅረቢያ ዘዴ ነው። ነገር ግን በጣምራ ክስ ውስጥ ጥቅማቸው የሚነካባቸው ሁሉ በስማቸው ተከራካሪ ወገኖች ሲሆኑ በቡድን ክስ ግን ተከራካሪ ሆኖ የሚቀርበው የቡድኑ ተወካይ ብቻ ነው። ሌሎቹ የቡድን አባላት በክሱ ውጤት ጥቅማቸው የሚነካ ቢሆንም በተከራካሪነት አይቀርቡም፤ ክስ መመሥረቱንም ላያውቁ ይችላሉ።

[2] ለምሳሌ ሪቻርድ ቢ ካፓሊ እና ክላውዲዮ ኮንሶሎ፤ "ክላስ አክሽንስ ፎር ኮንቲኔንታል ኢውሮፕ" ቴምፕል ኢንተርናሽናል ኤንድ ኮምፓራቲቭ ሎው ጆርናል፥ ቅጽ 6 ቁ 1. ፀደይ 1992 ገጽ 18 ይመልከቱ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የቡድን ክስ በአሜሪካ የሕግ ሥርዓት ብቻ የሚገኝ የሕግ ተቋም መሆኑና "የቡድን ክስ ከአሜሪካ የባሕር ዳርቻ ባሻገር የማይገኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በእርግጥ ሊነጻጸር የሚችል ሥነ ሥርዓትም የለም" ተብሎ በአጽንኦት ተገልጿል። ሕንድ ግን ከዚህ የተለየች መሆኗና የሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ክፍል 1 ድንብ ቁጥር 8 ከአሜሪካው ፌዴራል ደንብ ቁጥር 23 ጋር በቅርብ የሚመሳሰል የቡድን ክስ ሥርዓት የሚያቋቁም መሆኑም በተጨማሪ ተጠቅሷል።

## የቡድን ክስ ጽንሰ ሀሳብ

### 1. የቡድን ክስ ባሕርይ

የቡድን ክስ የአንድ ቡድን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አባላት በራሳቸውና በሌሎቹ የቡድኑ አባላት ስም እንዲከሱ ወይም እንዲከሰሱ ሊፈቀድላቸው የሚችልበት የሥነ ሥርዓት ዘዴ ነው:: በክሱ ውስጥ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ሆነው የሚቀርቡት ወገኖች ከክሱ ውጤት የሚያገኙት ወይም የሚያጡት የየራሳቸው የግል የሆነ ጥቅም አላቸው:: ክሱንም የሚያቀርቡት እነዚህኑ የየራሳቸውን ጥቅሞች ለማስከበር ሲሆን ከዚህም አልፈው ተርፈው በወኪልነት ደረጃ የሌሎቹን የቡድን አባላት ጥቅም አብረው ለማስከበር ጭምር ነው:: ይህን በመሰለው ክስ ወኪል ሆኖ ለመቅረብም የተወከሉትን አባላት ፈቃድ ማግኘት በመሠረቱ አስፈላጊ አይሆንም::[3] ሁሉም የቡድኑ አባላት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በራሳቸውና በሌሎቹም አባላት ስም ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ሆነው የቀረቡት ወገኖች ሁሉንም የቡድን አባላት እንደሚወክሉ ሕጉ ግምት ይወስዳል::[4]

ከቡድኑ አባላት መካከል የተወሰኑት በራሳቸውና ከእነርሱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ በሚገኙ በሌሎችም ስም ክስ እንዲያቀርቡና እንዲከላከሉ በሚፈቀድበት ጊዜ በግንባር ወይም በመረጧቸው ወኪሎቻቸው አማካይነት ፍርድ ቤት የመቅረብ ዕድል የሚያገኙት የተወሰኑ አባላት ብቻ እንደሚሆኑ ግልጽ ነው:: ስለዚህም፤ ከቡድኑ አባላት መካከል ከሌሎቹ ማንም ሰው ያለ ውሳንያተ ሕግ አግባብ መብቱን አያጣም (due process of law) የሚለው መሠረታዊ መርህ ተጠቃሚ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ የዚህ መብት ተጠቃሚ አይሆኑም ማለት ነው:: ይህም የሚያመለክተን የቡድን ክሶች የሚመሩበት ሥርዓት ከላይ የጠቀስነው መሠረታዊ መርህ አንዱ ተስናን (exception) መሆኑን ነው:: እንደ ጣምራ ክስ አቀራረብ ዘዴነቱ፤ የቡድን ክስ አቀራረብ መሠረተ ሀሳብ "እጅግ ፈታኝ የሆኑ አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጥያቄዎችን ያስነሳል:: ...እነዚህም፤ ውክልና ሲባል ምን ማለት ነው? በሕግ መድረክ አንድ ክስ የሚቀርብበትስ ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉት የፍትሐ ብሔር ክስ እምብርት የሆኑ የውክልናን ባሕርይና የክስን ዓላማ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው::"[5]

ከላይ የጠቀስነው ማንም ሰው ያለ ውሳንያተ ሕግ አግባብ መብቱን አያጣም የሚለው መሠረታዊ መርህ አንድ ሰው በሕግ መድረክ በግንባር ወይም በመረጣቸው ወኪሎቹ ወይም ወኪል እንዲሆኑለት በተለይ በተሰየሙ ሞግዚቶቹ ወይም ባለአደራዎቹ

---

[3] አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲውት፤ ሪስቴትመንት ኦፍ ዘ ሎው ኦፍ ጃጅመንትስ (1942) ክፍል 86፤ ገጽ 418:: ካርል ሲ. ሁዊተን፤ "ሪፕሬዘንታቲቭ ሱትስ ኢንቮልቪንግ ኑመረስ ሊቲጋንትስ" ኮርኔል ሎው ኳርተርሊ ቅጽ........(19.....) ገጽ 422 ስለዚህ ነጥብ ከኢትዮጵያ ሕግ አንጻር ለተሰጠው ማብራሪያ በዚህ ጽሑፍ ከዚህ በታች ገጽ 37 ይመልከቱ::

[4] እስቴሪን ሲ. ይዜል፥ ሲቪል ፕሮሲጀር (አራተኛ እትም)፤ ሊትል ብራውን ኤንድ ካምፓኒ፥ ኒዮርክ (1996):: አንዳንድ ፀሐፊዎች የቡድን ክስ ጣምራ ክስ የሚፈቀድበት ሥነ ሥርዓት ነው ይሉታል፤ በእርግጥም የቡድን ክስ የሚፈቀድበት ሥነ ሥርዓት አንዱ መልክ ነው:: ልዩነታቸው ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ጣምራ ክስ ሲጣመሩ በስማቸው የሚከራከሩ ወገኖች ሲሆኑ በቡድን ክስ ግን የቡድኑ ተወካይ ብቻ በስሙ የሚከራከር ወገን ነው:: ምክንያቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጣመር ተግባራዊ ሊደረግ አይችልም:: ሮበርት ሴድለር፥ ኢትዮጵያን ሲቪል ፕሮሲጀር፥ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፥ አዲስ አበባ (1968) ገጽ 70 ይመልከቱ:: እንዲሁም ከክሱ ሊነጠሉ የማይገባቸው ወገኖች ቢሆኑም እንኳ ሁሉንም ለማጣመር የማይቻል መሆኑ ከተረጋገጠ በቡድን ተወካዮች ሊወከሉ የሚችሉ መሆኑ ሊጤን ይገባል:: ከዚህ በታች ገጽ 7-9 ይመልከቱ::

[5] ይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 422::

አማካይነት ቀርቦና ጥቅሞቼን ያስከብሩልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ የመከራከር ዕድል ሳይሰጠው መብቶቹንና ጥቅሞቹን ሊነጠቅ እንደማይገባ የሚደነግግ ጽኑዕ የሕግ መመሪያ ነው::[6] ይህም መመሪያ ራሱ በተራው በርትዕና በሕገ ልቡና ላይ የተመሠረተ ነው:: ሆኖም ግን መርሁን ተፈጻሚ ለማድረግ ሲባል በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በሙሉ በክሱ ውስጥ መግባት ያለባቸው መሆኑ እንደ ግዴታ ቢጣል ይህን የመሰለው አሠራር በአንዳንድ አጋጣሚዎች ርትዕንና ሕገ ልቦናን የሚጻረር አድራጎት ሊያስከትል ይችላል፤ በገቢርም ቢሆን አሠራሩ ፍትሐዊና አመቺ አለመሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ አጋጣሚዎች ተከስተዋል::

እንዲሁም፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል (ማለትም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን በአንቀጽ 38 ላይ "ብዙ" ወይም "እያሌ" ወይም "በርካታ" በመባል በአኃዝ የተገለጹ) በተናጠል ክስ እንዲያቀርቡ ቢገደዱ ፍርድ ቤቶችም በፈንታቸው በመሠረቱ አንድ ዓይነት የሆኑ የሕግ፥ የፍሬ ነገርና የዳኝነት ጥያቄዎች ያላቸውን ለቁጥር የሚታክቱ ክሶችን ሰምተው ለመወሰን ይገደዳሉ ማለት ነው:: ይህን የመሰለውም ሥነ ሥርዓት ለፍርድ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በዕኩል ሁኔታ ለከሳሾችና ለተከሳሾችም ውድ ጊዜን በከንቱ የሚያባክን መሆኑ ግልጽ ነው:: ለምሳሌም ያህል፤ ከሳሾችን በሚመለከት ቀዳሚ የሆነውን የክስ ምክንያት መኖሩን የሚያመላክቱ ማስረጃዎችን ፈልፍሎ የማውጣቱን ተግባር እንኳን በኅብረት ቢሰሩት በአነስተኛ ጊዜ፥ ጥረትና ወጭ ሊያከናውኑት ሲችሉ በነፍስ ወከፍ ቢፈጽሙት ግን የሚያጠፉት ጊዜና ወጭ ከፍተኛ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም::[7] እንዲያውም፣ ከዚሁ ችግር የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ከነአካቴውም ክስ ከማቅረብ ይልቅ መተውን ለመምረጥ ይገደዱ ይሆናል:: ተከሳሾችን በሚመለከትም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: ከሳሾች ያሏቸው የመብት ጥያቄዎች በዓይነታቸው ተመሳሳይ በመሆናቸው የሚያስነሷቸው ጭብጦች በቀላሉ በአንድ የክስ መዝገብ ውስጥ ተጠቃለው ውሣኔ ሊያገኙ ሲችሉ ለተናጠል ክሶች እንዲዳረጉ ቢደረግ እነዚህን በርካታ ክሶች ለመከላከል የሚያስከትልባቸው ወጭና የሚደርስባቸው መጉላላት ከፍተኛ እንደሚሆን መገመቱ ቀላል ይመስለናል:: ስለዚህም፣ የቡድን ክሶች፣ የክሶች መንዛዛትንና ከዚህም ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን በባለጉዳዮች ላይ የሚደርሰውን መጉላላት ለመከላከል የታቀዱ የሥነ ሥርዓት ዘዴዎች ናቸው::[8]

ከዚህ በላይ፣ ሕጉ የጣምራ ክስ እንዲቀርብ በሚያስገድድባቸው ሁኔታዎችም ቢሆን፣ ከቁጥራቸው ብዛት የተነሳ አንድም ክሱ የሚመለከታቸው እነማን እንደሆኑ ለማፈላለግና በትክክል ለማረጋገጥ፣ አንድም ደግሞ እንደሚመለከታቸው ተረጋግጦ በክሱ ውስጥ ከገቡ በኋላም ቢሆን በየጊዜው የመለዋወጥና አንዱ በሌላው የመተካት ሁኔታ ስለሚያጋጥም፣ ከነዚህም ምክንያቶች የተነሳ የሚያስከትለው ወጭ ራሱ ከክስ የሚያሸሽ ሊሆን ስለሚችል፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ሁሉንም ግለሰቦች አጣምሮ በክሱ ውስጥ ማስገባቱ የማይቻል ወይም ገቢራዊነቱ የማይሳካ ሊሆን ይችላል:: በተጨማሪም:-

> "ሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ሆነው በክሱ ውስጥ ቢገቡ በቁጥራቸው መብዛት ምክንያት ከፍተኛ ወጭን ያስከትላል:: አብዛኛውን ጊዜም፣ አንዳንዶቹ በፍርድ ቤቱ የሥልጣን ክልል ውስጥ ስለማይገኙና የአን ዳንዶቹም አድራሻ የማይታወቅበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም፣ አንዳንዶቹ

---

[6]አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲውት፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 416:: የዚህ መርህ ዋና ዋናዎቹ መሠረተ ሀሳቦች በሕገ መንግሥቱ በምዕራፍ ሁለት በተለያዩ አንቀጾች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ::

[7] ሲ. ኤች ብራውን፥ ኤዲ. ቬስታል፥ ኤንድ ኤም ላድ፤ <u>ኬዝስ ኤንድ ማቴሪያልስ ኦን ፕሊዲንግ ኤንድ ፕሮሴጀር</u> ዴኒስ ኤንድ ኮ:: ቡፋሎ፥ ኒው ዮርክ (1953) ገጽ 537፤ ከዊክስ ቪ ባሬኮ ጉዳይ በመጥቀስ::

[8] ሳሬ ኤል ቴፐሊ ኤንድ ራልፍ ቢ. ሁዊተን፥ <u>ሲቪል ፕሮሴጀር</u>፥ ዘ. ፋውንዴሽን ፕሬስ ኢንኮር፥ ኒዮርክ (1994) ገጽ 681-2::

> ደግሞ በሞት ተለይተው ሊሆን ስለሚችል፤ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ቀጠሮዎች ስለሚተጓጎሉ ውሳኔዎች ያለቅጥ መዘግየታቸው አይቀርም"::[9]

ለማጠቃለል፤ መደበኞቹን የሥነ ሥርዓት ደንቦች በመከተል በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ግለሰቦች በሙሉ "በየስማቸው በአንድ መዝገብ ውስጥ በማጠቃለል የጣምራ ክስ ይቅረብ ቢባል ገቢራዊ ማድረግ ስለሚያዳግት ፍትሕን የማዛባት ውጤት እንደሚኖረው ግልጽ ነው:: ይህም የሚሆንበት ምክንያት ክሱ የሚመለከታቸው እነማን እንደሆኑ ማረጋገጡ ራሱ አስቸጋሪ በመሆኑና ማረጋገጥም የሚቻል ቢሆን እንኳን በሞት ወይም በሌላ ምክንያት የተሳታፊዎቹ ቁጥርና ማንነት በየጊዜው ሊለዋወጥ ስለሚችል ነው::"[10] ከዚህም በላይ፤ ሊሆን አይችልም እንጂ ምናልባትም ተሳክቶ የቡድኑ አባል ሊሆን የሚችለውን እያንዳንዱን ግለሰብ በትክክል ለይቶ ማረጋገጥና አድራሻውንም ማወቅ የሚቻል ቢሆን እንኳን እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ክሱ ውስጥ የመግባት ፍላጎት ላይኖራቸው፤ ቢኖራቸውም የሚያስገኝላቸው ጠቀሜታ ሲመዘን እንዲያፈገፍጉ ሊያደርጋቸው ይችላል::[11] ይህ ደግሞ በአደጋ ምክንያት በሚነሱ የአካል ጉዳት ክሶች ላይ በተለይም ሊያጋጥም ይችላል:: አንድ አደጋ በብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ ሁሉም በእኩል ደረጃ ስለማይጎዱ አነስተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ክሱን ለመከታተል ከሚያስከትለው ወጭና ከሚወስደው ጊዜ አንጻር ክስ ከማቅረብ ይልቅ መተውን ሊመርጡ ይችላሉ::[12] ስለዚህም፤ የቡድን ክሶች ዓላማ አያሌ ተከራካሪ ወገኖችን አጣምሮ ማቅረብ ወይም እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ያለውን የይገባኛል ጥያቄ በተናጠል ማስተናገድ በገቢር አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ የግለሰቦች ተናጠል የይገባኛል ጥያቄዎች ከሌሎች ግለሰቦች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ጋር በአንድነት የሚዳኙበትን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው::[13] ይህን በመሰሉ ጉዳዮችም፤ የቡድን ክሶች የተበደለ የፍትሕ መድረክ እንዳያጣና ፍትሕም እንዳይዘገይ ለመከላከል ይረዳሉ::

## 2. <u>የቡድን ክስ አጀማመር</u>

መደበኞቹን የሥነ ሥርዓት ደንቦች በደረቁ በመተርጎም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ባለጉዳዮች እያንዳንዳቸው በተናጠል ክስ ያቅርቡ ቢባል አያሌ ክሶችን ማስተናገዱ ሊያስከትል የሚችለውን አላመቺነት፤ በወል ያቅርቡ ቢባል ደግሞ የሚመለከታቸውን በሙሉ አሰባስቦ የጣምራ ክስ ማቅረብ የማይቻል ወይም በተግባር ሊሳካ የማይችል በመሆኑ፤ የእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ድምር ውጤት የፍትሕ መዛባትን ሊያስከትል እንደሚችል ከላይ ተመልክተናል:: እንግዲህ፤ በዓይነቱ ልዩ የሆነው የቡድን ክስ ሥርዓት አስፈላጊነቱ የመነጨው ይህን የመሰለው ሁኔታ እንዳያጋጥም ለመከላከል ነው:: የደንቡ

---

[9] አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲዩት፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 417::

[10] ብራውንና ሌሎች፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 553::

[11] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 557፤ ጃጅ ኢቫንስ በዊክስ ቪ. ባሬት አይል ካምፓኒ ጉዳይ ያለውን በመጥቀስ::

[12] አብርሃም ኤል ፓመራንትዝ፥ "ኒው ዲቨሎፕመንትስ ኢን ክላስ አክሽንስ፤ ሀዝ ዜር ዲዝ ኔል ቢን ሳውንድድ" <u>ቢዝነስ ሎዩር፥</u> ቅጽ 25(1970 ዓ.ም.)፥ ገጽ 1259::

[13] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 681-2::

መሠረትና ጥንተ ምክንያቱም ይኸው ነው::[14] ለቡድን ክስ ሥርዓት ምንጩ ርትዕ (equity) ነው::[15] ርትዕ ዕውቅና ሊሰጠውና ሊቀበለው የቻለውም እንደ ምግብ እንደ ልብስ የግድ የሚፈለግ መፍቅድ (necessity) በመሆኑ ነው:: በውሳንያተ ሕግ አግባብ ለሚለው አጠቃላይ ደንብ ተሰናን ሆኖ ተቀባይነት ሊያገኝ የቻለውም ከዚህ የተነሳ ነው::[16] በዚህም ሥርዓት አማካይነት፣ ፍርድ ቤቶች "የተከራካሪ ወገኖችና የፍርድ ቤቶች ጊዜና ንዋይ እንዳይባክን ለማድረግና አንድ ከሌሎች አያሌ ሰዎች ጋር የሙግት ተሳታፊ የሆነ ግለሰብ መብቶችና ግዴታዎችም ከሌሎቹ ጋር ባንድነት በፍርድ አደባባይ እንዲረጋገጡለት ለማድረግ" የሚያስችላቸው ሥልጣን አላቸው::[17]

በመሆኑም፣ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻው ሩብ ምዕተ ዓመት ጀምሮ በኮመን ሎው ተከታይ አገሮች የርትዕ ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓትን በሥራ ላይ በማዋል በጊዜው የነበሩትን የሥነ ሥርዓት ደንቦች ጥብቅነት ለማለዘብ ሲጠቁሙበት ቆይተዋል::[18] ይኸውም አሠራር፣ ስለተከራካሪ ወገኖችና ስለጣምራ ክሶች ፀንተው የቆዩትን ጥብቅ ደንቦች አንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወደጎን ለመተው አስችሏቸዋል:: ከጅምሩ ይሠራበት በነበረው መልኩ፣ የቡድን ክስ፣ አንድ በርካታ ሰዎችን ያቀፈ ሰብስብ መላ አባላቱ ለአንድ ክርክር መነሻ በሆነ ጉዳይ የሚያስከብሩት የጋራ መብት ወይም የሚካፈሉት የወል ጥቅም ወይም የየአንዳንዳቸው የይገባኛል ጥያቄዎችና የሚያስከትሏቸውም ጭብጦች የሚጋሩት መነሻ የክስ ምክንያት ያላቸው ሆኖ ሳለ ከአባላቱ ቁጥር ብዛት የተነሳ ግን ሁሉንም አባላት አሰባስቦ በስማቸው ወይም በወኪላቸው አማካይነት የጣምራ ክስ ለማቅረብ የማይቻል ወይም ተገብሮአዊነቱ የማይሳካ በሚሆንበት ጊዜ የርትዕ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን የሚቀርብ አቤቱታና ፍርድ ቤቱም እንደ ጥንቱ አባባል አቤቱታውን በመቀበል የሚሰጠው "የሰላም ትዕዛዝ" ነው::[19] ይህንኑም ደንብ ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ሌላ ታዋቂ የሕግ ሰው ተመሳሳይ በሆነ መልክ እንደሚከተለው ገልጾታል፣ "በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች በቁጥር አያሌ ሲሆኑና የቀረበው ክስም የተመሠረተው ለሁሉም የጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ ከሆነ ከአያሌዎቹ መካከል ጥቂቶቹ በራሳቸውም ሆነ በሌሎቹም ስም ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላሉ::"[20]

---

[14] አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲውት፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 419-431::

[15] ሁዊይተን፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 401፥ የመጀመሪያው የቡድን ክስ በ1676 ዓ.ም. ሁለተኛው ደግሞ በ1701 እንደቀረበ ይገልጻል::

[16] አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲውት፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 417፥ ዊሊያም ዊርት ብሉም "ዘ 'ኮመን ኩዌሽን' ፕሪንስፐል ኢን ዘ ክድ ፕሮቪዥን ፎር ሪፕሬዜንታቲቭ ሱትስ" ሚቺጋን ሎው ሪቪው ቅጽ 30(1932)፥ ገጽ 879::

[17] አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲውት፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 417::

[18] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 682::
[19] ዝኒ ከማሁ::

[20] ቻርልስ ፊስክ ቢች፣ ኤ ትሪቲዝ አን ሞደርን ፕራክቲስ ኢን ኤኩቲ፥ ደብሊው ኤች አንደርሰን ኤንድ ካምፓኒ፥ ሲንሲናቲ፥ ኦሀይዎ፥ ቅጽ 6፥ (1894) ገጽ 79::

ከላይ ከተገለጸው በቀላሉ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ይህ የርትዕ ፍርድ ቤቶች ያፈለቁት መሠረተ ሀሳብ ተፈጻሚ የሚሆነው ለአንድ ዓይነት የቡድን ክሶች ብቻ ነው:: ይህም በዓይነታቸው፣ መላ አባላቱ የሚያስከብሩት የጋራ ጥቅም ያላቸው ሆኖ ሳለ በቁጥር ግን አያሌ ከመሆናቸው የተነሳ ሁሉንም አባላት በአንድነት ማጣመሩ የማይቻል ወይም በገቢር የማይሳካ ክሶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን የቡድን ክስ ነው:: በእንደዚህ ዓይነት ክሶችም የቁጥር አያሌነት የጥቅምም መጋራት መኖሩን ማሳየት አስፈላጊ ነው::[21] እንዲሁም፣ "በኮመን ሎው ውስጥ እንደ አሁኑ ዘመን ዓይነት የቡድን ክስ ሥርዓት ባለመኖሩ" ደንቦቹ ተፈጻሚ ይሆኑ የነበሩት ርትዕን ተመርኩዘው በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነበር::[22] እንግዲህ ለቡድን ክሶች ተፈጻሚ የሚሆኑት ዘመናዊዎቹ ደንቦች የተወሰኑ ማሻሻያዎች ተደርጎባቸው የተወረሱት ከዚህ ምንጭ ነው::[23]

ይህን የመሰለውን ጉዳይ በሚመለከት የመጀመሪያው የሆነው የፈልድ መድበለ ሕግ (ኮድ) ለቡድን ክሶች ተፈጻሚ የሚሆነውን ደንብ እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል:-

> "የቀረበው ጥያቄ የብዙ ሰዎች የጋራ ጥቅም ጥያቄ በሚሆንበት ጊዜ ወይም ተከራሪዎቹ ወገኖች በቁጥር እጅግ በርካታ በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ፊት በግንባር እንዲቀርቡ ለማድረግ በገቢር አዳጋች ሲሆን ከመካከላቸው አንዱ ወይም ጥቂቶቹ የሁሉንም ጥቅም ለማስከበር ሊከሱና ሊከሰሱ ይችላሉ::[24]

በዚህ ደንብ አቀራረብ መሠረት፣ አንደኛው በክሱ ውስጥ በቀረበው ጥያቄ ላይ ተከራካሪዎቹ ወገኖች የጋራ ጥቅም ያላቸው በሚሆንበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በቁጥር አያሌ በመሆናቸው ሁሉንም ፍርድ ቤቱ ፊት ለማቅረብ በገቢር ሊሳካ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆን፣ ሁለት ዓይነት ቅርጽ ያላቸው የቡድን ክሶች አሉ ማለት ነው:: በብዙ የአሜሪካ ግዛቶች የኋላ ኋላ ተቀባይነት እያገኘ የመጣውና አሁንም የሚሠራበት ይኸው በመጀመሪያ በፈልድ መድበለ ሕግ ላይ የሠፈረው አመለካከት ነው::[25]

ከ1938 ዓ.ም. በፊት የቡድን ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት በፌዴራል ደረጃ ይመራ የነበረው "ፌዴራል ኢኩቲ ሩልስ ኤንድ ኮንፎርሚቲ አክትስ" እየተባለ በሚጠራው ሕግ ነበር:: የዚሁ ሕግ ደንብ (አንቀጽ) 48 እንደሚከተለው ይደነግጋል:-

> "ተከራካሪዎቹ ወገኖች በቁጥር እጅግ አያሌ ሲሆኑና ከባድ እንግልትና የቀጠሮ መንዛዛትም ሳያስከትል ፍርድ ቤቱ ፊት ሊቀርቡ የማይቻል ሲሆን ሁሉም እንዲቀርቡ ከማድረግ ይልቅ ፍርድ ቤቱ በመሰለው ከመካከላቸው የከሳሾችንም ሆነ የተከሳሾችን ተጻራሪ ጥቅሞች በሚገባ ሊያስከብሩ ይችላሉ ብሎ የገመታቸውን በቂ ወገኖች በክሱ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ክሱን ሊሰማ ይችላል:: <u>ይህ በሚሆንበትም ጊዜ የሚሰጠው ፍርድ በክሱ ውስጥ ያልገቡትን ተከራካሪ ወገኖች መብቶችና የይገባኛል ጥያቄዎች የሚነካ ሊሆን አይችልም</u>::"[26] (ሰረዝ የተጨመረ)

---

[21] ሁዊተን የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 415 ይመልከቱ፤ የእንግሊዝ አሠራርም ይኸው ነበር፥ ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 414 ይመልከቱ፤ ለዚህ ነጥብ፥ ተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ በታች በዚህ ጽሑፍ ገጽ10 ይመልከቱ::

[22] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊይተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 682::

[23] ዝኒ ከማሁ::

[24] ዝኒ ከማሁ::

[25] ዝኒ ከማሁ፤ በተጨማሪም ብራውን ኤት አል፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 554፥ ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 228፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁ.48 ይመልከቱ፤ ስለሁለቱ የቡድን ክስ ገጽታዎች ከዚህ በታች ከገጽ 10-13 ይመልከቱ::

[26] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 682-3::

በግልጽ ለማስተዋል እንደሚቻለው፤ የዚህ ድንጋጌ ስርዝ የተጨመረበት ክፍል አገላለጽ የቡድን ክስን *መሠረታዊ* ባሕርይ የሚገፍ ይዘት ያለው ነው::[27] ምክንያቱም፤ የቡድን ክስ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት፣ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙ ተከራካሪ ወገኖች ያሏቸውን የጋራ የክስ ጭብጦች በሙሉ በአንድ ክስ ለመወሰንና እነዚህም ውሳኔ ያገኙ ጭብጦች የሚያስከትሉት መብትና ግዴታ ስማቸው በመዝገብ ውስጥ በሰፈረው ተከራካሪ ወገኖች ላይም ሆነ ቀርበው ባልተከራከሩ ወገኖች ላይ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ስለሆነ ነው:: የቡድን ክስ ሥርዓት በተስናንነት ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገውም *በፍርድ ያለቀ የደቀቀ* (res judicata) የሚለውን የሕግ *መሠረተ* ሀሳብ ተፈጻሚ በማድረግ የፍርድ ቤቱንና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜና ወጭ ለመቆጠብ በማሰብ ነው:: ስለሆነም፤ ከዚህ ነጥብ አኳያ ደንብ ቁጥር 48 የቡድን ክስ አንዱ መሠረታዊ የሆነውን ጥያቄ ሊፈታ የሚችል መልስ ማስገኘት አልቻለም:: ይኸውም ጥያቄ፤ የኤኩቱ ደንቦች በ1912 እና በ1938 ዓ.ም. በተደጋጋሚ ቢሻሻሉም እንኳ እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ሳይፈታ ቆይቷል::

ከ1912 ዓ.ም. እስከ 1938 ዓ.ም. ድረስ የቡድን ክሶች ሥርዓት ይመራ የነበረው በ1912 ዓ.ም. በወጣው የኤኩቲ ደንቦች አንቀጽ ወይም ደንብ ቁጥር 38 ነበር:: ይኸውም ደንብ "የጋራ ወይም ጠቅላላ ጥቅም" መኖርን እንደ መስተገብርነት ቢሸረውም የደንብ 48ትን ሌሎች ሕፀፆች ሳላልዳሰሳቸው አንቀጽ 38ትን ተመርኩዘው የሚሰጡ ፍርዶችን የተፈጻሚነት አድማስ በተመለከተ እንደ በፊቱ ጊዜ ጥያቄዎች ማነሳታቸው አልቀረም::[28]

የፌዴራል ሥነ ሥርዓት ሕግ በ1938 ዓ.ም. ሲደነገግ የቡድን ክሶችን የሚመለከተው የዚሁ ደንብ ክፍል ደንብ ቁጥር 23 ነበር:: ይኸውም ደንብ "የቀድሞው ኤኩቲ ደንብ ቁጥር 38 ክለሳ ተደርጎ ይቆጠር ነበር::[29] ደንብ 23 የቡድን ክሶችን በሚከተለው አኳኋን ይከፍላቸዋል:: እነዚህም፤ አንደኛ፥ በሙያው በተሠማሩት ሰዎች አጠራር "ርቱዐን" የመደብ ክሶች የሚባሉት ሲሆኑ በይዘት ረገድም በአጠቃላይ የቡድን ክስ የማይፈቀድ ቢሆንም እንኳን በአንድ ክስ ጥቅም ያላቸውን ተከራካሪ ወገኖች በሙሉ በክሱ ውስጥ ማጣመር የግድ አስፈላጊ የሚሆንባቸውን ክሶች የሚመለከቱ ናቸው:: ሁለተኞቹና ሶስተኞቹ ደግሞ በቅደም ተከተል "ዝንቅ" የቡድን ክስ እና "ኢርቱዐን" የቡድን ክስ የሚባሉት ናቸው:: በአተረጓጎምም፤ "ዝንቅ" የሚባሉት በመሠረቱ አያሌ ክሶችን በውስጣቸው የሚያቅፉ ቢሆንም ለክሱ መነሻ የሆነን አንድን የተወሰነ ንብረት በተለይ የሚመለከቱ ወይም ሊመለከቱ የሚችሉ ክሶች ናቸው:: "ኢርቱዐን" የሚባሉት ደግሞ እንደገናም በውስጣቸው አያሌ ክሶችን የሚያካትቱ ቢሆንም እነዚሁ የጋራ የሆነ የሕግ ወይም የኩነት ጥያቄ የሚያስነሱና የጋራ መፍትሔም የሚሹ የቡድን ክሶች ናቸው::[30] ይልቁንም የደንብ ቁጥር 23 (1938) ዋናው ፋይዳ ራሱን ችሎ በተለይ ይሠራበት የነበረውን የፌዴራሉን የቡድን ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት የአፈጻጸም አድማስ በማስፋት በመደበኛ ክሶችም ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረጉ ነው:: ሆኖም ግን በቡድን ክስ የተሰጠ ፍርድ ቀርበው ባልተከራከሩ ወገኖች ላይ ስላለው የአስገዳጅነት ውጤት ቀደም ሲል የነበረው ጥርጣሬ ከደንቡ መውጣት በኋላም ቢሆን መፍትሔ

---

[27] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 683::

[28] ዝኒ ከማሁ፥ ይህ ጥያቄ ፌዴራል ሩል ኦፍ ሲቪል ፕሮሲጀር በ1966 ዓ.ም. እስከሚሻሻል ድረስ ሊቀጥል ችሏል፤ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 427-30 ይመልከቱ::

[29] ቴፕሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 683::

[30] የኤኩቲ ሩል ቅጂ በዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 683-4፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 276 ላይ ይገኛል:: እንደዚሁም ደግሞ በብራውን ኤት አል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 554-5 ተጽፎ ይገኛል::

ሊያገኝ አልቻለም።[31] "በአንድ የቡድን ክስ ላይ የተሰጠ ፍርድ የአፈጻጸም ወሰንን የሚመለከት በደንቡ ላይ ቁርጥ ያለ መሪ ቃል ካለመኖሩም የተነሳ ፍርድ ቤቶች 'ርቱዐን' የቡድን ክሶችን በሚመለከት የተሰጡ ፍርዶች በሁሉም የቡድን አባላት ላይ ተፈጻሚ ሲሆኑ 'ዝንቅ' እና 'ኢርቱዐን' የቡድን ክሶችን በሚመለከት የተሰጡት ፍርዶች ደግሞ ቀርበው በተከራከሩት አባላት ላይ ብቻ አስገዳጅ ይሆናሉ ከሚል ውሣኔ ላይ ደርሰዋል።"[32] ከዚህም በላይ፣ የቡድን ክሶችን "ርቱዐን"፥ "ዝንቅ" እና "ኢርቱዐን" በሚል ስያሜ መከፋፈሉ ራሱም ቢሆን በፍርድ ቤቶችም ላይ ሆነ በባለሙያዎች ላይ ግራ የሚያጋባ ሁናቴን ፈጥሯል።[33] የሦስት ዐሥርት ዓመታት የአሠራርና የአፈጻጸም ተሞክሮ ደንብ ቁጥር 23 እንከን እንዳለበት ሊያሳይ ችሏል። ስለዚህም በ1966 ዓ.ም. በአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሻሻል ተደረገ። በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ላለው የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ሕጋዊ መሠረት የሆነው በዚህ ሁኔታ የተሻሻለው ደንብ 23 ነው። ዛሬ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችና የፌዴራሉን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ደንብ በተቀበሉ የአሜሪካ ግዛቶች የቡድን ክሶች የሚመሩት በደንብ ቁጥር 23 ድንጋጌዎች ስለሆነ እነዚሁ ድንጋጌዎች "በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች ደረጃ ስላለው የቡድን ክስ አሠራር ጥሩ የሆነ አጠቃላይ ሥዕል" ይሰጡናል።[34]

### 3. <u>የቡድን ክስ ባሁኑ ጊዜ የሚገኝበት ደረጃ</u>

በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ዘንድ እየተሠራበት ያለው የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት እጅግ የበለጸገ ሥነ ሥርዓት መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል።[35] ለዚህ የበለጸገ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ሕጋዊ መሠረቱ የተሻሻለው ደንብ ቁጥር 23 ነው። ደንብ 23 "ርቱዕ"፥ "ዝንቅ" እና "ኢርቱዕ" የሚሉትን የቡድን ክስ ልዩነቶች አጥፍቷል፣ በምትኩም የቡድን ክስ ለመፍቀድ አስፈላጊ የሆኑ አራት ቅድመ ግዴታዎችን ይደነግጋል። እነዚህም አራት ቅድመ ግዴታዎች፣[36]

1. የቡድን አባላት ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉንም አባላት ለማጣመር አስቸጋሪ መሆን አለበት፤

2. ለቡድኑ አባላት የጋራ የሆኑ የሕግ ወይም የኩነት ጥያቄዎች መኖር አለባቸው፤

3. የተወካዮቹ የይገባኛል ጥያቄዎች ወይም መከላከያዎች ከሌሎቹ የቡድን አባላት የይገባኛል ጥያቄዎች ወይም መከላከያዎች ጋር አምሳልነት ያላቸው መሆን አለባቸው፤

4. ተወካዮቹ ተከራካሪዎች የቡድኑን አባላት ጥቅም ፍትሐዊና በቂ በሆነ ሁኔታ ለማስጠበቅ የሚችሉ መሆን አለባቸው፤ የሚሉት ናቸው።

በተጨማሪም ሁሉንም አባላት በመወከል ክስ የሚያቀርብ ወይም የሚከላከል ሰው፣ ጉዳዩ ከሚከተሉት ዘርፎች ባንዱ ሥር የሚጠቃለል መሆኑን ማሳየት[37] መቻል አለበት።

---

[31] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 683።

[32] ዊሊያም ኤ. ፍሪድላንደር፥ "ሲቪል ፕሮሲጀር-ፌዴራል ሩል 23 አግሪጌሽን ኦፍ ክሌይምስ ኢን ክላስ አክሽን" <u>ቱሌን ሎው ሪቪው</u>፥ ቅጽ 43 (1969)፥ ገጽ 363።

[33] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 364።

[34] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 686።

[35] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23 ይመልከቱ።

[36] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 686።

[37] ዝኒ ከማሁ፥ ለተሻሻለው ሩል 23 ቅጅ፤ ፍሪድላንደር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 364-5 ይመልከቱ።

1. የቡድኑ አባላት በተናጠል ቢከሱ ወይም ቢከላከሉ፣

   (ሀ) ለአንዱ አባል የሚሰጠው ፍርድ ለሌላው አባል ከሚሰጠው ፍርድ ጋር የሚቃረን ወይም የሚለይ በመሆኑ የቡድኑን አባላት በመጻረር የቆመው ወገን እርስ በርሱ የሚጋጭ ተግባር እንዲፈጸም የሚያደርገው መሆኑን፣ ወይም

   (ለ) እያንዳንዱን የቡድን አባል በሚመለከት የሚሰጠው ፍርድ በአፈጻጸም ወቅት ፍርድ ቤት ያልቀረቡትን የቡድን አባላት ጥቅም የሚነካ ወይም ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ያላቸውን ዕድል በሰፊው የሚቀንስ ወይም የሚያሰናክል መሆኑን፣ ወይም

2. የቡድኑን አባላት በመፃረር የቆመው ወገን የሁሉንም የቡድን አባላት ጥቅም የሚመለከቱ ድርጊት መፈጸሙን ወይም ለመፈጸም እምቢተኛ መሆኑንና ይህም ድርጊቱ ቡድኑን ባጠቃላይ የሚመለከት የመጨረሻ የእግድ ትዕዛዝ መስጠትን ወይም ተመጣጣኝነት ያለው የመፍትሔ ውሳኔ ማሳለፍን አስፈላጊ የሚያደርግ መሆኑን፣

3. ግለሰብ የቡድን አባላትን ከሚመለከቱት የሕግ ወይም የኩነት ጥያቄዎች ይልቅ የቡድኑን አባላት በጋራ የሚመለከቱት የሕግ ወይም የኩነት ጥያቄዎች ይበልጥ የሚያመዝኑ መሆኑንና በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊና ቀልጣፋ ፍርድ ለመስጠትም የቡድን ክስ ይበልጥ ተስማሚ መሆኑን።

ከዚህ ላይ እንግዲህ በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 23 መሠረት አንድ የፍርድ ቤት ክርክር በቡድን ክርክር መልክ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚቻለው ከላይ የተገለጹት አራት አስፈላጊ ሁኔታዎች ሲሟሉና ክርክሩም ከሦስቱ የቡድን ክስ ዘርፎች ባንዱ የሚጠቃለል ሲሆን ብቻ መሆኑ በጉልህ ይታያል።

የአራቱን የቡድን ክስ ቅድመ ግዴታዎች መሠረታዊ ይዘት እንደሚከተለው ባጭሩ መዳሰስ ይቻላል።[38]

ሀ. <u>አያሌነት</u>፡- ይህ ቃል በቡድኑ ውስጥ ያሉት አባላት በቁጥር ብዛት ያላቸው በመሆኑ ሁሉንም በግለሰብ ደረጃ አጣምሮ ለማቅረብ አዳጋች መሆኑን የቡድኑ ተወካይ ማሳየት እንዳለበት ለማመልከት ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት ቃል ነው፤[39] ማለትም "ከቡድኑ አባላት ቁጥር ከፍተኛነት የተነሣ አባላቱን ሁሉ አጣምሮ የማቅረቡ ሁኔታ ስኬታማነት አስቸጋሪ ሲሆን ነው።"[40] በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎችን የማጣመሩ ሁኔታ ስኬታማነት አስቸጋሪ የሚሆነው ምን ሁናቴዎች ሲያጋጥሙ ነው? የሚለው ጥያቄ ከየጉዳዩ የተለየ ሁኔታ ጋር ተያይዞ መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው። *በሀንስበሪና ሊ ጉዳይ* (1940 ዓ.ም.) የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደወሰነው፣ ክሱ የሚመለከታቸው ወገኖች በሙሉ እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ እንኳን ቢቻል በሞት ወይም በሌላ ምክንያት በየጊዜው ለውጥ መደረጉ ስለማይቀር እንደ መደበኛው የክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት የሁሉም ስም በፍርድ ቤቱ መዝገብ ላይ እንዲገለጽ ማስገደዱ በተከራካሪ ወገኖች ማንነት ላይ በየጊዜው ሊያስከትል ከሚችለው ተቃውሞ የተነሳ በውጤቱ ፍትሕን እንደማጓደል ይቆጠራል።[41] ከዚህም በላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሁሉም ሰዎች ተመሳሳይ አስተሳሰብ የላቸውም። በመሆኑም በአንድ ክስ ውስጥ ሁሉም፥ በተለይም ደግሞ ከክሱ የሚያገኙት ጥቅም በጣም አነስተኛ በመሆኑ ክስ ማቅረቡ ራሱ

[38] ይዜል፥ ገጽ 967-9፤ የቡድን ክስ ዘርፎችን በሚመለከት ከዚህ በታች በገጽ 14-16 ይመልከቱ።

[39] ዝኒ ከማሁ ገጽ 967።

[40] ዝኒ አዲ ከማሁ።

[41] ከብራውን ኤት አል ገጽ 553 የተጠቀሰ፥ አሜሪካን ሎው ኢንስቲትውት፥ ክፍል 86፥ ገጽ 417።

ፋይዳ ቢስ በሚሆንበት ጊዜ÷ በአንድነትና በፈቃደኛነት ይሳተፋሉ ብሎ መጠበቅ የማይመስልና በገቢርም ያጋጥማል ተብሎ የማይጠበቅ ነው::[42] ይህ የፍርድ ቤቱ አስተያየት የተመሠረተው፤ ተከራካሪ ወገኖች በቁጥር እጅግ ከፍተኛ በሚሆኑበት ጊዜ በሞትም ሆነ በሌላ ምክንያት መብቶቻቸውና ግዴታዎቻቸው መለዋወጣቸውና ከፍና ዝቅ የማለት ሁኔታ ማሳየታቸው አይቀሬ ስለሚሆን ያለ ከፍተኛ ችግር ሁሉንም በክሱ ውስጥ ተከራካሪ ወገኖች አድርጎ ለማቅረብ የማይቻል ሲሆንና እነዚህም ሁኔታዎች ተዳምረው የክሱ ሂደት ተገቢውን ሥርዓት ተከትሎ በፍርድ እንዳይደመደም አብዛኛውን ጊዜ መሰናክል መፍጠራቸው አይቀርም በሚል እሳቤ ላይ ነው:: ስለዚህም የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ስምና የመኖሪያ ሥፍራ ለማረጋገጥ፤ እንዲሁም በሞት ወይም በሌላ ምክንያት በተለዩት ተከራካሪ ወገኖች ምትክ የተወካዮቻቸውን ስም አረጋግጦ በመዝገቡ ውስጥ ለመጨመር፤ ወይም ደግሞ መጀመሪያ በነበሩት ተከራካሪ ወገኖች ፋንታ ክሱ ከተመሠረተ በኋላ በሽያጭ ጥቅማቸው በተላለፈላቸው ሰዎች ለመተካት አስቸጋሪ በመሆኑ፤ ቁጥራቸው አያሌ የሆነ ወገኖች በስም በስማቸው ተመዝግበው በክሱ ውስጥ መጣመር አለባቸው የሚለውን ግዴታ ማስቀመጡ ፍትሐዊ አሠራር አይሆንም::[43] ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች በየስማቸው መዝግቦ ማጣመሩ እንደ ግዴታ ከተጣለ የገቢራዊነቱ አስቸጋሪነት የሚመነጨው ከነዚህ ሁኔታዎች ነው:: ሆኖም ግን የተከራካሪ ወገኖች ቁጥር አያሌነት በራሱ ለመተግበር አስቸጋሪነትን (ኢገቢራዊነትን) አያመለክትም:: በሌላ አነጋገር ለመተግበር አስቸጋሪነት በራሱ ግምት የሚወሰድበት ጉዳይ አይደለም::[44] ለመተግበር አስቸጋሪነት ግምት የሚወሰድበት ጉዳይ ባለመሆኑም የቡድኑ ተወካይ የጋራ የሆኑ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ያሏቸው የተወሰኑ ሰዎች መኖራቸውንና እነዚህም ግለሰቦች ብዛት ያላቸው በመሆኑ ሁሉንም አጣምሮ በክሱ ውስጥ ማቅረብ በተግባር አስቸጋሪ መሆኑን አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት መቻል አለበት::[45] ስለዚህም አያሌነት የጋራ የሆነ ጥያቄ መኖር አለበት ከሚለው መሠረተ ሀሳብ ጋር የተቆራኘ ነው::

የተሻሻለው ደንብ ቁጥር 23 ይህን ጥያቄ የቀረጸው ችግር በሚያስከትል ሁኔታ ነው:: ድንጋጌው አንድ ክስ የቡድን ክስ ሆኖ እንዲቀጥል ይፈቀድ ዘንድ አንድም የቡድኑ አባላት ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉንም አጣምሮ ለማቅረብ አስቸጋሪ መሆን አለበት፤ ወይም ለቡድኑ አባላት የጋራ የሆኑ የኩነት ወይም የሕግ ጥያቄዎች መኖር አለባቸው የሚል ነው:: በዚህም ምክንያት የቡድኑን አባላት አጣምሮ ለማቅረብ አስቸጋሪ እስከሆነ ድረስ፤ ለቡድኑ አባላት የጋራ የሆኑ የኩነት ወይም የሕግ ጥያቄዎች ባይኖሩም የቡድን ክሱ ለመቀጠል የሚችል ይመስላል:: ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ፤ ምንም እንኳ ደንብ 23 በቁሙ ሲተረጎም የዚህ ዓይነት ውጤት ሊኖረው ቢችልምና አንዳንድ ፍርድ ቤቶችም ይህን አተረጓጎም ተከትለው ጉዳዮችን የወሰኑ ቢሆንም÷ ይህን ድንጋጌ በዚህ መልክ ተርጉሞ ተፈጻሚ ማድረግ ስህተት ነው የሚል አመለካከት አለ:: "የአንድ ቡድን አባላት ቁጥር ምንም ይሁን ምን፤ የቡድኑ አባላት የጋራ ጥያቄ ያላቸው ካልሆነ በስተቀር እየታየ ባለው ሕግ መሠረት በውክልና የሚካሄድ ክስ (የቡድን ክስ) ሊፈቀድ አይገባም:: ከዚህ በተለየ ሁኔታ መደምደም እጅግ ብዙ የሆኑ እርስ በርሳቸው ግንኙነት የሌላቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች በአንድ ክስ እንዲታዩ የማድረግ ውጤትን ያስከትላል::"[46] ይህን ጭብጥ አስመልክቶ ታዋቂው ፓመሮይ ራሱ የሚከተለውን እንደገለጸ ተጠቅሷል፤

---

[42] የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት÷ ብራውን ኤት አል እንደጠቀሰው÷ ገጽ 557::

[43] ሁዊተን ገጽ 414::

[44] ዝኒ አዲ ከማሁ::

[45] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 435::

[46] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 434::

> "የደንቡ ቋንቋ እነዚህ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ሁሉንም የሚመለከት አጠቃላይ ወይም የጋራ የሆነ ጥቅም ሊኖራቸው እንደሚገባ ግልጽ በሆነ መንገድ አያመለክትም:: ሆኖም ለውሣኔ የቀረበው ጥያቄ የሁሉንም ጥቅም በጋራ ወይም በአጠቃላይ የሚመለከት ካልሆነ በቀር ገቢራዊነቱ እስከ ሚያስቸግር ድረስ እጅግ ብዛት ያላቸው ግለሰቦች በአንድነት ሆነው በከሳሽነት ክስ የሚመሠርቱበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል ብሎ ማሰቡ አስቸጋሪ ነው::"[47]

ለ. <u>ጋርዮሽነት</u>::- በቡድን አባላት መካከል "የጋራ ጥቅም" ሊኖር ይገባል የሚለውን ቅድመ ግዴታ አስታኮ አብዛኛውን ጊዜ የሚነሳውና ብዙ ሙግትም ያስከተለው አከራካሪ ጭብጥ "የጋራ ጥቅም" ሲባል ልኩ ወይም መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚለው ጥያቄ ነው:: ፍርድ ቤቶች ለዚህ ጥያቄ የሰጡአቸውን መልሶች ስንቃኝ የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን:: አንዳንዶቹ ፍርድ ቤቶች ተከራካሪዎቹ ወገኖች በሕግ የጣምራ ክስ ለማቅረብ ከሚያስችላቸው በሁለንተናው ያልተለየ *የጋራ ጥቅም* ሊኖራቸው ይገባል በማለት ሲወስኑ[48] አንዳንዶቹ ደግሞ *የወል* ወይም *ዕሩይ* ጥቅም ሊኖራቸው ይገባል ይላሉ::[49] እንዲሁም፤ አንዳንዶቹ የጥቅም *ኅብረት* ሊኖራቸው ይገባል በማለት ሲወስኑ[50] ሌሎቹ ደግሞ *እዩይ* ጥቅም ወይም *ተመሳሳይ* ጥቅም ሊኖራቸው ወይም *ዕጣ ፈንታቸው ተመሳሳይ* ሊሆን ይገባል በማለት ወስነዋል::[51]

ነገር ግን ከፍርድ ቤቶቹ አንዱም እንኳን ይህን አጠቃላይ ወይም የጋራ ጥቅም የተባለውን ቅድመ ግዴታ ለማመልከት የተጠቀመባቸውን ቃላት በጥሬው ከማስቀመጥ አልፎ ትርጓሜ አልሰጣቸውም:: ሆኖም ግን እነዚህ የተለያዩ ቃላት የቡድን ክስን ወሰን ወይም ዳር ድንበር የማጥበብ ወይም የማስፋት ውጤት ያላቸው መሆኑን ለመገንዘብ አዳጋች አይሆንም:: በአሁኑ ዘመን ያለውን አመለካከት ስናይ የቡድን ክስ የተፈጻሚነት ዳር ድንበር ሰፋ ተደርጎ መከለል እንዳለበት የሚደግፍ ነው:: ስለዚህም የቡድኑ አባላት የተጣመረ ወይም አንድ ዓይነት የሆነ ጥቅም ያላቸው መሆኑን ማሳየት አስፈላጊ አይሆንም:: "ጉዳዩ በሚያስነሳቸው መሠረታዊ የኩነትና የሕግ ጭብጦች ላይ" ሁሉንም ባለጉዳዮች የሚያስተሳስር መጠነኛ የሆነ የጋራ ጥቅም እንዳለ ማሳየቱ በቂ ነው::[52] በእርግጥ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ምን ጊዜም ቢሆን በጋራ የሚያስተሳስሯቸው ነገሮች መኖራቸው የማይቀር የሆነውን ያህል ከሌሎቹ ጋር የማይዛመዱ የየግላቸው የሆኑ ነገሮች ሊኖሩም ስለሚችሉ አጋጣሚው ለክርክር በር መከፈቱ አይቀርም:: ለምሳሌም ያህል፤ በአንድ ለፍርድ ቤት በቀረበ ጉዳይ ተከሳሾች በአንድ ለመስኖ በሚያገለግል የውሃ ቦይ ላይ ግድብ ይሠራሉ:: ግድቡም የውሃው ከፍታ እንዲጨምር በማድረጉ ከበስተበታቹ ባሉት ረባዳ ሥፍራዎችና የእርሻ ማሳዎች ላይ ጉዳት በማድረሱ በአካባቢው ያሉ ባለርስቶች:-

(ሀ) የውሃ ቦዩ ያለአንዳች ግድብ ወይም ሌላ መሰናክል ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ እንዲፈስ ያላቸው መብት እንዲረጋገጥላቸው፤

(ለ) ተከሳሾቹ በውሃው መውረጃ ቦይ ላይ የገነቡትን መሰናክል እንዲ ያነሱ ትዕዛዝ እንዲጣልባቸው፤

(ሐ) ተከሳሾቹ ወደፊት ይህን የመሰለ ግድብ ከመገንባትና ከመሥራት እግድ

---

[47] ፓመሮይ፥ በሁዊተን፥ ገጽ 415 እንደተጠቀሰ::
[48] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 410::
[49] ብሉም፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 894-5፥ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 407-8::
[50] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 895::
[51] ሁዊተን፤ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 407-8::
[52] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 880-95፥ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 434::

እንዲጣልባቸው፤ እና

(መ) ስለደረሰበት ጉዳት ከእያንዳንዱ ተበዳይ ጋር ሂሳብ እንዲተሳሰቡ እንዲታዘዝላቸው፤

በመጠየቅ ባቀረቡት ክስ፤ "ብዛት ያላቸው ክሶች በተናጠል እንዳይቀርቡ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑና ፍርድ ቤቱም ይህን የመሰለው ክስ በርትዕ ሥልጣኑ ውስጥ የሚታቀፍ አድርጎ ከተቀበለው ክሱ የሚያስነሳቸውን ጥያቄዎች በሙሉ፥ የጉዳት ካሣውን መጠን ጥያቄ ጭምር፥ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ስለሚኖረው አቤት ባዮች አንድነት ሆነው ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ" በማለት ተወስኗል::[53] እንግዲህ፤ ይህ ውሣኔ እንደሚያንፀባርቀው የቡድን ክስ ማቅረቢያ ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊ የሚሆነው አቤት ባዩችን የሚያስተሳስራቸው በቂ የሆነ የጋራ ጥቅም መኖሩን ብቻ ማሳየቱ እንጂ ከዚህ የላቀ የጥቅም ቁርኝት አይጠበቅም:: እንዲሁም እያንዳንዱን አቤት ባይ በተናጠል የሚመለከቱ ጭብጦች መኖራቸው የቡድን ክስ እንዳይቀርብ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም::[54]

በሌላ በኩል ደግሞ፥ አቤቱታ የቀረበበት ድርጊት ወይም ጥቃት በሁሉም ላይ የደረሰ በመሆኑ ሁሉንም ከሳሾች በጋራ የሚመለከታቸው ቢሆንም እያንዳንዱ ከሳሽ የድርጊቱ ሰለባ የሆነው በግለሰብ ደረጃ በተለየ መልኩ በመሆኑና ከዚህም የተነሳ ሁሉም ከሳሾች የጋራ ጥቅም አላቸው ሊባል ስለማይቻል ከከሳሾች መካከል የተወሰኑት ብቻ በራሳቸውና በሌሎቹም ስም የቡድን ክስ ለማቅረብ አይችሉም ተብሎ ተወስኗል::[55] በሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች፤ "የጉዳት ካሣ ለማግኘት በሚቀርብ ክስ እያንዳንዱ የቡድን አባል በራሱ ላይ የደረሰውን ጉዳትና የሚገባውን ካሣ ለማስረዳትና ለማረጋገጥ በክሱ ውስጥ ጣልቃ መግባት አለበት" የሚል ውሣኔ ተሰጥቶአል::[56]

ለዚህ የደንቡ ጠባቡ አተረጓጎም መንስኤው ፓመሮይ ያሳደረው ተጽዕኖ ነው የሚል አስተያየት ሲኖር ለዚህም ምክንያቱ ሕጉ ስለሚፈቅዳቸው የበደል ማካካሻ መፍትሔዎች ባቀረበው ጽሑፍ ላይ አንድ የቡድን ክስ ሊያሟላ የሚገባቸውን መስፈርቶች አስመልክቶ የሰነዘረው የሚከተለው ሀሳብ ነው:-

> "የቡድን ክስ ሊያሟላ ስለሚገባው መስፈርት የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት የሚከተለውን ሁኔታ በዓይነ ሕሊናችን እንቅረጽ:: በቁጥር አያሌ የሆኑ ሰዎች በአንድ ሙግት ውስጥ በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት በግንባር ቀርበዋል:: ክሱ በዚህ መልኩ እንዲቀጥል ከተፈቀደ ከመካከላቸው አንዱ በራሱ ስምና ሌሎቹንም በመወከል ሊከስ ወይም ሊከሰስ ይችላል:: ይህን የመሰለው መጣመር ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ ግን ከሕጉ አንቀጾች አንዱ የሚፈቅድ እንኳን ቢሆንም አንዱ ሌሎቹን በመወከል ክስ ሊያቀርብ ወይም ሌሎቹን እንደሚወክል ተደርጎ ክስ ሊቀርብበት አይችልም"::[57]

ስለዚህም፤ በዚህ መስፈርት መሠረት የተወሰኑ ሰዎች በራሳቸው ስምና ሌሎችንም ሁሉ በመወከል ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉት "ክሶቻቸው ለክሱ መነሻ ከሆነው

---

[53] ብሉም፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 883-4፥ በተጨማሪም ማርሻል ቢ. ግሮስማን፥ ፕሬሬኩዚትስ ኤንድ አዘር ሪኳየርመንትስ፥ ክላስ አክሽን 1975፥ ሊቲጌሽን ኮርስ ሀንድቡክ ሲሪስ ነምበር 71፥ ፕራክቲሲንግ ሎው ኢንስቲቲውት፥ ኒውዮርክ (1975)፥ ገጽ 17 ይመልከቱ::
[54]ጃጅ ቱረንታይን፥ በአልኮ ኢንተርናሽናል ግሩፕ ኢንኮርፖሬትድ ሴኪዩሪቲስ ሊቲጌሽን ጉዳይ፥ በይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 973፥ እንደተጠቀሰ::
[55]ቢች፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 84፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3::
[56] ብራውን ኤት. አል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 559::
[57] ከብሉም የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 898 የተጠቀሰ::

አንድ ተግባር ጋር ትስስርነት ካለው ድርጊት ወይም ካላቸው ድርጊቶች የመነጨ በሚሆንበት ጊዜ" ወይም "ተከራካሪዎቹ ወገኖች በሙሉ ለክሱ መነሻ በሆነው ጉዳይ ላይ ጥቅም ያላቸውና የተጠየቀውንም ዳኝነት ለማግኘት መብት ያላቸው" ሲሆኑ ብቻ ነው::[58] እንግዲህ፣ ይህን አተረጓጎም ከተከተልን፣ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ከጣምራ ክስ አቀራረብ ሥርዓት ያልተለየና የተጣለበትም ገደብ ተመሳሳይ ነው ማለት ነው:: ሆኖም፣ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓትን ጥብቅ የሆነው የጣምራ ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ካሳደረበት ተጽዕኖዎች አላቆ ሰፋ ያለ ትርጓሜ ሊሰጠው እንደሚገባ የሙያው ጠበብት ባለማሰለስ ያቀረቡዋቸው አሳማኝ ክርክሮች እንዲሁም የቈድሞው አሠራር በሥራ ላይ ያስከተላቸው ችግሮች ተዳምረው በአሁኑ ወቅት የቡድን ክስ ለብቻው የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት እንዲኖረው አስችለውታል:: ስለዚህም በአንድ ክስ ውስጥ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች የጋራ የሆኑ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ካሉ፣ እነዚህም የጋራ ጥያቄዎች ተከራካሪዎቹ ወገኖች በግለሰብ ደረጃ ካሏቸው ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ይልቅ ገዝፈው የሚታዩ ከሆነ፣ እንዲሁም የቀረበውን ክርክር ፍትሐዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመቋጨት የቡድን ክስ የላቀ አማራጭ ዘዴ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ይህን የመሰለው ክስ በቡድን ክስ መልክ እንዲቀርብ ተሻሽሎ የወጣው ደንብ 23 ይፈቅዳል::[59]

ለተከራካሪዎቹ ወገኖች የጋራ የሆኑት የሕግና የኩነት ጥያቄዎች እነዚሁ ወገኖች በተናጠል ካሏቸው ጥያቄዎች ግዝፈት አላቸው፣ እንዲሁም የቡድን ክስ ከሌሎች የክስ አቀራረብ ዘዴዎች የላቀ አማራጭ ነው ሊባል የሚቻለው ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው የሚሉት ጥያቄዎች ለፍርድ ቤቱ ውሣኔ የተተው ናቸው:: እነዚህንም ጥያቄዎች ለመወሰን ፍርድ ቤቱ የደንቡን ዓላማዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት:: እነዚህም ዓላማዎች፣ "ጊዜን፥ ጉልበትን፥ ወጭን መቀነስ እና በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሰዎች ተመሳሳይ ዳኝነት እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆኑ እነዚህንም ለመተግበር/ ሲባል ለፍትሕ ወርትዕ መሠረት የሆኑት የሥነ ሥርዓት መመሪያዎች መስዋዕት አለመደረጋቸውን ወይም ሌሎች ያልተፈለገ ውጤት የሚያስከትሉ ተግባራት የሚፈጸሙበት መንገድ አለመፈጠሩን በተጓዳኝ ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው::"[60] እንግዲህ ከደንብ 23 ድንጋጌዎች በግልጽ የምንረዳው ነገር አንድ የቡድን ክስ ለማቅረብ የጋራ ጥያቄ መኖሩን ማስረዳቱ ብቻውን በቂ አለመሆኑን ነው:: ይህ የጋራ ጥያቄ እያንዳንዱ አባል በተናጠል ከሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ገዝፎ የመውጣት ባሕርይ ሊኖረው ይገባል:: "በአንድ ጉዳይ ላይ የጋራ ጥያቄዎቹ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች የሚያስገኙት ጠቀሜታ የጉዳዩ ጉልህ ገጽታው ከሆኑና እነዚህም ጥያቄዎች ጊዜ ሳይፈጁ በአንድ ቀጠሮ ሊወሰኑ የሚችሉ ከሆኑ፣ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በተናጠል ያቀረቧቸውን ክሶች ለመወሰን የቱን ያህል ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ቢሆንም የጋራ ጥያቄዎቹ ግዝፈት እንዳላቸው ይቆጠራል::"[61] የቡድን ክስ ከሌሎቹ የላቀ የክስ አቀራረብ ዘዴ ነው የሚባለው ደግሞ፣ (ሀ) የቡድኑ አባላት በግለሰብ ደረጃ የሚያቀርቧቸው የጉዳት ካሣ ጥያቄዎች እጅግ አነስተኛ ከመሆናቸው የተነሳ የተናጠል ክስ ማቅረቡ ፋይዳ ቢስ ሲሆን፣ (ለ) ለክሱ መነሻ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ አስመልክቶ የሚመሠረቱት ክሶች በቀጠሮ ላይ መሆን የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ጊዜን በመቆጠብና ተመሳሳይ ዳኝነት በማስገኘት ረገድ ያለውን ፋይዳ የማይጎዳው፣ ተከራካሪዎቹም ወገኖች የተናጠል ክስ ለማቅረብ የጠነከረ ጉጉት እንደሌላቸው የሚያመለክት ሲሆን፣ (ሐ) ክስ የቀረበበት

---

[58] ሁዊተን፥ "ኤ እስተዲ ኦፍ ዘ እስታቲውትስ ሁዊች ኮንቴይን ዘ ተርም ሰብጀክት ኦፍ ዘ አክሽን ኤንድ ሁዊች አሪሌት ቱ ጆይንደር ኦፍ አክሽንስ፥ ኤንድ ፕሌንቲፍስ ኤንድ ቱ ካውንተርክሌይምስ"፣ <u>ኮርኔል ሎው ሪቪው</u>፥ ቅጽ 10(1932-33 ዓ.ም.) ገጽ 241.

[59] ለፌድራል ሩል ኦፍ ሲቪል ፕሮሲጀር እሩል 23(ቢ)፥ ከዚህ በላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 37 የተጠቀሱትን ምንጮች ይመልከቱ::

[60] ቴፕሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 691.

[61] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 692.

መድረክ ወይም ፍርድ ቤት ምስክሮች፥ ማስረጃዎችና ሌሎችም ተመሳሳይ ነገሮች የሚገኙበትን ሥፍራ በሚመለከት ረገድ ተስማሚ ሲሆን፤ እና (መ) እያንዳንዱን አባል በተናጠል የሚመለከቱት ጭብጦች እጅግ ብዙ ባለመሆናቸው የጎላ ችግር ሳያጋጥም ለማስተናገድና ላልቀረቡ አባላትም መጥሪያ እንዲደርሳቸው ሕጉ የሚጠይቀውን ግዴታ ለማሟላት የሚቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በሌላ አነጋገር፤ ከአባላቱ ብዛት የተነሳ ቡድኑ ለአስተዳደር የማያመች ስብስብ መሆን የለበትም።[62]

ሐ. <u>አምሳልነት</u>፡- (እንደገናም፤ ይህም ቃል ቢሆን፤ ወዶ ሳይሆን ባጋጣሚ ከነሱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያለ በመሆኑ ብቻ የቡድን ተወካዩ ጥቅሞች ከሚወክላቸው ከሌሎቹ የቡድን አባላት ጥቅሞች ጋር በዋና ዋና ገጽታዎቻቸው አንድ ዓይነት መሆን እንዳለባቸው ለማመልከት በሙያው የተሠማሩ ሰዎች የፈጠሩት ቃል ነው።

> "በቡድን ክስ ውስጥ፤ በግለሰብ ደረጃ በሚቀርብ ክስ የግል ባለጉዳይ ያለውን ሚና ተክቶ አስፈላጊዎቹን እርምጃዎች በመውሰድ ክርክሩን የሚመራውና የሚቆጣጠረው የቡድኑ ተወካይ ነው። ስለዚህም በክሱ ውስጥ ያልቀረቡትን የቡድን አባላት ጥቅሞች በሚገባ ለማስከበር እን ዲቻል የቡድኑ ተወካይ ከክሱ የሚያገኘው ጥቅምና በክሱ ለመግፋት ያለው የተነሳሽነት ስሜት ከአንድ የግል ባለጉዳይ ያልተናነሰ ሊሆን ይገባል። አምሳልነት ሲባልም ምስጢሩ ይኸው ነው።"[63]

ይህ ከላይ የሰፈረው መመዘኛም ሊሟላ የሚችለው ተወካዮች ሆነው የቀረቡት ባለጉዳዮች የይገባኛል ጥያቄዎችና መከላከያዎች ከተወከሉት ባለጉዳዮች የይገባኛል ጥያቄዎችና መከላከያዎች ጋር አምሳልነት ያላቸው በሚሆንበት ጊዜ ነው።[64] ስለዚህም፤ የተወሰኑ ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ስምና ሌሎችንም በስም ያልተጠቀሱ ወገኖችን በመወከል ያቀረቡት ክስ እንዲቀጥል ይፈቀድ ዘንድ መፍቻው ይህ የይገባኛል ጥያቄዎችና መከላከያዎች አምሳልነት ነው። ሆኖም ግን፤ ይህ አምሳልነት የተሰኘው መስፈርት የሚሟላው መቼና ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን የሚያስችል አንድ ብቸኛ ቀመር ሊኖር እንደማይችል በመስፈርቱ ውስጥ የታቀፉት ሀሳቦች ባሕርይ ራሱ ጠቋሚ ነው። ከዚህም የተነሳ፤ ሌላው ቀርቶ በመሠረቱ ተመሳሳይ ክሶች ያሏቸውን ጉዳዮች በተመለከተ እንኳን ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ውሣኔዎች ላይ ሲደርሱ ታይተዋል። ለምሳሌም ያህል፤ አንድ የተወሰነ ተግባር ለማከናወን ገንዘብ እንዲያዋጡ የመዋጮው ዓላማ ተገልጾ የደብዳቤ ጥሪ ከተላለፈላቸው ሦስት መቶ ሰዎች መካከል ሦስቱ ቀሪዎቹን በመወከል ያቀረቡት ክስ፤ የተወከሉት ሰዎች መዋጮ ሊያደርጉ የቻሉባቸው ሁኔታዎች ክስ አቅራቢዎቹ ሊያደርጉ ከቻሉባቸው ሁኔታዎች ተመሳሳይ ላይሆኑ ስለሚችሉ ሰስቱ ሁሉንም በአግባቡ ይወክላሉ ሊባል አይቻልም በማለት ተቀባይነት አጥቷል።[65] በሌላ ጉዳይ ደግሞ፤ በተወካዮቹና በተወከሉት የቡድን አባላት የይገባኛል ጥያቄዎች መካከል የሚታዩ የፍሬ ነገር ልዩነቶች የቡድን ክስ እንዳይፈቀድ ሊያስከለክሉ የሚችሉት ከእነዚህ ልዩነቶች የተነሳ የቡድኑ ጥቅሞች አደጋ ላይ የሚወድቁ ሲሆን ብቻ ነው በማለት ተወስኗል።[66]

ስለዚህም፤ አምሳልነት እንዳለ የሚቆጠረው ዋናውን ጥያቄ በተመለከተ በክሱ ውስጥ ወኪል ሆነው በቀረቡትና ጠርሶም ባለቀረቡት (ልሕሳን) ተከራካሪዎች ወገኖች ጥቅሞች መካከል ቅራኔ ወይም የተጻራሪነት ባሕርይ የሌለ እንደሆ ነው። ከዚህም

---

[62] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 693።

[63] ይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 967።

[64] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 687።

[65] ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 417።

[66] ጃጅ ቱረንታይን፥ በአልኮ ኢንተርናሽናል ግሩፕ ኢንኮርፖሬትድ፥ ሲኪዩሪቲስ ሊቲጌሽን ጉዳይ፤ በይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 972-3 እንደተጠቀሰው።

በተጨማሪ፣ "ፍርድ ቤቱ ፊት የቀረቡት ተወካዮችም ሆነ ያልቀረቡት ወገኖች የይገባኛል ጥያቄዎችና መከላከያዎች ከአንድ ድርጊት የመነጩና ዕኩያ አምሳያነት ባላቸው የሕግ ወይም የጳኝነት ንድፈ ሀሳቦች ላይ የተመሠረቱ ከሆኑ ሕጉ የሚጠይቀው መስፈርት እንደተሟላ አድርጎ መቁጠሩ ከሁሉም ይልቅ የተሻለ አማራጭ ነው" የሚል አስተያየት ይቀርባል::[67] መላው ቡድን ጉዳት የደረሰበት ከተሰነዘረ ከአንድ ድርጊት ወይም ድርጊቶች ሲሆን፣ ወይም ጥቃት የተፈጸመባቸው ጥቅሞች እንዳይደፈሩ ጥበቃ የሚያደርግላቸው የሕግ ወይም የርትዕ ድንጋጌ አንድ ዓይነት በሚሆንበት ጊዜ፣ የከፊሎቹ የቡድን አባላት ጥቅሞች የመላው የቡድን አባላት ጥቅሞች አምሳያ እንደሆኑ (አምሳልነት እንዳላቸው) ግምት ይወሰዳል::

ጥያቄው አስቸጋሪ ቢሆንም፣ የዘወትር አሠራራቸው ሲታይ ግን፣ ፍርድ ቤቶች ለዚሁ መስፈርት አንድም፣ አንዳችም ትኩረት አይሰጡትም አልያም ደግሞ ከውክልና ብቃት መሠረታዊ ደንብ ጋር ተዛምዶ ያለው የዚሁኑም ደንብ መሠረት የሚያጠናክር መጣኔ አድርገው ይመለከቱታል::[68] ከቶውንም፣ አንዳንድ ፍርድ ቤቶች የውክልና ብቃት ደንብ የሚጠይቀው መስፈርት የተሟላ ለመሆኑ እርግጠኞች ከሆኑ ከዚሁ ከደረሱበት መደምደሚያ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ አምሳልነት እንዲሟሉ የሚጠይቃቸውን መመዘኛዎች አዛንፎ እስከ መተርጎም የመሄድ ፈቃደኝነት አሳይተዋል::[69]

መ. <u>የውክልና ብቃት</u>:- ከአሁኑ በፊት፣ በ1966 ዓ.ም. በወጣው በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 23 ግልጽ ሆኖ ከመቀረጹ በፊት "ርቱዕ የቡድን ክሶችን" በሚመለከት ካልሆነ በቀር በሌሎቹ የቡድን ክሶች ላይ የሚሰጥ የፍርድ ውሳኔ የሚያስከትለው ውጤት አሻሚ እንደነበረ መግለጻችን ይታወሳል:: ከዚህ ዓመት ምኅረት በኋላ ግን፣ ከባሕርይ የተነሳ ልዩነት ሳይደረግ፣ ማንናቸውንም ዓይነት የቡድን ክስ አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ ስማቸው በክሱ ማኅደር ውስጥ በሰፈረው ተከራካሪ ወገኖች ላይ ሆነ ፍርድ ቤቱ ፊት ባልቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች ላይ በእኩል ተፈጻሚ ይሆናል:: የዚህም ውጤት፣ *በፍርድ ያለቀ የደቀቀ* (res judicata) የሚለው መሠረተ ሀሳብ በክሱ ውስጥ ተነስተው ውሳኔ ባገኙት ጭብጦች ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆን ከቡድኑ አባላት መካከል አንዳቸውም ክርክር ተደርጎባቸው ውሳኔ ያገኙትን ጭብጦች በሚመለከት አዲስ ክስ ሊመሠርት አለመቻሉ ነው::[70] ስለዚህም፣ የውክልና ብቃት ጥያቄ ከቀደምቶቹ የርትዕና ከተተኪዎቹ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓቶች ይልቅ በተሻሻለው ደንብ 23 ውስጥ የበለጠ ወሳኝነት ያለው ጥያቄ ነው ማለት ነው::

የተሻሻለው ደንብ 23፣ "ተወካዮቹ ተከራካሪ ወገኖች ፍትሐዊነትና ብቃት ባለው ሁኔታ የመላውን የቡድን አባለት ጥቅሞች በሚገባ ሊያስጠብቁ የሚችሉ" መሆናቸው ከተረጋገጠ "ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ ወይም ከፊሎቹ ወኪል በመሆን በሁሉም ስም ክስ ሊያቀርቡ ወይም ክስ ሊቀርብባቸው ይችላል" በማለት ይደነግጋል::[71] በአንድ በቀረበ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ፊት በግንባር የቀረበው ተከራካሪ ወገን ወይም የቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች ፍትሐዊ በሆነና ብቃት ባለው መልኩ የቡድኑን አባላት ጥቅም ሊያስከብሩ ይችላሉን የሚለው ጥያቄ እንደ ነገሩ ሁኔታ በእያንዳንዱ ጉዳይ በፍርድ

---

[67] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፦ የተጠቀሰው ዝራ፦ ገጽ 687፦ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 292::
[68] ዝኒ ከማሁ
[69] ይዜል፦ የተጠቀሰው ሥራ፦ ገጽ 967
[70] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፦ የተጠቀሰው ሥራ፦ ገጽ 687፦ አሜሪካን ሎው ኢንስቲቲዩት፦ የተጠቀሰው ሥራ፦ ክፍል 86፦ ገጽ 415::
[71] ብራውን ኤት. አል. የተጠቀሰው ሥራ፦ ገጽ 557::

ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት ጥያቄ ነው።[72] ሆኖም ግን ይህንኑ የውክልና ብቃት ጥያቄ በተገቢው መንገድ ለመወሰን ሕጉ እንዲሚሉ ለሚጠይቃቸው ሁለት መመዘኛዎች ፍርድ ቤቱ ተገቢውን አትኩሮት መስጠት አለበት። የመጀመሪያው መመዘኛ የሚጠይቀው ፍትሐዊ ውክልና መኖሩን ለማረጋገጥ ከቡድኑ አባላት መካከል በቁጥር በቂ የሆኑ ሰዎች ስማቸው በክሱ ማህደር ውስጥ ሰፍሮ በተካራካሪነት መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ነው።[73] በክሱ ማኅደር ውስጥ ስማቸው ሰፍሮ የቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች ቁጥርና የተወከሉት አባላት ቁጥር እንዴትና በምን ያህል መመጣጠን አለበት የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች የተለያየ መልስ ሰጥተውበታል።[74] በበርካታ አበዳሪዎች በዋስትና የተያዘ ንብረት ተሽጦ አበዳሪዎች ባላቸው የይገባኛል ጥያቄዎች መሠረት ዕዳቸው እንዲከፈላቸው በቀረበ አንድ ክስ ከአበዳሪዎቹ አንዱ በሁሉም ስም ክስ እንዲያቀርብ ሲፈቀድለት በአንጻሩ ደግሞ እያንዳንዳቸው የተወሰነ ገንዘብ በማዋጣት አንድ የልማት ድርጅት ካቋቋሙ ሰዎች መካከል ሶስቱ ያቀረቡት ክስ ሌሎቹን መዋጮ አድራጊዎች በሚገባ ሊወክሉ አይችሉም በሚል ምክንያት ውድቅ ሆኖአል።[75] ምንም እንኳን የተወካዮች አባላት ብዛት ከቁጥር አንጻር በቂ ሊሆን የሚገባው ቢሆንም ቁጥር ብቻውን የውክልና ብቃት መኖሩን እንደማያመለክት መገንዘቡ በጣም አስፈላጊ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ፍርድ ቤቱ ፊት የቀረቡት የቡድን አባላት ቁጥር በርከት ያለ መሆን በራሱ ፍትሐዊነትና ብቃት ያለው ውክልና መኖሩን የሚያሳይ ማረጋገጫ ተደርጎ አይወሰድም።[76] የውክልና ብቃት መኖር አለመኖር ሁኔታን በሚመዝንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በሚከተለው መሠረተ ሀሳብ ሊመራ ይገባል። "ጥቅሙ ጥቅማቸው፥ ጥቅማቸው ጥቅሙ ካልሆነ በቀር ከመካከላቸው አንዱ የቡድን ተወካይ በመሆን በመላ አባላቱ ስም ክስ እንዲያቀርብና እንዲከራከር ሊፈቀድለት አይገባም። የጥቅም ግጭት የውክልናን ባሕርይ ከሥር መሠረቱ የማፍረስ ጠባይ አለው።"[77] ይህን በተመለከተ፣ *በሐንሰበሪ እና በሊ* መካከል በቀረበው ጉዳይ ጀስቲስ ስቶን የሰጡት የሚከተለው አስተያየት በጣም ጠቃሚ ነው፦

> "በአንድ ክርክር ውስጥ የቀረቡ የቡድን አባላት ብቸኛና የጋራ ጥቅም አንድም የጋራ የሆነ መብትን ለማስከበር አልያም ግዴታቸውን እንዲወጡ የቀረበባቸውን ክስ ለማስተባበል ብቻ ከሆነ ከቡድኑ አባላት ከሌሎቹ ቀሪዎቹን በመወከል ሊከራከሩ ይችላሉ ማለት አንድ ነገር ነው። እንደ ምርጫቸው በጋራም ሆነ በተናጠል መብታቸውን ለማስከበር ወይም በተለዋጩ የቀረበባቸውን የመብት ጥያቄ ለማስተ ባበል በጋራም ሆነ በተናጠል ክስ ሊመሠርቱና ሊመሠረትባቸው የሚ ቻል ተከራካሪ ወገኖች በሙሉ እንደ አንድ ቡድን ስለሚቆጠሩ ከመካ ከላቸው የተውጣጡ የተወሰኑ አባላት በቀሪዎቹ አባላት ስም ለመከ

---

[72] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 558፥ ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 687፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 293።

[73] ብራውን ኤት. አል. የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 558፣ ሁዊተን፥ ፕሩለር ሊቲጌሽን፥ ገጽ 435።

[74] ለምሳሌ ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 426-7 ይመልከቱ።

[75] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 417፡

[76] ሙር፥ በብራውን ኤት. አል. የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 558 ላይ እንደተጠቀሰው።

[77] በክላርክና በቸዝ ማንሐታን ባንክ መካከል የነበረው ጉዳይ፥ በብራውን ኤት አል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 561።

> ራከር የውክልና ብቃት እንዳላቸው ይቆጠራል ማለት ደግሞ ጨርሶ የተለየ ሌላ ነገር ነው።"[78]

የውክልና ብቃት አወሳሰን ጥያቄ እያንዳንዱ ጉዳይ እየታየና እየተመዘነ መወሰን ያለበት ጥያቄ ነው። ተገቢ ውሳኔም ላይ ለመድረስ "ተወካዮቹ በአማካሪነትና በተሟጋችነት ያቆሟቸው የሕግ ባለሙያዎች ችሎታ፣ ታማኝነትንና ሐቀኝነትን የመሳሰሉ የተወካዮቹ ክትመቶች፣ ተወካዮቹ ከክሱ የሚያገኙት ወይም የሚያጡት የጥቅም መጠን፣ በተወካዮቹ አባላትና በሌሎቹ አባላት መካከል ያለው የጥቅም መጋጨት፥ ተጻራሪነትና ቁርኞ መጠን" ሊመዘኑ የሚገባቸው መጣኔዎች ናቸው።"[79] እዚህ ላይ መጨመር ያለበት ጉዳይ ቢኖር፣ ጥቅሞቻቸው ፍትሐዊና ብቃት ባለው ሁኔታ አለመጠበቁን ማረጋገጥ ከተቻለ፣ በፍርድ ያለቀ የደቀቀ የሚለው መሠረተ ሀሳብ ፍርድ ቤቱ ፊት ሳይቀርቡ በቀሩት ተከራካሪ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ነው።[80]ይህን የመሰሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፣ በውሳንያተ ሕግ አግባብ የሚለው መርህ እንዲሟሉ የሚጠይቃቸው ሁኔታዎች ስለሚጓደሉ የተሰጠው ውሳኔ ባልቀረቡት አባላት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባውም በማለት ለማጤየቅ በር ይከፍታል።[81]

## ሠ. <u>የቡድን ክሶች ስለሚመደቡባቸው ዘርፎችና ክስ መቅረቡን ስለማስታወቅ።-</u>

በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ በፌዴራል ደረጃ ፀንቶ ባለው አሠራር፣ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት አግባብነት ያለው በሶስት ዘርፍ ሊመደቡ ለሚችሉ የቡድን ክሶች ብቻ ነው።[82] በሌላ አነጋገር፣ በአንድ ክስ ውስጥ ቀደም ሲል አያሌነት፥ የጋራ ጥቅም፥ አምሳልነት፥ እና የውክልና ብቃት ብለን የሰየምናቸው ቅድመ ግዴታዎች ተሟልተው የሚገኙ ቢሆንም እንኳ ይኸው ክስ ከሶስቱ ዘርፎች በአንዱ ሥር የሚወድቅ ካልሆነ በቀር በቡድን ክስ ሥርዓት መሠረት እንዲቀርብ ፈቃድ ሊሰጠው አይችልም። ከዚህ በመቀጠል አንድ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ይሰጥ ዘንድ ሊሟሉ የሚገባቸውን እነዚህን ተጨማሪ መስተገብሮች አንድ ባንድ እንመለከታለን። የመጀመሪያው ዘርፍ ተፈጻሚ የሚሆነው ከሁለት ሁኔታዎች አንዱ መኖሩ ሲረጋገጥ ነው። ግለሰብ የቡድን አባላት በተናጠል ክስ ቢመሠርቱ ወይም ቢመሠረትባቸው የተለያዩ ውጤቶች የሚያስከትሉ ፍርዶች ሊሰጡ ስለሚችሉ ከዚህ የተነሳ በተከላካይነት የቆመው ሌላኛው ወገን እርስ በርሳቸው የማይጣጣሙና የሚጋጩ የተለያዩ አቋሞች እንዲይዝ የሚገደድበት ሁኔታ ያጋጥማል። አንደኛው ሁኔታ ያልነው ይህን የመሰለውን ነው። ስለዚህም የዚህኛው የሕግ ክፍል ዋና ዓላማ የቡድኑ ተቃዋሚ ሆኖ ለቀረበው ወገን ጥበቃ ለማድረግ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ የመንግሥት የግምጃ ቤት ሰነዶችን ሽያጭ አስመልክቶ የአንድ ቡድን ግለሰብ አባላት ከፊሎቹ ሽያጮቹ ፈራሽ እንዲሆኑላቸው፥ ከፊሎቹ ደግሞ የወለድ ክፍያዎች እንዲፈጽሙላቸው፥ ሌሎች ጥቂቶች ደግሞ በሰነዶቹ ሽያጭ ላይ ገደብ እንዲደረግ በመጠየቅ በማዘጋጃ ቤቱ ላይ ክስ ቢያቀርቡና ከነሱም መካከል የሰነዶቹ ሽያጭ ፈራሽ እንዲሆን የጠየቁት ከሳሾችና ወለድ እንዲከፈላቸው የጠየቁት ከሳሾች ቢፈረድላቸው፣ ተከሳሹ ማዘጋጃ ቤት በአንድ በኩል ለሽያጭ ያቀረባቸው ሰነዶች ዋጋ ሲያጡበት በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚሁ ላይ ወለድ እንዲከፍል

---

[78] በይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 987።

[79] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 687፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 293።

[80] በሀንስበሪና በሊ መካከል የነበረው ጉዳይ፥ በይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 486።

[81] ገዚ ከማሁ።

[82] <u>ፌደራል ሩል ኦፍ ሲቪል ፕሮሲጀር</u> ሩል 23(ቢ)።

ሲደረግ ለመፈጸም ግራ የሚያጋባ አቋም ላይ ይወድቃል።[83] አንዳንድ ጊዜም ደግሞ፤ ተናጠል የቡድን አባላት በሚያቀርቡት ወይም በሚቀርብባቸው ክስ ላይ የሚሰጥ ውሣኔ የእነሱን ብቻ ሳይሆን የሌሎቹንም አባላት ጥቅሞች በሚመለከት ጭምር አብሮ የመወሰን ጠባይ ያለው፤ ወይም ደግሞ ሌሎቹ አባላት ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ያላቸውን ችሎታ በእጅግ የሚያጠብ ወይም የሚያሰናክል፤ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ሁኔታ ያልነውም ይህን የመሰለውን ነው። እንደገናም ለምሳሌ ያህል፤ ከአንድ ኩባንያ ባአክሲዮኖች መካከል ጥቂቶቹ የትርፍ ክፍያ እንዲያደርግ በኩባንያው ላይ ክስ ቢመሠርቱ ረቱም ተረቱም የትርፍ ክፍያን በሚመለከት የሚሰጠው ፍርድ የሁሉንም ባለአክሲዮኖች ዕጣ ፈንታ ይወስናል።[84] ምክንያቱም ቢባል፤ በክፍያው ጥያቄ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ በፍርድ ያለቀ የደቀቀ ስለሚሆን ይህንኑ ጭብጥ አስመልክቶ አዲስ ክስ ማቅረብ የማይፈቀድ ስለሆነ ነው።

የቡድን ክሶች ሁለተኛው ዘርፍ ተፈጻሚ የሚሆነው፤ የአንድ ቡድን አባላትን መብቶች በተለየ ሁኔታ የሚያስጠብቁ ደንቦች በሚኖሩበት ጊዜ ተቃዋሚ ሆኖ የቀረበው ወገን እነዚሁኑ ደንቦች በመተላለፍ አንድ ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ወይም በደንቦቹ መሠረት እንዲፈጽም ሲጠየቅ እምቢተኛ ሲሆንና ከዚህም የተነሳ መላ አባላቱን የሚመለከት የእግድ ወይም የመብት ማረጋገጫ ውሣኔ ማሳለፍ አግባብ የሚሆንባቸው የክስ ዓይነቶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ነው። በዚህ ምድብ ሥር ለሚወድቁ ክሶች ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው ተከሳሹ በአንድ ቡድን አባላት ላይ ሕገ ወጥ የሆነ የአድልዎ ተግባር ፈጽሟል በማለት የሚቀርብ ክስ ነው። እንደ እውነቱም ከሆነ፤ ደንብ ቁጥር 23 (ለ) (2) የተደነገገው ተከሳሹ በዘር ላይ የተመሠረተ አድልዎ ፈጽሟል በማለት በደሉ የተፈጸመበት ቡድን የሚያቀርበውን የሲቪል መብት ጥያቄዎች በዓይነ ሕሊና በመቅረጽ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም።[85] ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ክሳሹ የቡድን ክስ የሚመሠርተው፤ በመራጮች ምዝገባ ላይ ተገቢ ያልሆነ አሠራር እንዳይፈጸም፥ ትምህርት ቤቶች ለቡድኑ አባላት ጭምር ክፍት እንዲሆኑ፥ በሠራተኞች አቀጣጠር ሥርዓት ላይ ለውጥ እንዲደረግ፥ ወዘተ፥ በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ተከሳሹ አካል ወይም ግለሰብ እርምጃ እንዲወስድ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ነው። እንዲሁም፤ ማኅበራዊ ጠባይ ያላቸውን የልጆች፥ የሴቶች፥ የአቅመ ደካሞችና የአረጋውያንን መብት ለማስከበር በስማቸው የቡድን ክስ ማቅረብ ይቻላል። በደል ተፈጽሞባቸው እያለ፤ "በተናጠል ክስ ለማቅረብ የገንዘብና ተከታትሎ የማስፈጸም አቅም የሌላቸው እጅግ በርካታ ዜጎች ሳይካሱ እንዳይቀሩ አለኝታና ተስፋ የሚሆናቸው" በዚህ በሁለተኛው ዘርፍ የተመለከተው የመደብ ክስ ዓይነት ነው።[86]

ሶስተኛው ዘርፍ የቡድን ክስ ተፈጻሚ የሚሆነው የቡድኑ አባላት ካሏቸው የተናጠል ጥያቄዎች ይልቅ የሚጋሯቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ገዝፈው የሚታዩና ከሌሎች የክስ አቀራረብ ዘዴዎችም ይልቅ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ክርክሩን ቀልጣፋና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለመቁረጥ የላቀ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን ነው።[87] ይህኛው ዓይነት የቡድን ክሶች ዘርፍ፤ አባላት የየግላቸው የሆኑ የተለያዩ ጥቅሞች ያሏቸው ቢሆንም የሚያስተባብሯቸው የተወሰኑ የጋራ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ካሉ ለመብቶቻቸው በጋራ እንዲቆሙ የሚያስችላቸው ነው። ስለዚህም፤ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ሲነጻጸር በእንደዚህ ዓይነቱ ክስ ውስጥ በቡድኑ አባላት መካከል "ያለው ትስስር የላላ

[83] ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 689 ይመልከቱ።

[84] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 690።

[85] ይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 968-9፤ ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 690-1፡

[86] አርተር አር. ሚለር፥ "ኦፍ ፍራንከንስታይን ሞንስተርስ ኤንድ ሻይኒንግ ናይትስ፥ ሚዝ፥ ሪያሊቲ ኤንድ ዘ ክላስ አክሽን ፕሮብሌም"፥ "ሀርቫርድ ሎው ሪቪው፡ ቅጽ 92(1979)፥ ገጽ 665፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3።

[87] በዚህ ጽሑፍ ከላይ ገጽ 13 ይመልከቱ።

ነው።" በቀድሞው ደንብ 23 ድንጋጌዎች ላይ "ኢርቱዕ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት የነበረውም ይህ በዚህ ዘርፍ ውስጥ የሚወድቀው የቡድን ክስ ዓይነት ነበር። ይህም ስያሜ ሊሰጠው የቻለው "ቡድኑ ሊያስፈጽመው የፈለገው ወይም በቡድኑ ላይ ለማስፈጸም የተፈለገው መብት በባሕርዩ የተለያየና እነዚህንም የተለያየ ባሕርይ ያላቸውን መብቶች በጋራ የሚነካ የሕግ ወይም የኩነትና የዳኝነት ጥያቄ" ይዘት ያለው በመሆኑ ነው።[88] በውሳንያተ ሕግ አግባብ የሚለውን መርህ አስመልክቶ ከረር ያለ ክርክር የሚያስነሳ በመሆኑም ከሌሎቹ የቡድን ክስ ዘርፎች ይልቅ የበለጠ አወዛጋቢ ለመሆን የበቃው ይኸኛው የቡድን ክስ ዘርፍ ነው። በዚህ ዘርፍ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚመደቡት፣ ከሳሾች ለደረሰባቸው ጉዳት የገንዘብ ካሣ እንዲከፈላቸው የሚያቀርቧቸው ክሶች ናቸው።[89]

በፍርድ ቤቶች ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች በመነሳት፣ በዚህ ዘርፍ ሥር የሚወድቁ ክሶች በሁለት ንዑስ ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ። የመጀመሪያዎቹ ንዑስ ክፍሎች አያሌ ሰዎች አነስተኛ የገንዘብ ካሣ እንዲከፈላቸው በመጠየቅ የሚያቀርቧቸውን የክስ ዓይነቶች የሚያቅፉ ናቸው። ይህን ዓይነቶቹን ክሶችም "የአጥቢያ ዳኛ ክሶች" ወይም ዳኛን በመዋጥ "የአጥቢያ ክሶች" ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። በተጨማሪም፣ ይህን የመሰሉ ክሶች በእንግሊዝኛው የሕግ ቅላጼ "ኢምፕራክቲካል፦ በት - ፎር - ሩል 23" በመባል የሚታወቁ ሲሆን በእኛም "ዕድሜ ለደንብ ቁጥር 23" እንደ ማለት ነው። ይህን ስያሜ ሊያገኙ የቻሉትም፣ የቡድኑ ተቃዋሚ ሆኖ የቆመው ወገን በቡድኑ አባላት ላይ ተመሳሳይ ጥቃት ቢፈጽምም ይኸው ጥቃት ያስከተለው ጉዳት በገንዘብ ሲተመን እጅግ አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ የቡድኑ አባላት እያንዳንዳቸው በተናጠል ክስ ቢያቀርቡ ርባና ቢስ ስለሚሆን ክስ የመቅረቡ ሁኔታ የማይመስል መሆኑን ለማመልከት ነው።[90] ስለዚህም፣ ይህን የመሰለ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ የቡድን ክስ ሥርዓት፣ ግለሰብ የቡድን አባላት ያሏቸውን የይገባኛል ጥያቄዎች በአንድነት በማሰባሰብ አንድን ግዙፍ የሆነ ኩባንያ ወይም የመንግሥት አካል በእኩልነት ደረጃ ለመቋቋም የሚችል አንድ ኃያል የኢኮኖሚ አሃድ ለመፍጠር ያስችላቸዋል።[91] የሶስተኛው ዘርፍ ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ፣ በቁጥር እጅግ ብዙኃን የሆኑ ሰዎች ከአይሮፕላን መከስከስ፥ በሆቴል ላይ በደረሰ የእሳት ቃጠሎ፥ ለአስቤስቶስ ትነት መጋለጥ፥ ወዘተ፥ በመሳሰሉት አደጋዎች ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት የሚያቀርቧቸውን "ከውል ውጭ በመነጨ ኃላፊነት ላይ የተመሠረቱ የብዙኃን ክሶችን" የሚያቅፍ ነው። ይህን በመሰሉ ጉዳዮች እያንዳንዱ ከሳሽ በተከሳሹ ላይ ራሱን የቻለ የሚያዋጣ ክስ ሊመሠርት ይችላል። ሆኖም ግን በተናጠል የሚቀርቡ ክሶች ከፍተኛ ወጭንና የጊዜ መስዋዕትነትን ሊጠይቁ ይችላሉ። ስለዚህ የቡድን ክስ ማቅረቡ የተሻለ አማራጭ ነው። ከዚህም በላይ ግን ይህን የመሰሉ ክሶች በአንድነት ተጠቃለው መታየታቸው ከከሳሾች ይልቅ ለተከሳሾች የጎላ ጠቀሜታ አለው።[92]

## 4. <u>ክስን ስለማስታወቅ</u>

የቡድን ክሶች ሶስተኛው ዘርፍ በዓይነቱ፣ ምንም እንኳ የሚያገናኟቸው የተወሰኑ የሕግና የኩነት ነገር የይግባኛል ጥያቄዎች ቢኖሯቸውም በመሠረቱ ግን ተናጠል የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎች ያሏቸው ባለጉዳዮች ስብስብ እንደመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ፊት ያልቀረቡት ልሕሳኑ ተከራካሪ ወገኖች "ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን በተሻለው ዘዴ በመጠቀም፣ ክስ መቅረቡን እንዲያውቁት ማስታወቂያ ሊደርሳቸው እንደሚገባ" ደንብ

---

[88] የፌዴራል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሩል 23 (1938 ዓ.ም.)፡
[89] ይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 969።
[90] "ትልልቅ የቡድን ክሶችን ስለማስተዳደር"፥ <u>ሀርቫርድ ሎው ሪቪው፥</u> ቅጽ 87(1973 ዓ.ም.) ገጽ 427።
[91] ዝኒ ከማሁ።

[92] ይዜል፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 969 ይመልከቱ።

ቁጥር 23 ይደነግጋል:: "ይኸውም ዘዴ፤ የተቻለውን ጥረት አድርጎ የቡድኑ አባላት ሊሆኑ የሚችሉትን ግለሰቦች ለይቶ ለማወቅ የሚቻል በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ በግል መጥሪያ እንዲደርሳቸው ማድረግንም እንደሚጨምር" በደንቡ ላይ ተመልክቷል:: ሕገ መንግሥቱ በሚጠይቀው ደረጃ በውሳንያተ ሕግ አግባብ የሚለው መርህ በሥራ ላይ ውኀል ሊባል የሚቻለውም ይህ መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነው:: ሊሰጣቸው የሚገባው ማስታወቂያ ምን ዓይነት ቅርጽ ሊኖረው ይገባል የሚለው ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ እያንዳንዱን ጉዳይ በመመርመር መልስ የሚሰጥበት ነው:: የቡድኑ አባላት ቁጥር በርካታ በሚሆንበት ጊዜ ማስታወቂያ የመስጠቱ ወጪ ከፍተኛ ስለሚሆን ይኸውም ከክስ ለመሸሽ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ሁኔታው የቡድን ክሶች የተቋቋሙበትን ዓላማ ሊያመክን ይችላል::[93] ይህ ደግሞ በተለይም ዕውነትነት የሚኖረው የቡድኑ አባላት የይገባኛል ጥያቄዎችና ከነሱም ተነጥለው የማይታዩት የተወካዮቹ የይገባኛል ጥያቄዎች የሚያስገኙት የገንዘብ ጥቅም በጣም አነስተኛ በሚሆንበት ጊዜ ነው:: ፍርድ ቤቱ፤ *በአይሰን* በአንድ ወገን *በካርሊሌ ኤንድ ጃክሊን* በሌላው ወገን በቀረበው ጉዳይ፤ ተዉካዩ ከሳሽ ለማስታወቂያ የወጣውን ወጭ እንዲሸፍንና የማስታወቂያ አሰጣጡም በውሳኜያተ ሕግ አግባብ ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ጋር በተቻለ መጠን እንዲጣጣም ተለይተው ሊታወቁ ለሚችሉት የቡድን አባላት በግል መጥሪያ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፤ በማለት የሰጠው ብይን ተቃውሞ ያስከተለው ከዚህ ከጠቀስነው ምክንያት የተነሳ ነው::[94] ማስታወቂያ አሰጣጥ የሚያስከትለውን ወጭ ለመቀነስ ይቻል ዘንድ አንድ አዘውትሮ የሚቀርብ አስተያየት አለ:: ይኸውም፤ "በአዲሱ ደንብ መሠረት በፍርድ ያለቀ የደቀቀ በሚለው መሠረተ ሀሳብ ተከሳሾችም ጭምር ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ <u>ብቁዐት</u> <u>ቀዳማይ</u> ያለው ክስ መሆኑን ማሳየት ከቻሉ የማስታወቂያው አሰጣጥ ላስከተለው ወጭ ተከሳሾችም የፊንታቸውን ክፍያ ሊፈጽሙ ይገባል" የሚል ነው::[95]

ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው ከቡድን ክስ ዘርፎች ውስጥ ሶስተኛውን ዘርፍ በሚመለከት ብቻ ነው:: ከአሁን በፊት እንደገለጽነው፤ ማስታወቂያ የመስጠቱ ሁኔታ ግዴታ ሆኖ ሊቀርብ የቻለው ከዚህ ዓይነቱ የቡድን ክስ የተለየ ባሕርይ የተነሳ ነው:: ይህም ባሕርዩ ተወካዮችንና ውክልናቸውን በሚመለከት

---

[93] ለምሳሌ ቴፐሊ ኤንድ ሁዊተን የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 694 ይመልከቱ፤ አሽተን ፈልፕ ጁኒየር፥ "ሲቪል ፕሮሲጀር፥ ፌዴራል ሩል 23(ለ)(2) "ኖቲስ ኢን ክላስ አክሽንስ ሙሌን ሪኮንሲደርድ"፥ <u>ቱሌን ሎው ሪቪው፥</u> ቅጽ 43(1969 ዓ.ም.) ገጽ 373፤ ማኔጂንግ ዘ ላርጅ ክላስ አክሽን" ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 86:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተጠቀሰው ጉዳይ ፍርድ ቤቱ እንዳለው፤ "የግል መጥሪያ እንዲልኩ በከሳሾች ላይ ግዴታ መጣል ደሀውን ጴጥሮስን ለመጥቀም ታስቦ የተቀየሰውን ዘዴ ሀብታሙን ጳውሎስን ለማገልገል እንደተሠራ አድርጎ ባሕርዩን መለወጥ ይሆናል::" ዝኒ አዲ ከማሁ::

[94] ፈልፕስ፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 375-6፥ "ማኔጅንግ ዘ ላርጅ ክላስ አክሽን"፥ ከላይ ግርጌ ማ:ቁ. 90፥ገጽ 433-4:: ፓሜራንዝ፥ ገጽ 433-41:: ፓሜራንዝ በዚህ ጽሑፉ በአይዘን ጉዳይ ፍ/ቤቱ በውሳኔው ያስቀመጠውን ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ ከተቀበልን አስቂኝ የሆነ ውጤት ላይ ሊጥለን እንደሚችል ይገልጻል:: ለዚህም አስተያየቱ ማስደገፊያ አድርጎ ያቀረበው የሚከተለውን ጉዳይ ነው:: በዚህ ጉዳይ ቁጥራቸው 4 ሚሊዮን የሚሆን ሻጮችና ገዢዎች በመተባበር ተከሳሾች የነፃ ገበያ ሕግጋትን በመጣስ ተገቢ ያልሆነ ንግድ ያካሂዳሉ በማለት ክስ ይመሠርቱባቸዋል:: ተከሳሾችም ማስታወቂያ የመስጠቱ ግዴታ ለክርክራቸው እንደሚጠቅማቸው ስለተረዱት መከላከያቸውን በዚሁ ላይ ይመሠርታሉ:: ስለዚህም፤ "የቡድኑ አባላት ሊሆኑ ከሚችሉት ሰዎች መካከል ቁጥራቸው 1 ሚሊዮን የሚሆኑትን በስም ሳይቀር ማንነታቸውን ለይተው ለማረጋገጥ እንደሚችሉና እነዚህንም አባላት በሙሉ ያለአንዳች ክፍያ ለማቅረብ ደስተኛ እንደሆኑ፤ በከሳሾችም በኩል የሚፈለግ ሌላ ነገር ሳይኖር ለ1,000,000ኑ አባላት መጥሪያውን በየአድራሻቸው በፖስታ ለመላክ የሚያስፈልገውን 2,000,000 ዶላር ወጪ መሸፈን ብቻ መሆኑን ለከሳሾች ጠበቃ ይገልጻሉ:: ይህም ብቻ አይደለም:: በማያያዝም፤ ሌሎችም 3 ሚሊዮን የቡድን አባላት እንዳሉና እነዚህኞቹን ግን አስፈላጊው ሁሉ ጥረት ቢደረግም ማንነታቸውን ለማረጋገጥ ስላልተቻለ ሊደርሳቸው የሚችለው በመላ አገሪቱ ሊሠራጩ በሚችሉ ጋዜጦች ላይ የሚወጣ ማስታወቂያ ብቻ ነው በማለት በተጨማሪ ይገልጻሉ::" ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 1263-64::

[95] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 265 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6::

በውሳንያተ ሕግ አግባብ ከሚለው መርህ ጋር በጥብቅ የተያያዙ በርካታ ጭብጦችን ያስነሳል። የማስታወቂያው ዓይነተኛ ዓላማም፤ በአንድ ቡድን ውስጥ ሊሰባሰቡ የሚችሉ ግለሰቦችን ጥቅማቸውን የሚነካ ክስ በመመሥረት ላይ መሆኑን፤ እንደ ፍላጎታቸውም በክሱ ውስጥ ሊገቡ ወይም ከክሱ ሊወጡ የሚችሉ መሆናቸውን በመግለጽ ጠቅላላ ሁኔታውን እንዲያውቁት ለማድረግ ነው። ይህ ማስታወቂያ ደርሷቸው በክሱ ውስጥ *"በፈቃደኛነት ካልገቡ"* ወይም ከክሱ *"በፈቃደኛነት ካልወጡ"* በተወካዮች አማካይነት የቀረበው ክስ እንዲቀጥል እንደተስማሙበት ይቆጠራል።[96] ይህ ግምት ስለሚወስድም ከክሱ እንዲወጡ ከጠየቁት አባላት በስተቀር ተጠቃሚ ሆኑ ተጎጂ በሌሎቹ ላይ ፍርዱ ተፈጻሚ ይሆናል።[97] የማስታወቂያ ጠቀሜታው ከቡድኑ አባላት መካከል በተናጠል ክስ ለማቅረብ የሚፈልጉ ካሉ በሩን ክፍት የሚያደርግ ከመሆኑ ላይ ነው። በልማድ ዘወትር እንደሚያጋጥመው ከሆነ፤ በተለይ የሚቀርበው የይገባኛል ጥያቄ የሚያስገኘው ጥቅም አነስተኛ በሚሆንበት ጊዜ ግለሰብ አባላት በተናጠል ክስ ከማቅረብ እንደሚቆጠቡ ነው። ፓሜራንትዝ የሚባለው ጸሐፊ እንደዘገበው ከሆነ፤ አንድ በቡድን ሊቀርብ የሚችል ክስ በሚያጋጥምበት ጊዜ ከአባላቱ መካከል በክሱ ውስጥ ላለመግባት የሚመርጡት በአኃዝ ከአንድ መቶኛ በታች የሚሆኑት ሲሆኑ ከነዚህም መካከል በግሉ ክስ ለማቅረብ የመረጠና የገፋበት አንድም አባል አልተገኘም።[98] ይህ የመሰሉ ሁኔታዎች ሲመዘኑም፤ ጥብቅ የሆነ የማስታወቂያ አሰጣጥ ሥርዓት ሊኖር ይገባል የሚል አቋም መያዝ፤ በመሠረቱ የፎርማሊቲ ጉዳይ ለሆነ አሠራር ከሚገባው በላይ እሴት መስጠትና ለዚህም ሲባል "የላቀ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ካላቸው የመብት ማስከበሪያ መፍትሔዎች መካከል ዐቢይ የሆነውን" የቡድን ክሶች አቀራረብ ሥርዓት እንደ ማፋለስ የሚቆጠር ነው።[99]

## II. በኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ የቡድን ክስ ያለው ሥፍራ

### 1. መግቢያ

በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ ላይ እንደተመለከተው፤ "በወኪል አማካይነት መሟገት" በሚል ርዕስ ሥር በመከተት የቡድን ክሶች ሥርዓት የኢትዮጵያ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንዱ ክፍል ሆኖ ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሠራበት ቆይቷል። እንደ ሌሎቹ የሥነ ሥርዓቱ ሕግ ድንጋጌዎችም ሁሉ በሕጉ ላይ ለሰፈሩት የቡድን ክስ ሥርዓት ድንጋጌዎች ሙብእ የሆናቸው የሕንዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ይመስላል።[100] ስለዚህም፤ የቡድን ክሶችን ሕጋዊ መሠረትና የአፈጻጸም አድማስ በመተርጎምና በመወሰን ረገድ የሕንድ ፍርድ ቤቶች ያካበቱት ልምድ፤ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38ትን ለመተርጎምና ስማስፈጸም ኃላፊነቱ ለወደቀባቸው ለኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም

---

[96] አሩል 23 (ሐ)(2)፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 37።

[97] ሁዊተን፥ "ሪፕረዘንታቲቭ ሱትስ"፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 422።

[98] ፓመራንትዝ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 1266።

[99] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 1265። እዚህ ላይ፤ በተለይ ደንብ ቁ. 23 ተሻሽሎ በወጣበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ተቃዋሚዎች የነበሩት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። አንዳንዶቹ "ሕግ ዕውቅና የቸረው መግረምት (ማስፈራሪያ)" በማለት ሲተቹት አንዳንዶቹ ደግሞ የደንቡ ዕውነተኞቹ ተጠቃሚዎችና እውነተኞቹ ተከራካሪ ወገኖች ሊባሉ የሚገባቸውም በደል የደረሰባቸው የቡድኑ አባላት ሳይሆኑ ጠበቆች ናቸው የሚል እምነት ነበራቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የቡድን ክሶችን ጨምሮ ሁሉም ትላልቅ ክሶች "ብሄሞቶች" ናቸው ብለው ያምኑ ነበር። እንዲሁም ሌሎች ደግሞ፤ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ከአጥቢያ ዳኛ ችሎትነት ለማዳን ይጠቅማል ተብሎ የተደረገው ለውጥ የተባለለትን ያህል የጎላ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ባለው ሥራት አልተካከለም የሚል አቋም ነበራቸው። አንዳንዶችም፤ የቡድን ክሶችን፤ ሙግት ውስጥ ለመግባት ሀሳቡም ፍላጎቱም የሌላቸውን ሰዎች ወደ ሙግት ለመገፋፋት የተፈጠሩ አድርገው ይመለከቷቸው ነበር። ለምሳሌም ያህል፤ ካፖሊ ኤንድ ኮንሶሉ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 233 ይመልከቱ።

[100] ሮበርት ኤ ሲድለር፥ <u>ኢትዮጵያን ሲቪል ፕሮሲጀር</u>፥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ጋር በመተባበር፥ አዲስ አበባ 1968 ዓ.ም.፥ ገጽ 5 ይመልከቱ።

ሆነ ይህንኑ ድንጋጌ ለመተንተንና ለማብራራት ፍላጎት ላላቸው ኢትዮጵያውያን የሕግ ጠቢባን ጠቃሚ ምንጮች በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ። በሌላ ጎኑም ደግሞ፣ ለፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን በአጠቃላይ ለአንቀጽ 38 ደግሞ በተለይ ምንጩ የሕንድ ሕግ የመሆኑ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕግ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓትና በአሜሪካ ዳብሮ በሥራ ላይ በዋለው የቡድን ክስ አሠራር ንድፈ ሀሳብ መካከል የግንኙነት ሰንሰለት ይፈጥራል።[101] በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38፣ በሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ትዕዛዝ 1 ደንብ ቁጥር 8 እና የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ደንብ ቁጥር 23 መካከል ያለው ይህም የግንኙነት ሰንሰለት፣ በሕንድና ብሎም በአሜሪካ የሰፈነውን አሠራር መዳልው ወይም መመዘኛ አድርገን በመጠቀም የአንቀጽ 38ትን ድንጋጌዎች ይዘትና የተፈጻሚነታቸውን አድማስ ለመገምገም የሚያስችለን ጽኑዕ መሠረትና አመክንዮ ይፈጥርልናል።

በዓለም ውስጥ ከአሜሪካ ፌዴራል ደንብ ቁጥር 23 ጋር ተመሳሳይ የሆነ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ያላት ብቸኛ አገር ሕንድ እንደሆነች ሁሉ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ውስጥ እንዲካተት መደረጉ ኢትዮጵያን የኮንቲኔንታል ሥርዓተ ሕግ ተከታይ ከሆኑት አገሮች መካከል የመጀመሪያዋ ያደርጋታል።[102] በተለይም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 37(2) (ለ) አማካይነት የቡድን ክሶችን ሥርዓት ፍትሕ አደባባይ ለመቅረብና በሕገ መንግሥቶች የተጠበቁትን መብቶች ለማስከበር ከሚያስችሉ የሥነ ሥርዓት ደንቦች አንዱ አድርጎ በመቁጠር የዕውቅና ደረጃውን ከፍ ስላደረገው ከላይ የሰነዘርነው አስተያየት ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል።[103] ምንም እንኳ የቡድን ክሶችን ወደ ሕገ መንግሥት ደረጃ ከፍ የማድረጉ ሁኔታ ብልህነት አጠያያቂ ቢሆንም፣ እኝህን የክስ ዓይነቶች የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም በውሳንያተ ሕግ አግባብ የሚለው መርህ በተለምዶ አሠራር ከሚጠይቀው ውጭ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉ የሥነ ሥርዓት ደንቦች አድርጎ ሕገ መንግሥቱ ራሱ ስላቀረባቸው ይኸው ሁኔታ የቡድን ክሶችን የተፈጻሚነት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ክርክር ቢቀርብ አሳማኝ መልስ በመስጠት ረገድ የፍርድ ቤቶቻችንን ሸክም በእርግጥ ያቃልላቸዋል።[104]

## 2. <u>የቡድን ክሶች በኢትዮጵያ ሕግ ያላቸው የተፈጻሚነት አድማስ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት "ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል" ማንኛውንም በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው በማለት ይደነግጋል።[105] ይሁን እንጂ ከአሁን በፊት እንደገለጽነው፣ የቡድን ክስ

---

[101] ካፓሊ ኤንድ ኮንሰሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 218።

[102] ዝኒ ከማሁ፥ ነገር ግን ከዚህ ጋር ተጻራሪ ለሆነ አቋም፥ ጀሮም ኤስ እስሎዋን፥ "ጌምስ ፍሬንች ፒፕል ፕሌይ ዊዝ ክላስ አክሽንስ ኦር ፍሬንች ጌምስ ዊዝ ክላስ"፥ <u>ቴምፕል ሎው ኳርተርሊ</u>፥ ቅጽ 45፥ ቁጥር 1(1971 ዓ.ም.) ገጽ 210-238፤ እንዲሁም፥ ካፖሊ እና ኮንሰሎ፥ ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 211 ይመልከቱ።

[103] የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 የህንድ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 አምሳያ ሲሆን በህንድ የሕግ ሳይንስ እንደ ሕገ መንግሥታዊ ዋስትና ተደርጎ ይታያል።

[104] ሴድለር የሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች እያሻሻሉ ተለዋዋጭ ከሆኑ ፍላጎቶችና ሁኔታዎች ጋር እያስማሙ እንዲሠሩባቸው ለነሱ ቢተው ይሻላል በማለት ይከራከራል። የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 4። እንደዚህ ያለው የማስማማት ዕድል በሕገ መንግሥት ደረጃ የተደነገጉ ደንቦችን በሚመለከት አስቸጋሪ ይሆናል፤ ምክንያቱም ሕገመንግሥት ማሻሻል ከባድም፥ ጊዜም የሚወስድ ስለሆነ ነው።

[105] የኢትዮጵያዊ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፥ ነጋሪት ጋዜጣ፥ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1(1995 ዓ.ም.) አንቀጽ 37(1)።

በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ከሕገ መንግሥቱ የቀደመ ታሪክ አለው:: ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ የቆየው የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38(1) እንደሚከተለው ይደነግጋል:-

> "ብዙ ሰዎች በአንድ ዓይነት ክስ የጥቅም ግንኙነት ሲኖራቸው ለየብቻ ወይም በኅብረት ሊከሱ ወይም ሊከሰሱ ይችላሉ:: ስለሆነም ስለጋራ ጥቅማቸው ለመከላከል በወኪልነት እንዲከሱ ወይም በተከሳሽነት እንዲከላከሉ ፍርድ ቤቱ ሊፈቅድላቸው ይችላል::"

እንግዲህ፣ በዚህ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ መሠረት የቡድን ክሶች የአፈጻጸም አድማስ ምን ይመስላል? ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(2) (ለ) ጋርስ እንዴት ይዛመዳል? ሕገ መንግሥቱ መተርጎም ያለበት በፍትሐ ብሔሩ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 ላይ የተደነገገውን በማገናዘብ ነው ወይስ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(2) (ለ) ከፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 የሰፋ ትርጉም አለው?

ለመግቢያ ያህል፣ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 ላይ ገና ከመጀመሪያው፣ በውስጡ የሰፈሩት ቃላት አንቀጹ ሩሕ እንዳይኖረውና እሴት እንዲያጣ አድርገውታል የሚል ትችት ለመሰንዘር ይቻላል:: እንደ እውነቱም ከሆነ ይዘቱ እጅግ ውሱን ከመሆኑ የተነሳ ሕግ አውጭዎቹ ሕጉን በሚያረቁበት ጊዜ ትክክለኛውን የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ለመዘርጋት አስበው ያደረጉት መሆኑ ያጠራጥራል:: ምናልባትም፣ እስካሁን ድረስ በዚህ ሕግ ዙሪያ የተወሰኑ ጉዳዮች ላለመኖራቸው አንዱ ጥሩ ምክንያት ሊሆን የሚችለው ይኸው ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል::[106] ከዚህ ለጥቆ በሚቀርቡት ክፍሎች እንደ ቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ድንጋጌነቱ በአንቀጽ 38 ላይ የሚታዩትን አንኳር አንኳር ሕፀፆች ባጭር ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን::

## 3. በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 ላይ የሚታዩ ሕፀፆች

### 3.1. አያሌነት

በሕጉ አንቀጽ 38 መሠረት የቡድን ክስ ሊቀርብ የሚችለው ብዙ ሰዎች በአንድ ዓይነት ክስ የጥቅም ግንኙነት ያላቸው ሲሆን ነው:: እዚህ ላይ ቁልፍ የሆነው ቃል "ብዙ" የሚለው ነው:: ይህን የመሰሉ አሻሚ ቃላት በሚያጋጥሙበት ጊዜም አዘውትሮ የሚነሳው ጥያቄ ከመካከላቸው የተወሰኑ ሰዎች በራሳቸው ስምና በሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በሚገኙ ሰዎች ስም ለመክሰስም ሆነ ለመከሰስ እንዲፈቀድላቸው ጥቅም ያላቸው የቡድኑ አባላት ብዛት ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚለው ነው::

ፕሮፌሰር ሴድለር እንደሚሉት ከሆነ "የኢትዮጵያ ሕግ አርቃቂዎች አያሌ የሚለውን ቃል በመሸሽ ብዙ በሚለው ቃል ተጠንቅቀው የተኩት የቡድኑ አባላት ቁጥር ከሁለት በላይ እስከሆነ ድረስ ከፍተኛ ሊሆን እንደማይገባው ሆን ብለው ለማመልከት ነው::"[107] ይህ ዓይነቱ አተረጓጎም ለቡድን ክስ ሥርዓት ከጽንሱ ጀምሮ እስካሁን እድገቱ ለሕልውናው መሠረት ለአሠራሩም ሕይወት የሆነውንና የሚሰጠውን መሠረታዊ ዓላማ የሚያፈርሰ አተረጓጎም ነው::

---

[106] በከፊል የፍርድ ቤቶች መዝገብ በሚገባ ተደራጅቶ ባለመያዙ፥ በከፊልና ይልቁንም ደግሞ ረጅም የዳኝነት ሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች እንደገለጹልኝ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 38 ላይ ተመሥርቶ የቀረበ ክስም ሆነ መከላከያ ስለሌለ የዚህ ጽሑፍ ፀሐፊ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የተወሰነ የቡድን ክስ ጉዳይ ለማግኘት ያደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል::

[107] ሴድለር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 63::

ካሁን ቀደም በዚህ ጽሑፍ ክፍል አንድ ላይ እንደተመለከተው፣ የቡድን ክስ ርትዕ የወለደው የክስ አቀራረብ ሥርዓት ነው። ዓላማውም ለአንድ ክስ መነሻ በሆነው ጉዳይ ላይ ጥቅም ያላቸው ሰዎች ቁጥር እጅግ ብዙ በመሆኑ የተለመዱትን መደበኛ የሥነ ሥርዓት ደንቦች ተከትሎ የጣምራ ክስ ማቅረብ በገቢር የማይሳካ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን ለማስቻል ነው። መደበኞቹ የሥነ ሥርዓት ደንቦች በይዘታቸው ግልጽና በተፈጻሚነታቸውም በሐውርታዊ ናቸው። የመከሰስ መብት በሕገ መንግሥታት እና በውሳንያተ ሕግ አግባብ በሚለው የሥነ ሕግ መርህ የተጠበቀ ውድ የሆነ ንብረት ወይም የነጻነት አዱኛ ነው። በውሳንያተ ሕግ አግባብ ሲባልም፣ አንድ ሰው መጥሪያ ሳይደርሰውና ቀርቦም ለመከራከር ዕድል ሳይሰጠው በሕጋዊ ንብረቱና መብቱም ላይ አንዳችም ውሳኔ ሊሰጥ እንደማይቻልና መብቱም ለአደጋ ሊጋለጥ የሚችለው ሕግ የሚጠይቀው ሥርዓት ተከብሮ ፍርድ ቤት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር የማሰማት ዕድል ከተሰጠው በኋላ ብቻ መሆኑን በአጽንኦት የሚያስገነዝብ ነው።

የቡድን ክስ ደግሞ፣ ቁጥራቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ሰዎች በራሳቸው ስምና በሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በሚገኙ ሰዎች ስም እንዲከሱ ወይም እንዲከሰሱ፤ ይህም በሚሆንበት ጊዜ በክሱ ላይ የሚሰጠው ፍርድ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በሚገኙት በሁሉም ሰዎች ላይ ጭምር ተፈጻሚ እንዲሆን የሚፈቅድ ሥነ ሥርዓት በመሆኑ እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውን ሕገ መንግሥታዊ ከለላ የሚሰጡትን ድንጋጌዎች የሚሽር ነው። የሚሽር እንደመሆኑም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ተከራካሪ ወገኖች ልሕሳን ተከራካሪ ወገኖች በመሆናቸው ለመከራከር ዕድል ሳይሰጣቸው የመከሰስም ሆነ መከላከያ የማቅረብ መብታቸውን ያጣሉ ማለት ነው። ከተለመደው አሠራር ውጭ የሆነውን ይህን ሥርዓት መከተል ያስፈለገውም በክሱ ጥቅም ያላቸውን ወገኖች በሙሉ ፍርድ ቤት ለማቅረብ በገቢር የማይቻል ስለሚሆን ነው። ስለዚህም፣ ፕሮፌሰር ሴድለር የቡድን ክሱ አባላት ቁጥር በርካታ መሆኑ አስፈላጊ አይደለም በማለት የሰጡትን አስተያየት እውነትነት ከተቀበልን በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ የተደነገገው የቡድን ክስ ሥርዓት ለቡድን ውክልና አስፈላጊነት መነሻ የሆኑትን ታሪካዊ ሁኔታዎች ያላገናዘበ ደንብ ነው የሚል ክርክር ማቅረብ ይቻላል። ይህንንም ያልንበት ምክንያት፤ ርትዕ የቡድን ክስ ሥርዓትን የፈለሰፈው <u>በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ አያሌ ሰዎችን በሙሉ ለማጣመር አዳጋች የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ</u> መደበኛውን የሥነ ሥርዓት ደንብ በመተካት እንዲያገለግል ለማድረግ መሆኑ አጽንኦት ሊሰጠው ስለሚገባ ነው።[108]

አንድ ጉዳይ ሁለት ወይም ሶስት ወይም ብዙ ሰዎችን ብቻ የሚመለከት ከሆነ እነዚህኑ ፍርድ ቤት ለማቅረብ አዳጋች እንደማይሆን ግልጽ ነው።::[109] ይህን የመሰሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙም ከውሳንያተ ሕግ አግባብ መርህ ውጭ ለመፈጸም የሚሰጥ ማናቸውም ምክንያት ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህም፤ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ የተመለከተው የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ይህን በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ሰዎች በሙሉ ፍርድ ቤት ለማቅረብ አዳጋች የመሆኑን ችግር የሚፈታ ካልሆነ ወይም እንዲፈታ ታስቦ የተደነገገ ካልሆነ ከዚህ ውጭ ሌላ ፋይዳ አለው ለማለት አይቻልም።

[108] ከላይ በዚህ ጽሑፍ ገጽ 3-6፤ እስቴፈን ሲ. ይዜል፥ <u>"ፍሮም ሚዲይቫል ሊቲጌሽን ቱ ሞደርን ክላስ አክሽን</u>"፥ ዬል ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፥ ኒው ሄቨን ኤንድ ለንደን (1987 ዓ.ም.) ገጽ 2 ይመልከቱ።
[109] "አዳጋችነት" impracticability የማይቻል መሆን ማለት ሳይሆን፥ የቡድኑን አባላት ሁሉ ለማጣመር የሚኖረው ችግርና አመቺ አለመሆን ማለት ነው። ማርሻል ቢ. ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 116።

የሕንዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የሚጠቀመው "አያሌ" በሚለው ቃል ነው። ምንም እንኳ "ብዙ" እና "አያሌ" በተሰኙት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት እምብዛም ግልጽ አይደለም የሚል ክርክር ሊቀርብ ቢችልም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ቃል የቁጥር ብዛትን እንደሚያመለክት የታወቀ ነው። "ከአያሌ" ሰዎችም ይልቅ "ብዙ" ሰዎችን ለይቶ ለማወቅና ማንነታቸውን ለማረጋገጥ ይቀላል። እዚህ ላይ ለማጉላት የተፈለገው ዋናው ነጥብ፡ የጋራ ጥቅም ያላቸውን ሁሉንም ሰዎች ፍርድ ቤት ለማቅረብ ያዳግታል ወይስ አያዳግትም የሚለው ጭብጥ ሰዎቹን ለይቶ ለማወቅና ማንነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ከቁጥራቸው በየጊዜው መጨመርና መቀነስ ጥያቄ ጋር በቅርብ የተያያዘ መሆኑን ነው። ይህን የመሰለውን በየጊዜው መጨመርና መቀነስ ጥያቄ ጋር በቅርብ የተያያዘ መሆኑን ነው። ይህን የመሰለውን በየጊዜው ቁጥሩ የሚለዋወጥና የአባላቱን ማንነት ለማረጋገጥ የማይቻል ቡድን በተሻለ ሊገልጽልን የሚችለውም ቃል "አያሌ" የሚለው ነው። በሕንድ አገር የዘወትር የዳኝነት አሠራርም "ይህ ደንብ (የቡድን ክስ) ተፈጻሚ እንዲሆን ተከራካሪዎቹ ወገኖች ተለይተው የታወቁና ማንነታቸው ሊረጋገጥ የሚችል መሆኑ አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ እንዲያውም የአባላቱ ቁጥር በየጊዜው የመዋዠቅ ጠባይ ያለው አካላትም ጭምር በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሊከሱና ለክሰሱ እንደሚችሉ በአሁኑ ወቅት ስምምነት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ነው።"[110]

ከአሁን በፊት እንደገለጽነው፡[111] ፌዴራል ደንብ ቁጥር 23 አያሌነትን የሚተረጉመው በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ሰዎች ማጣመሩ በገቢር የሚያዳግት ከመሆኑ አኳያ ነው። ይህም ቢሆን ግን አያሌነትን በአቅጩ ለመለካት የሚያገለግል አንድ ብቸኛ የሆነ ቀመር የሌለ መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል። የሕንድም ሆኑ የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ለመስጠትም ሆነ ለመከልከል የሚጠቀሙበት እስፍንት እንደቀረበው ጉዳይ የተለያየና ባመዛኙም በጉዳዩ የተለየ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ለምሳሌም ያህል፡ በሕንድ ሰላሣ ተከሳሾች ያሉበት ቡድን ደንቡ የሚጠይቀውን አያሌነት ያሟላል ተብሎ ሲወሰን በአሜሪካም አሥራ ስምንት አባላት ያሉት ቡድን በቂ ብዛት እንዳለው ተቆጥሯል። እነዚህን ጉዳዮች የጠቀስነው ከጉዳዮቹ ዓይነት የተነሳ ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ያላቸው የቡድን ክሶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለምሳሌነት ያህል እንጂ ዓይነተኛ ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉት የቡድን ክሶች የሚያቅፏቸው አባላት ቁጥር እጅግ ብዙ ነው። እንደገናም ለምሳሌ ያህል፡ በ1970ዎቹ ዓመታት በአሜሪካ 550 የታክሲ ኩባንያዎች፡ 1300 ታላላቅ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት፡ 10, 000 የናፍጣ ጅምላ አከፋፋዮች፡ 250,000 የልብ ሕመም ጠንቅ የሚያስከትል ምርት ተጠቃሚዎች፡ እና ከዚህም የበለጠ ቁጥር ያላቸው ቡድኖች የቡድን ክስ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸዋል።[112] ይህን ለመሰለውም ቁጥር የተሻለ ገላጭ የሚሆነው "ብዙ" ከሚለው ቃል ይልቅ "አያሌ" የሚለው መሆኑ እምብዛም የሚያከራክር አይመስለንም።

አያሌነት ከቡድን ክስ ባሕርይ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። የቡድን ክስን እሴት የሚያላብሰው ከሳሾችን ወይም ተከሳሾችን በአንድነት ለማጣመር አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ በተወሰኑ አባላት አማካይነት ክሱ በሁሉም ስም እንዲቀጥል ዕድል የሚሰጠው

---

[110] ሙላ፡ <u>ኮድ ኦፍ ሲቪል ፕሮሲጀር</u> (አዘጋጅ ፒ.ኤም ባክሺ)፡ ቦምቤይ፡ ኤን ኤም ትሪፓቲ ፕራይቬት ኩባንያ (1070 ዓ.ም.) ገጽ 422።

[111] ከላይ ገጽ 6-7።

[112] ከላይ ገጽ 8-9 ይመልከቱ፡ ሲ. ኤ. ራይት እንዳለው "በርካታ አባላት ያሉት ቡድን አስፈላጊ የሆነው የቡድን አባላት ፍርድ ቤት ቀርበው የመሰማት ዕድል ሳያገኙ መብታቸውን እንዳያጡ ለመጠበቅ ነው።" <u>ሎው ኦፍ ፌደራል ኮርትስ</u>፡ ሆርንቡክ ሲሪስ፡ እስቱደንት ኤዲሽን፡ ሴንት ፓል፡ ሚኒሶታ፡ ዌስት ፐብሊሺንግ ኩባንያ (1983 ዓ.ም.) ገጽ 473፡ በተጨማሪም፡ የቡድን ክስን ለመፍቀድ የቡድን አባላት ቁጥር በርካታ ከመሆኑ የመነጨ "የማጣመር ከባድ ችግር ወይም አስቸጋሪነት" መረጋገጥ አለበት። · ዝኒ ኢዲ ከማሁ።

ባሕርዩ ነው:: ለቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት ልደትና ለተፈጻሚነቱም መሠረት የሆነው ይህ በገቢር በሥራ ላይ ለማዋል አዳጋች መሆኑ የፈጠረለት ተፈላጊነት ወይም መፍቅድ ነው:: ዓላማውም ለዚሁ መፍቅድ እልባት ማስገኘት ነው::

በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ "ብዙ" የሚለው ቃል መስፈሩ የቡድን ክስ ይህ የተፈላጊነት ባሕርዩ አቅጣጫውን እንዲስት ያደርገዋል:: ይህም ቢሆን ግን የቡድን ክስ መታየት ያለበት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙትን ሁሉንም ከሳሾች ወይም ተከሳሾች ለማጣመር አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ፍትሕን ለማስገኘት የሚረዳ ልዩ መፍትሔ ተደርጎ እንጂ የመደበኛው የጣምራ ክስ ሥነ ሥርዓት ምትክ ሆኖ የሚያገለግል የሥነ ሥርዓት ደንብ ተደርጎ መቆጠር የለበትም:: በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ወይም ብዙ በሚሆንበት ጊዜ መደበኛው የጣምራ ክስ ሥነ ሥርዓት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል:: በተጨማሪም፣ ሕገ መንግሥቱ በአንድ ቡድን ውስጥ ሊታቀፉ ስለሚችሉት የአባላት መጠን ህዱእ መሆኑ ጥሩ አጋጣሚ ነው:: ይህም በመሆኑ ሕግ አውጭውም ሆነ ፍርድ ቤቶች አንቀጽ 38 ለትክክለኛው የቡድን ክስ ዓላማ እንዲያገለግል ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል::

## 3.2. <u>ጋርዮሽነት</u>

ጋርዮሽነት፣ ከአባላቱ አንዱ ወይም በቁጥር ከአንድ በላይ የሆኑት በራሳቸው ስምና በሌሎቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በሚገኙት አባላት ስም ለመክሰስና ለመከሰስ ይችሉ ዘንድ የቡድኑ አባላት ምን ያህል የጋራ ጥቅም ሊኖራቸው ይገባል ከሚለው ጥያቄ ጋር የተዛመደ ነው:: ይህ ጭብጥ ለብዙ ሙግቶች መነሻ የሆነና በፍርድ ቤቶችም መካከል የተለያዩ ውሳኔዎችን ያስከተለ ነው::[113] የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38[የእንግሊዝኛው ቅጂ] መሳ የቡድኑ አባላት *እዩይ* ጥቅም ሊኖራቸው እንደሚገባ ይደነግጋል:: ሆኖም ግን "እዩይ" የሚለው ቃል የቡድኑን አባላት በጋራ የሚያስተሳስራቸው ጥቅም ምን ያህል ሊሆን ይገባል ለሚለው ጥያቄ እምብዛም መልስ አያስገኝልንም:: ፕሮፌሰር ሴድለር ይህንኑ አስመልክተው ስለ አንቀጽ 38 ሲያብራሩ፣ "የውክልና ክስ ይፈቀድ ዘንድ የተከራካሪዎቹ ወገኖች ጥቅሞች *ሰሩይ* ሊሆኑ እንደሚገባ" ይገልጻሉ::[114] (ሰረዝ የተጨመረ):: በማያያዝም "በወኪል አማካይነት የሚቀርብ ክስ የታቀደው *በኩልኼያቸው እዩይ* የሆኑ ጥቅሞች ያሏቸውን ሰዎች ከመካከላቸው ባንዱ እንዲወከሉ ለማስቻል ነው" በማለት ለአስተያየታቸው አጽንኦት ይሰጡታል::[115] (ስርዝ የተጨመረ)::

የህንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግም የሚጠቀመው በአንድ ዓይነት ቃል ነው:: በሕንድ የሰፈነውን አሠራር በተመለከተም ተደጋግሞ የሚሰማው፣ "ቃሉ ከአንድ ድርጊት የመነጨ የሚል አንድምታ እንደሌለው ግንዛቤ ያገኘ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪዎቹ ወገኖች እያንዳንዳቸው ከክሱ የሚያገኙት ጥቅም እዩይ ሊሆን ይገባል" የሚለው አስተያየት ነው::[116] ፕሮፌሰር ሴድለር ያቀረቡት መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የበቁትም በሕንዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ የሠፈረውን "እዩይ ጥቅም" የሚለውን አባባል ግልጽ ትርጉም መነሻ በማድረግ ይመስላል:: ሆኖም ግን፣ የሕንዱን ሕግ ቀረብ ብለን ከተመለከትነው የጥቅሞች ዕሪና የጋርዮሽ መሠረተ ሀሳብ አንዱ ገጽታ

---

[113] ከላይ ገጽ 8-9 ይመልከቱ::

[114] ሴድለር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 64::

[115] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 65::

[116] ሙላ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 422-3::

መሆኑንና ተከራካሪዎቹንም ወገኖች በጋራ የሚያገናኟቸው የኩነትና የሕግ ጥያቄዎች እስካሉ ድረስ እያንዳንዳቸው የተለያዩ ጥቅሞች ቢኖሯቸውም በወኪል አማካይነት ክስ እንዳያቀርቡ ወይም እንዳይቀርብባቸው የመከልከል ጠባይ የሌላቸው መሆኑን ልንረዳ እንችላለን:: በሁለንተናው እዩይ የሆነ ጥቅም መኖርን እንደ ግዴታ ማስቀመጥ የሙግት መንተትንና ከዚህም አልፎ የፍትሕ መዛባትን ለመግታት ዓላማው አድርጎ የተነሳን የሥነ ሥርዓት ዘዴ ጠቀሜታ በእጅጉ መገደብ ይሆናል:: ለቡድን ክስ ታሪካዊ መነሻው መፍቅድነት ቢሆንም ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በከፊል፥ ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ ግቅ ሙሉ በሙሉ: ምቹነትና ጠቀሜታ ተጨማሪ ዐቢይ መሊሊቶቹ ሆነዋል:: የክሶች ብዛት የሚያስከትለውን ጫና ለመቋቋም ለፍርድ ቤቶችም ሆነ ለተከራካሪዎች ወገኖች የሚፈጥረው አመቺነት ከላይ ደጋግመን የጠቀስናቸው ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የቡድን ክስ መተኪያ የሌለው አማራጭ እንዲሆን አድርገውታል:: ሙሳ የተባለው ታዋቂ የሕግ ምሁር ስለሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ደንብ ቁጥር 8 ሲተች "ፍርድ ቤቶች፣ 'እዩይ ጥቅም' ማለት ሰሩይ ጥቅም ማለት አለመሆኑን፡ ተመሳሳይነት ኖሮአቸው በዓይነታቸው የተለያዩ ጥቅሞችንም እንደሚጨምር ወስነዋል" በማለት ገልጸአል:: [117] በሁለንተናው እዩይ የሆነ ጥቅም ያላቸው የቡድን አባላት የሚያጋጥሙበት ሁኔታ ፈጽሞ አይኖርም ባይባልም እጅግ ውሱን እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም::[118] ስለዚህ ለሕጉ ቀደም ሲል የሰጠነው ሰፋ ያለ ትርጉም ምክንያታዊነት ጭምር ያለው ነው ማለት ነው:: ሕግ ደግሞ እንደ መስቀል ወፍ ከስንት አንዴ ብቅ ስለሚሉ ሁኔታዎች ለመደንገግ ይከጅላል ብሎ ግምት መውሰድ ያስቸግራል:: አብዛኛውን ጊዜ፣ በሁለንተናው እዩይ የሆነ ጥቅም፥ ሰሩይ ጥቅም፡ እዩይ ጥቅም ወይም የጥቅም ኅብረት የተሰኙት ጥያቄዎች በአንድ ክስ ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉት የመብት ማረጋገጫ ፍርድ እንዲሰጥ በመጠየቅ በሚቀርቡ ክሶች ላይ ብቻ ነው:: ለምሳሌም፡ አንድ ሰው የአንድ መንደር መውጫ መግቢያ የሆነውን መንገድ ቢያጥር ቢዘጋ ከመንደር ነዎሪዎቹ መካከል አንዱ ከዚሁ ተግባሩ እንዲቆጠብ በራሱና በሌሎቹም መንደርተኞች ስም ክስ ሊያቀርብበት ይችላል:: እንዲሁም፡ አንድ ግብር ከፋይ፡ ማዘጋጃ ቤቱ የሰበሰበውን ግብር ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንዳይጠቀምበት እንዲታዘዝለት በራሱና በሌሎችም ግብር ከፋዮች ስም በማዘጋጃ ቤቱ ላይ ክስ ሊመሠርት ይችላል::

በሌላም ወገን፡ ሕገ መንግሥቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚጠቀምበት "እዩይ ጥቅም"[119] በሚለው ፈንታ "ተመሳሳይ ጥቅሞች"[120]በሚሉት ቃላት ስለሚጠቀም በቡድን አባላት ስም ክስ ስለሚቀርብበት ሁኔታ ሰፋ ያለ መሠረት ይጥላል:: "ተመሳሳይ ጥቅም" የተሰኙት ቃላት "እዩይ ጥቅም"[121] ከተሰኙት ቃላት የተለዩና ሰፋ ያለ ትርጉምም ያዘሉ የመሆናቸውን ያህል በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 የተጣለው ጠባብ የውክልና መሠረት ቀሪ ተደርጎ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(2) (ለ) ተተክቷል የሚል ግምት መውሰድ ይቻላል:: ይህም ስለተባለ ግን፣ ሕገ መንግሥቱ ሰፋ ያለ መሠረት የሚጥል ቢሆንም የቡድን አባላት በራሳቸውና በሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ በሚገኙ አባላት ስም ለመክሰስና ለመከሰስ እንዲችሉ ምን ያህል የጋራ

---

[117] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 423::

[118] ሙላ፡ የተጠቀሰው ሥራ፡ ገጽ 422-3፥ እነዚህ "ርቱዐን" የቡድን ክስ ተብለው ይታወቁ የነበሩት ናቸው፥ ሆኖም፡ "ርቱዐን" "ዝንቅ" እና "ኢርቱዐን" በሚባሉት የቡድን ክስ ዓይነቶች መካከል የነበረው ልዩነት እንዲቀር ከተደረገ ወዲህ የቡድን ክስ የተፈጻሚነት አድማስ እየሰፋ መጥቷል:: ጆሴፍ ጀ. ሲሞኦኔ፡ ፕሮሲጀራል ፕሮብሌምስ ኦፍ ክላስ ሱትስ"፥ ሚቺጋን ሎው ሪቪው፡ ቅጽ 60(1961-1962 ዓ.ም.)፡ ገጽ 925::

[119] የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(2)(ለ)፥ ከላይ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6::

[120] ዝኒ ከማሁ::

[121] በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን "የቃላት ፍቺ" ይመልከቱ::

ጥቅም ሊኖራቸው ይገባል ለሚለው ጥያቄ በመጠኑም እንኳ ግልጽ የሆነ መልስ እንደማይሰጥ መዘንጋት የለበትም።

ስለዚህም አንቀጽ 37(2) (1) ራሱም ቢሆን ለተለያዩ ትርጉሞች ክፍት የሆነ አንቀጽ ነው። ሆኖም፣ ሕገ መንግሥቱን በምንተረጉምበት ጊዜ፣ ምንም እንኳን በአንዳንድ ጉዳዮች የተከሳሹ ድርጊት በሁሉም የቡድን አባላት ላይ እዩይ ወይም ዕሩይ ጉዳት ሊያስከትል ቢችልም፣[122] በአብዛኞቹ ጉዳዮች ላይ ግን ይህ ሁኔታ እንደማያጋጥም መገንዘብ ይገባል። ለምሳሌም ያህል፤ "አንድ ንቱግ የፋብሪካ ምርት በበርካታ ሰዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ እንደሚያጋጥመው ሁሉ፤ በቡድኑ አባላትና በተከሳሹ መካከል ያለው ብቸኛ ትስስር ተከሳሹ ከፈጸመው ድርጊት የተነሳ ሁሉም በተከሳሹ ላይ የጋራ ቅሬታ ያላቸው መሆኑ ብቻ እንጂ[123] ከዚህ በተረፈ በእያንዳንዱ የቡድን አባል ላይ የደረሰው ጉዳት ከሌላው የተለየና የማይገናኝ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን፤ መላው የቡድን አባላት በጋራ ባላንጣቸው ላይ የሚያቀርቡት ክስ ለሁሉም አባላት የጋራ የሆኑ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ማስነሳቱ አይቀርም። አንድ ሰው በአንድ ኅብር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ላይ አንድ ድርጊት ፈጽሞ ከሆነና ድርጊቱም የፈነጠቃቸው የሕግና የኩነት ጭብጦች መላ የኅብሩን አባላት በእኩልነት የሚመለከቱ ከሆነ ግለሰብ አባላት ተናጠል የይገባኛል ጥያቄዎች ቢኖሯቸውም ኅብሩ ግን እንደ ኅብርነቱ ጥቅሙን የሚያስከብርበት የጋራ መድረክ እንዲከለከል የሚያደርገው ሥነ ሥርዓታዊ ምክንያት አይኖርም።[124] ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን *"ኤጀንት ኦሬንጅ"* በመባል የሚታወቀው ክስ ነው (1983)። ይህን የ"ኦሬንጅ ኤጀንት" ሰለባ በሆኑት በ2.4 ሚሊዮን ሰዎች ስም የቀረበውን ክስ የሰሙት የፌዴራሉ ዳኛ የቡድን ክስ እንዲቀርብ የተፈቀደበትን ምክንያት ሲያስረዱ "ወደሚቀጥለው ምዕተ ዓመት ሊሸጋገርና ተሸጋግሮም ምዕተ ዓመቱን ሊያገባድድ የሚችል አሰልቺ ድግግሞሽን" ለመከላከል የተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።[125] የአንድ ድርጊት ሰለባ በሆኑት በ2.4 ሚሊዮን ሰዎች ስም ክስ ቀረበ ሲባልም ሁሉም የተጎዱት በእኩል መጠን እንዲሁም ሁሉም የሚሹት ዳኝነት በሁለንተናው ዕሩይ ነበር ማለት አይደለም። በክሱ ውስጥ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ሊያሰጡ የሚችሉ በቂ የሆኑ የጋራ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ነበሩ ማለት ብቻ ነው። ፈቃድ ለመስጠት ተቀዳሚ መመዘኛዎች ተደርገው የተወሰዱትም የቡድን ክስ ያለው አመቺነትና የሚያስገኘው ጠቀሜታ ነበሩ። እዚህ ላይ በተጨማሪ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር፣ የድርጊቱን ሰለባዎች በአንድ ክስ ውስጥ ማጣመሩ ለተከሳሹ የበለጠ አመቺና ጠቃሚ መሆኑን ነው።፣ ይህን አስመልክቶ በአሁኑ ወቅት ተፈጻሚ የሚሆነው ደንብ *በቪክቶሪያን ኢንቬስተርስ እና በሪስፓንሲቭ ኤንቫየርመንት* መካከል በተነሳው ክስ ላይ በሚከተለው አኳኋን ተገልጿል፡-

> "በርካታ ሰዎች በአንድ ፕሮጀክት ወይም ኩባንያ ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የተደፋፈሩት በአንድ የሂሳብ ሪፖርት ላይ የቀረበውን ዘገባ ወይም ለሕዝብ ይፋ የተደረገ የሂሳብ መግለጫን መነሻ በማድረግ ሲሆንና ከዚሁም ሪፖርት ወይም መግለጫ የተነሳ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበትን ሀብት የሚመለከቱ የገንዘብ ሰነዶች የገበያ ዋጋ እድገት ያሳዩ ሲሆን ኢንቬስተሮቹን ግለሰቦች በጋራ የሚያስተሳስሯቸው እሙር የሕግና የኩነት ጭብጦች ካሉ

---

[122] እንደዚህ ያሉ ክሶች በ1983 ዓ.ም. የፌዴራል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ደንቦች "ርቱዐን" የቡድን ክሶች በመባል ይታወቁ የነበሩ ክሶች ናቸው። ከላይ ገጽ 5፤ እንዲሁም ሲምአኔ፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 118 ይመልከቱ። ይህን የመሰሉት ክሶች፤ የተለያዩ የተናጠል ጥቅሞች ያላቸው ሆኖ ሳለ ከዚሁ በተጓዳኝ የሚያስተሳስሯቸው እሙርነት ያላቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ያሏቸውን አባላት ለሚመለከቱ የቡድን ክሶች ጉዳይ መፍትሔ ሊያስገኙ ባለመቻላቸው ባሁኑ ጊዜ እንዲቀሩ ተደርጓል።

[123] ካፖሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 224።

[124] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 224-5፥ እስሎአን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 218።

[125] ካፖሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 225።

> እያንዳንዱን ኢንቬስተር በተለይ የሚመለከት የግል ጥያቄ ቢኖርም ይኸው ሁኔታ የቡድን ክስ እንዳይቀርብ ለማስከልከል አግባብነት አይኖረውም"[126]

ስለዚህም፣ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38(1) ድንጋጌዎች በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች በለሆሳስ የተዋጡ መሆናቸውን ግምት በመውሰድ፣ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት መሠረት የቡድን ክስ ማቅረብ እንዲፈቀድ አባላቱ ሊኖራቸው የሚገባው የጋራ ጥቅም ምን ያህል መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ እሙር የጋራ የሕግና የኩነት ጥያቄዎች የመኖር ሁኔታ በቂ ነው የሚል መልስ መስጠት እንችላለን:: በሁሉም አባላት ላይ በጋራ ጉዳት ካደረሰ ድርጊት የመነጩ የጋራ ጭብጦች መኖር በተወካዮቻቸው አማካይነት ክስ ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ በቡድኑ አባላት መካከል በቂ ትስስር ይፈጥራሉ:: ይህን በመሰሉ ጉዳዮች እያንዳንዱ የቡድን አባል በተናጠል ክስ ቢያቀርብ "በክስ አቤቱታዎቹ ላይ የሚሰፍሩት ሀሳቦች በይዘታቸው ባብዛኛው አንድ ዓይነት ወይም ዕሩይ መሆናቸው አይቀርም፤" ስለዚህም "እነዚህ የጋራ ጭብጦች በአንድነት ታይተው ቢወሰኑ የዳኝነት ቅልጥፍና እንዲሰፍን ይረዳል::"[127] ይህም ጠቀሜታ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሰዎች አያሌ በመሆናቸው የጣምራ ክስ ማቅረቡ ስኬት አልባ በሚሆንበት ጊዜ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ፍትሕ እንዳይጓደል ተተኪ ሆኖ በማገልገል ከሚሰጠው ጠቀሜታ በተጨማሪ መሆኑ አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል::[128] ስለዚህም፣ ወደፊት እንደምናየው፣ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት እንደ አሠራር ዘዴነቱ፣ ግለሰቦች ጥቅሞቻቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች በግንባር ወይም በመረጡት ወኪል አማካይነት ችሎት ቀርበው የመከራከርና ጉዳያቸውን የማስረዳት መብቶቻቸውን በሚመለከት ጥበቃ የሚያደርጉላቸውን የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎችና የውሳንያተ ሕግ አግባብ አንድምታን በማያናጋ አኳኋን ፍትሕን ለማስፈንና የአሠራር ምቹነትን ለመፍጠር ይረዳል::

## 3.3. ፈቃድ እንደ ቅድመ ግዴታ

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 መሠረት ቁጥራቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የቡድን አባላት በራሳቸውና በሌሎቹም አባላት ስም ሊከሱ ወይም ሊከሰሱ የሚችሉት ሁሉም የቡድን አባላት ይህን ዓይነቱ ክስ እንዲቀርብ የተስማሙ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካመነበት ብቻ ነው:: አንቀጹ ተፈጻሚ እንዲሆን የተፈለገው "ብዙ" ሰዎችን ባቀፈ ቡድን ላይ እንደመሆኑ የሁሉንም አድራሻ ለማወቅና ስምምነታቸውን ለማግኘት በእርግጥም አስቸጋሪ አይሆንም:: ስለዚህም፣ ከመካከላቸው ዋናው የክሱ አንቀሳቃሽ የሆነው አባል ወይም የሆኑት አባላት በቡድኑ ስም ክስ ከመመሥረታቸው በፊት የእያንዳንዱን አባል ስምምነት ማግኘት ይኖርባቸዋል:: ከመካከላቸው ስምምነቱን ያልሰጠ አባል ካለም ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ሆኖ የቀረበና ጉዳዩም በፍርድ የታየ ቡድን አባል ከመሆኑ የተነሳ ብቻ ከክሱ ውጤት የሚያገኘውም ሆነ የሚያጣው አንዳችም ጥቅም ወይም ግዴታ አይኖርም::

የቡድኑ ተወካይ ክሱን የመሠረተውና ያካሄደው በሌሎቹ የቡድን አባላት ስምምነት መሠረት በሚሆንበት ጊዜ በተወካዩና በሌሎቹ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት የሚመስለው በቡድንና - በተወካይ መካከል እንዳለ ግንኙነት ከመሆን ይልቅ

126 ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 17::

127 ካፓሲ ኤንድ ኮንሰሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 224-5::

128 ከዚህ በላይ ገጽ 2-3 ይመልከቱ:: በአሜሪካ የአሠራ ልማድ፣ ይህ ነጥብ፣ ከተናጠል ጥያቄዎች ይልቅ የጋራ ጥያቄዎች ግዝፈት ሊኖራቸው ይገባል ከሚለው ከደንብ ቁ. 23 (ለ) (3) መስተገብር ጋር አብሮ የሚታይ ነው:: ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 16 ይመልከቱ::

በጠበቃና - በደንበኛ መካከል እንዳለ ግንኙነት ነው:: ልዩነቱ፤ በፊተኛው ሁኔታ ተወካዩ ከሚወክላቸው አባላት ጋር የጋራ የሆኑ የይግባኝል ጥያቄዎችና መከላከያዎች ያሉት ከመሆኑ ላይ ብቻ ነው:: እንዲሁም የቡድኑ ተወካይ ከክሱ ውጤት የሚያገኘውም የሚያጣውም ጥቅም ያለው ሲሆን አንድ የሕግ ጠበቃ ግን ከሚከፈለው አበል ውጭ ሌላ ጥቅም የለውም:: ቢሆንም ግን፤ በሁለቱም ሁኔታዎች እንዲወከል የተፈለገው ሰው ስምምነት ወሳኝነት አለው:: እንዲሁም፤ በሁለቱም ሁኔታዎች ክሱ በግል የሚመለከታቸው ሰዎች በግንባር ባይቀርቡም ወኪል መርጠው በመሰየማቸው ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸውን የማሰማት መብታቸው እንደተጠበቀላቸው ይቆጠራል:: ይህን በመሰሉ ጉዳዮችም የልሕሳን አባላት ጥያቄ ሊነሳ የማይችል ከመሆኑም በላይ መላው የቡድን አባላት መርጠው በሰየሟቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት በሙግቱ ተካፋይ ስለሆኑ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ፍርድ በሁሉም የቡድን አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል:: *በፍርድ ያለቀ የደቀቀ የሚለው መሠረተ ሀሳብ ተፈጻሚ የሚሆንበትም ምክንያት* ተስማምተው በሰየሟቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ጉዳዩን አስመልክቶ በክሱ ውስጥ ሊነሱ በሚችሉት የሕግና የኩነት ጭብጦች ላይ ክርክር ስለተደረገባቸው ነው:: ሆኖም፤ ውክልናው በወካዮቹ ስምምነት ላይ የተመሠረተ የቡድን ክስ እንደ ቡድን ክስ ሊቆጠር ይገባል ለማለት ያዳግታል:: ከአሁን ቀደም የቡድን ክስ ሥርዐት እንዴትና ለምን ሊጀመር እንደቻለ ጥንተ ነገሩን ለማመልከት ሞክረናል:: ከዚህም ታሪኩ፤ ለውክልና መኖር ስምምነት መኖር ያስፈልጋል የሚለው መሠረተ ሀሳብ በሥነ ሥርዓት ሕጎች አፈጻጸም ረገድ ያስከተለውን ችግር ለመፍታት የተፈለሰፈ ዘዴ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ከዚህን ጊዜም ጀምሮ የቡድን ክስ አሠራር ሥራ ላይ መዋል በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 ላይ ከተመለከተው ዓይነት "ትውክልት በስምምነት" ሥርዐት በሕንድና በአሜሪካ ሕግና ልማዳዊ አሠራር ወደ ተመለከተው ዓይነት "ትውክልት እንበለ ስምምነት" ሥርዐት የተደረገ ሽግግር ነው ማለት ይቻላል::[129] ከሌሎች ጋር በአንድነት በተከሳሹ ድርጊት ጉዳት የደረሰበት አንድ ሰው በራሱና በሌሎቹም ስም ክስ ለማቅረብ በሚፈልግበት ጊዜ አብረውት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በቁጥር አያሌ በመሆናቸው አብዛኛውን ጊዜ የእያንዳንዳቸውን ስምምነት ለማግኘት የማይቻለው ይሆናል:: እነዚህንም ሰዎች በአንድነት በማጣመር ክስ ለማቅረብ ቢሞከር ከአሁን በፊት እንደገለጽነው ሙከራው ስኬታማ ሊሆን አይችልም:: ከዚህም በላይ፤ እያንዳንዱ የቡድን አባል በተናጠል ክስ እንዳያቀርብም፤ አንደኛ፥ ከክሱ ውጤት ሊገኝ የሚችለው ካሣ የክሱን ወጪ ለመሸፈን እንኳን በቂ አይሆንም:: ሁለተኛም፥ ለሁሉም የቡድን አባላት የጋራ የሆኑትን የሕግና የኩነት ጭብጦች በተለያዩ የክስ መዝገቦች በተናጠል መዳኘት የአሠራር አመቺነት አይኖረውም::[130] ኤስ. ሲ. ያዜል የተባለው ፀሐፊ፤ ከአንድ ታላቅ መደብር (ሐኖት) የተበላሹ ዕቃዎችን ከገዙ በሺዎች ከሚቆጠሩ ሸማቾች መካከል አንዱ የሁሉንም ሸማቾች ስምምነት በማግኘት በራሱና በሌሎቹም ስም ክስ ለማቅረብ ቢሞክር ሊደርስበት የሚችለውን ፈተና እንደሚከተለው አድርጎ በጥሩ ሁኔታ አስቀምጦታል::

> "መጀመሪያ ነገር፤ አንድ ሸማች ከሱ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሌሎችም ሸማቾች መኖራቸውን የሚያውቅበት አንዳችም መንገድ አይኖርም:: ምናልባትም ደግሞ ተመሳሳይ ቅሬታ ሊኖራቸው የሚችል ሌሎችም ሸማቾች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል የሚል የመላ ምት ጥርጣሬ ቢያድርበትም እነዚሁኑ ሸማቾች አግኝቶ እውነቱን ለመረዳት ያለው ዕድል የመነመነ ነው:: እንደ ዕድል ሆኖ ቀንቶት ቢያገኛቸውም እንኳን ሁሉንም በቡድን ለማሰባሰብ፤ ክሱ የሚያስከትለውንም ወጪ በጋራ እንዲሸፍኑ ስምምነታቸውን ለማግኘት፤ ጉዳያቸውን በሚከታተልላቸው ጠበቃ አመራረጥ ላይም እንዲስማሙ ለማድረግና፥ የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመፈጸም ከፍተኛ ድካም የሚጠይቅ ነው:: ከዚህም በተጨ

[129] ከላይ ገጽ 2-3 ይመልከቱ፤ ለቡድን ክስ ውክልና የቡድን አባላት ፈቃድ የማያስፈልግ ስለመሆኑ ይዜል ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2፥ ገጽ 11-16 ይመልከተ::

[130] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28፥ እንዲሁም ሙላ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 421፥ ሲሞእኔ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ካፓሊ ኤንድ ኮንሰሉ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 224-5 ይመልከቱ::

> ማሪ እነዚህ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ሳይታለም የተፈታ ከመሆኑም በላይ ለድካም ማበረታቻ ሊሆን የሚችል ቆሉ የሌለው መሆኑ ችግሩን ተስፋ አስቆ ራጭ ያደርገዋል። በሌላ አነጋገር፤ ከክሱ የሚገኘው ጥቅም አነስተኛ መሆን፤ ግለሰብ የቡድን አባላት ሌሎቹን በማሰባሰብ በቡድን የማደራጀቱን ተግባር እንዲያከናውኑ የሚያበረታታ አይደለም።"[131]

ስለዚህም፤ እነዚህ ሁኔታዎች ሲጤኑ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ከተፈለገ የመላ አባላቱ ስምምነት ያስፈልጋል የሚለው መስተገብር የማይመስልና በገቢርም ሊሳካ የማይችል ነው። የሕንድ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ደንብ ቁጥር 8 የፍርድ ቤቱን ፈቃድ እንጂ የቡድን አባላቱን ስምምነት እንደ ግዴታ አድርጎ የማይቆጥረውም ከዚሁ ምክንያት የተነሳ ነው። በሌላ አነጋገር፤ ሕጉ የሚጠይቃቸው አያሌነት፥ ጋርዮሽነትና ማስታወቂያ መስጠት መስተገብራት ከተሟሉና ከፍርድ ቤቱም ፈቃድ ከተገኘ የሌሎቹ ስምምነት ሳያስፈልገው ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ በራሱና በሌሎቹም አባላት ስም በከፈተው ክስ ሊገፋበት ይችላል።[132] የአሜሪካ ፌዴራል ደንብ ቁጥር 23ትን በተመለከተም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ የሚሆነው አያሌነት፥ ጋርዮሽነት፥ አምሳልነት፥ እና የውክልና ብቃት የተሰኙት መስተገብሮች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው።[133] በተጨማሪም፤ ክሱ ከአሁን ቀደም ከተጠቀሱት የቡድን ክስ ዘርፎች ውስጥ በአንዱ ሥር እንደሚወድቅ ማሳየት ያስፈልጋል።[134] የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ለማግኘት የቡድን አባላቱ ስምምነት አግባብነት ያለው መስተገብር አይደለም።

ስለዚህም፤ የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 የሁሉም ቡድን አባላት ስምምነት እንደሚያስፈልግ ሲደነግግ ሊያስገኘው የፈለገውን ግብ በሕንዱ ደንብ ቁጥር 8 እና በፌዴራሉ ደንብ ቁጥር 23 ላይ የተደነገጉት የውክልና ብቃትና የማስታወቂያ መስጠት መሠረተ ሀሳቦች የማስገኘት ውጤት አላቸው ማለት ይቻላል። ከዚህም የተነሳ፤ ምንም እንኳ በእኛ ሕግ ላይ የአባላት ስምምነት እንደ መስተገብር ሆኖ የተወሰደ ቢሆንም ሌሎች መስተገብሮች ከተሟሉ ፍርድ ቤቱ ያለ እንዳች ማመንታት የአባላት ስምምነት መኖሩን ስለሚቀበለው የፍርድ ቤቱን ፈቃድ ማግኘት ሶስቱም የሕግ ሥርዓቶች የሚጋሩት ቅድመ ሁኔታ ነው ማለቱ ያስኬዳል።[135] በሌላ አነጋገር፤ የቡድን ክሱ ሊቀጥል የሚችለው ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ሲሰጥ በመሆኑ፤ ፍርድ ቤቱም ሕጉ የቡድኑ አባላት ስምምነት መኖር ያለበት መሆኑን ሲደነግግ ሊያስገኝ የፈለገው ግብ ስለውክልና ብቃትና ማስታወቂያ መስጠት ተፈጻሚ በሚሆኑት መሠረተ ሀሳቦች አማካይነት የተገኘ መሆኑን ካመነበት ፈቃድ ከመስጠት ወደኋላ ስለማይል በእኛም ሕግ ቢሆን የቡድን አባላት ስምምነት አስፈላጊ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረብ ይቻላል።

### 3.4. <u>ስለውክልና ብቃትና ማስታወቂያ ስለመስጠት</u>።

ከላይ በሰፈረው በዚህ ጽሑፍ ክፍል፤ የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 አያሌነት እና ጋርዮሽነት የተሰኙትን መስተገብራት በሚመለከት የተጠቀመባቸው ቃላት የቡድን ክስ አቀራረብ ሥነ ሥርዓትን መሠረታዊ ባሕርዩን ያሳጡት መሆኑን ተመልክተናል። እንዲሁም፤ በሕጋችን ላይ የሠፈረው የቡድን ክስ ለማቅረብ እንዲቻል የመላው ቡድን አባላት ስምምነት ያስፈልጋል የሚለው መሠረተ

---

[131] ይዜል፤ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2፤ ገጽ 10።

[132] ሙላ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 421፥ ሴድለር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 63።

[133] ሩል 23፥ <u>ፌዴራል ሩል ኦፍ ሲቪል ፕሮሲጀር</u>፥ ከላይ ግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 33፤ ይዜል ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108፥ ገጽ 15፥ ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ ገጽ 231።

[134] ከላይ ገጽ 13-15 ይመልከቱ።

[135] ሴድለር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 63።

ሀሳብም በየትም አገር ተመሳሳይ የማይገኝለት መስተገብር ከመሆኑም በላይ አላስፈላጊም እንደሆነ በተጨማሪ ተመልክተናል። ተመሳሳይ የሚይገኝለት መሆኑም የሌሎች አገሮችን ልምድ ለማገናዘብ ሙከራ ያልተደረገ መሆኑን የሚጠቁም ሲሆን ይህም ሁኔታ፤ በዚህ ፀሐፊ እምነት፤ በሕጉ ላይ ለሚታዩት ሕፀፆችና በሥራም ላይ ላለመዋሉ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል።

እንደ እውነቱም ከሆነ፤ በአገራችን እስካሁን ድረስ የቡድን ክስን የሚመለከቱ ክሶች ቀርበው የማያውቁበት ምክንያት ምን ይሆን የሚለውን ጥያቄ ጠይቀን መልሱን ብንሻ ሩቅ ሳንሄድ ምክንያቱ እነዚሁ ሕፀፆች መሆናቸውን በቀላሉ እንረዳለን። የሚከተለውን ጥያቄ እንጠይቅ። አንድ *ብዙ* ሰዎችን የሚያቅፍ ቡድን አባል የሆነ ግለሰብ በግሉ ወይም መርጦ በሾመው ወኪሉ አማካይነት ለራሱ በሚመቸው አኳኋን ክስ አቅርቦ መብቱን ለማስከበር ሲችል ለምን ብሎ ይህን መብቱን ለሌላ ለማያውቀው ወይም በአጋጣሚ ላወቀው የቡድን አባል ያስረክባል? ከልማድ ዘወትር አንጻር ሁኔታውን ስንመዝነው አንድ ለባዊ ግለሰብ ይህን የመሰለውን መሠረታዊ መብቱን የሚመለከት ተግባር ለሌላ ሰው አሳልፎ ይሰጣል ብሎ ለመገመት ያዳግታል። ከዚህም በላይ ደግሞ፤ የቡድን ክሱ በዓይነቱ ግምታቸው አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ያላቸውን "*ብዙ*" ሰዎች የሚያቅፍ ቡድን ከሆነ ለአባላቱ ተጨማሪ ጥቅም ሊያስገኝ ቀርቶ ክሱ የሚያስከትለውን ወጪ እንኳን ሊሸፍን መቻሉም ያጠራጥራል። በሌላ አነጋገር፤ በገንዘብ ተመን አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ያሏቸው "ብዙ" ሰዎች ሕያውነት ያለው አህድ ለመመሥረት ይቻላቸዋል ከማለት ይልቅ ባመዛኙ አይቻላቸውም ማለቱ የበለጠ ተአማኒነት አለው።

ስለሆነም፤ በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አስተያየት፤ አያሌነት እና ጋርዮሽነት የተሰኙት መስተገብሮች በሕንድና በአሜሪካ ሕጎች በተሰጣቸው ትርጉም መሠረትና በሚተገበሩትም መልክ ሕጋችን ሊስተካከል ይገባዋል። ከአሁን በፊት እንደተመለከትነውም፤ በእነዚህ ሁለቱ አገሮች በስማቸው የቡድን ክስ ይቀርብ ዘንድ የአባላቱን ፈቃድ ማግኘት በንድፈ ሀሳብ ደረጃ አግባብነት እንደሌለው መሠረተ ሀሳብ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በውጤትም ረገድ ቢሞከር እንኳ ሊሳካ የማይችል አሠራር ተደርጎ የሚቆጠር ነው። የቡድን ክሶች ሊቀርቡ የሚችሉትም በፍርድ ቤቱ ፈቃድ ስለሆነ የፈቃድ አሰጣጡ ሂደት የአባላት ስምምነት መሠረተ ሀሳብ ሊያስገኝ የፈለገውን ግብ በተመሳሳይ ሁኔታ ያስገኛል።

እነዚህ ከላይ የገለጽናቸው ፍሬ ነገሮች እውነትነት አላቸው ብለን ከተቀበልን የአባላትን ስምምነት እንደ መስተገብር አድርጎ የሚደነግገውን የሕጋችንን ክፍል ሊከተል የሚችል አንዳችም ችግር ሳይኖር በቀላሉ እንደሌለ አድርገን ከሕሊናችን ልናወጣው እንችላለን ማለት ነው። ፍርድ ቤቶቻችንም ቢሆኑ፤ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ሊሟሉ የሚገባቸው ሌሎቹ አገባሪዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ያላንዳች ችግር የልሕሳን አባላት ጥቅሞች በሚገባ እንዲጠበቁ ማድረግ ይችላሉ። ከዚህም የተነሳ የውክልና ብቃትና ለልሕሳኑ አባላት ማስታወቂያ መስጠት አስፈላጊነት የተሰኙት ሁለቱ መስተገብራት የበለጠ ጉልህ ሚና ስለሚኖራቸው ተጨማሪ ማብራራትን ይጠይቃሉ።

3.4.1. <u>የውክልና ብቃት</u>

ከአሁን በፊት እንደተመለከትነው፣[136] የውክልና ብቃት በሚል የሚጠራው መስተገብር የሚያተኩረው በአንድ የቡድን ክስ ውስጥ ልሕሳኑን አባላት የሚወክለው ሰው የሚወክላቸውን አባላት ጥቅሞች ፍትሐዊነትና ብቃት ባለው መንገድ ለማስከበር በበኩሉ ብቁ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ጥያቄ ላይ ነው። የፍትሐ ብሔር ሥነ

[136] ከላይ ገጽ 11-13 ይመልከቱ።

ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38(1) ይህ ሰው በዚህ ረገድ ያለበትን ኃላፊነት አስመልክቶ የሚገልጸው አንዳችም ነገር የለም።

በአንቀጽ 38 መሠረት ሁሉም የቡድን አባላት አንድ ዓይነት ጥቅም እንዲኖራቸው ከማስፈለጉ በተጨማሪ የቡድን ክስ እንዲቀርብ የሌሎቹ አባላት ስምምነት ስለሚያስፈልግ፣ አባላት ጥቅማችንን ያስከብርልናል ብለው ለማይተማመኑበት ሰው ወይም ሰዎች ስምምነታቸውን አይለግሱም የሚል ግምት መውሰድ ይቻላል። የሕንዳዱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ደንብ ቁጥር 8 ስንመለከት፣ ልሕሳን አባላትን የሚወክሉት ሰዎች ክሱን በትጋት መከታተላቸውን ለመቆጣጠር ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው ለፍርድ ቤቶች ሲሆን ተወካዩ ይህን ግዴታውን በሚገባ ያልተወጣ መሆኑን ካመኑበትም በሌላ አባል ወይም በሌሎች አባላት እንዲተካ ማድረግ ይችላሉ።

በአሜሪካ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ፣ የፌዴራሉ ደንብ ቁጥር 23 የውክልና ብቃትን የቡድን ክስ እንዲፈቀድ ሊሟሉ ከሚገባቸው አራቱ መስተገብራት አንዱ አድርጎ ያስቀምጠዋል። በአሜሪካ ሰፍኖ የሚገኘው እንመት ለውክልና ብቃት መሠረተ ሀሳብ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ከሁለት ምክንያቶች የተነሳ ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ልሕሳኑን የቡድን አባላት የሚወክለው ሰው ክሱን ለመምራትና ለመቆጣጠር ያልተገደበ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑ ነው። ይኸውም ሥልጣንና ኃላፊነት ምን እንደሚመስል አንድ የአሜሪካ ፍርድ ቤት በሚከተለው አኳኋን ገልጾታል።

> "ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በሚሰማበት ወቅት ከሳሾችን ወክሎ የቆመው ወገን ክሱን የሚከታተለውና በችሎትም የሚሟገተው በቅን ልቦና፥ በተመስጦና በበቂ ሙያዊ ክህሎት አለመሆኑን ተገንዝቦ ሌላ ትእዛዝ ካልሰጠ በቀር፣ አንድ ክስ አቅራቢ የክሱን ሂደት በመሰለው መንገድ ለመምራትና ለመቆጣጠር ከፍጹምነት የደረሰ ሥልጣን አለው። የከሳሾቹ ሁሉ ቀንጮ፥ የነገር አባቱ በዓለ ውዴቱ፥ አንድ ሰው ብቻ ነው። ክስ መሥራቾቹ መላው ከሳሾች ክሱን ከአመሠራረቱ እስከ ተፍጻሜቱ ለማብቃትና ከተረቱም ወጪና ኪሣራውን ለመሸፈን ኃላፊነቱን ወስደዋል። ሁኔታው ይህ በመሆኑም እያንዳንዱ ከሳሽ ያለቅንጅት በየፊናው የመሰለውን እርምጃ እንዲወስድና ተከሳሹም ያለበት ግዴታ ከምን እንደመነጨ አንዱ ከሌላው በተለየ ሀሳብ እየተመራ ክሱን እንዲመራ ሊፈቀድለት አይገባም። ይፈቀድለት ቢባልም በገሃዱ ዓለም ዕውን ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም። በብዙዎቹም ጠበብት ድጋፍ ያገኘው ደንብ ይህ ነው።"[137]

የቡድኑ ተወካይ ማወቅ ሲገባው ባለማወቅም ሆነ በመዘንጋት ቁልፍ ምስክሮች ቀርበው እንዲመሰክሩ አስፈላጊውን እርምጃ ሳይወስድ ሊቀር ይችላል ወይም አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ሳያቀርብ ሊቀር ይችላል። እንዲሁም፣ በቂ መከላከያ ባለመቅረቡ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በወቅቱ ጥያቄ ሳያቀርብ ሊቀር ይችላል ወይም ደግሞ በተገላቢጦሹ ለወከላቸው ከሳሾች ጠቃሚ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዩን በዕርቅ ለመጨረስ አስፈላጊውን እርምጃ ሳይወስድ ሊቀር ይችላል። እነዚህ ሁሉ የልሕሳን ከሳሾችን ዕጣ ፈንታ የሚወስኑ እርምጃዎች ናቸው። እንግዲህ፣ ከላይ እንደተመለከተው፣ በአሜሪካ ሕግና እንመት ለውክልና ብቃት ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ የተደረገበት የመጀመሪያው ምክንያት ይህን የመሰሉ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፣ ልሕሳኑ አባላት በቡድናቸው ተወካይ አማካይነት ጉዳያቸውን ለፍርድ ቤቱ እንዳሰሙ ስለሚቆጠር ተወካዩ ክርክር ያቀረበባቸውን የሕግና የኩነት ጭብጦች በሚመለከት ረገድ የሚሰጠው ውሳኔ በሁሉም አባላት ላይ ተፈጻሚ

[137] ስምኦኔ ኤ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ፥ 933።

መሆኑ ነው:: በሌላ አነጋገር መላው አባላት *በፍርድ ያለቀ የደቀቀ* ለሚለው መሠረተ ሀሳብ ተገዢ ይሆናሉ::

> "ክሱ ጉዳዩን በሚሰማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቡድን ክስ ሥርዓት እንዲቀርብ ከተፈቀደ በኋላ ከሥርው እስከ ውልብኙ ክርክር ተደርጎበት በፍርድ- ፍጻሜ ካገኘ፤ በክሱ ውስጥ መሳተፍ አለመሳተፋቸው ከቁጥር ሳይገባ ፍርዱ በሁሉም የቡድን አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል:: በቡድኑ ላይ ከተፈረደበትም ማንኛውም አባል መላ ክሱን በሚመለከትም ሆነ ከዝርዝር ጭብጦቹ አንዱን በሚመለከት ዳግም ሌላ ክስ ከማቅረብ ይታገዳል:: ቡድኑ ረቺ ከሆነ ደግሞ ተከሳሹ የተጣለበትን ግዴታ በሚመለከት የተሰጠው ፍርድ የሚፀናበት ሲሆን ልሖሳን አባላት ፍርድ ቤት መቅረብ የሚኖርባቸው በግል ለደረሰባቸው ጉዳት ይገባኛል የሚሉትን ካሣ ለማስረዳት ብቻ ነው::"[138]

ስለዚህም፤ ልሖሳኑ የቡድን አባላት ለተወካዩ የሚያስረክቡት በእግራቸው ተተክቶ ጉዳዩን የመምራት ሥልጣን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊያቀርቧቸው የሚችሏቸውን የይገባኛል ጥያቄዎች ወይም መከላከያዎች የማቅረብ መብታቸውን ጭምር ነው:: ስለሆነም፤ የቡድን ክስ ሊፈቀድ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን የውክልና ብቃት ንኡድ ግምት ሊሰጠው የሚገባ መሠረተ ሀሳብ ነው::

ይህን ካልን ዘንድ፤ የውክልና ብቃት የሚወሰነው እንዴት ነው፤ ማለትም ምንን ተመርኩዞ ነው? መጀመሪያ፤ የይገባኛል ጥያቄዎችን ወይም መከላከያዎችን በሚመለከት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙት ሰዎች መካከል አንዱ ካልሆነ በቀር በራሱና በሌሎቹም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ባሉ ሰዎች ስም ሊከስ ወይም ሊከሰስ ስለማይችል ተወካዩ የግድ ከቡድኑ አባላት አንዱ ሊሆን ይገባል:: ሁለተኛ፤ "የተወካዩ ጥቅሞች ከወካዮቹ ጥቅሞች ጋር እንደ እግር ሶስቱ ክፍሎች ሳይዛነፉ የተሳሰሩ ሊሆን ይገባል::"[139] በሌላ አነጋገር መጫሚያቸውን ቢጫማ የሚስማማው ሰው መሆን አለበት፡[140] እነዚህ መስተገብራት በአንድነት ሲጠቃለሉም <u>አምሳልነት</u> በመባል ይታወቃሉ:: መሠረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ በተወካዩ ጥቅምና በልሖሳኑ አባላት ጥቅም መካከል ተጻራሪነት ወይም ቅራኔ ከሌለ በቀርም አምሳልነት እንዳለ ይቆጠራል::[141] አምሳልነት መኖሩን ለመወሰን መሠረት ተደርጎ የሚወሰደውም ስማቸው በክሱ መዝገብ ውስጥ የሰፈረው አባላት ቁጥር ከመላው የቡድን አባላት ቁጥር ጋር ያለው ተመጣጣኝነት እንዲሁም በአባላት የይገባኛል ጥያቄዎች የገንዘብ መጠን መካከል ተመጣጣኝነት መኖር አለመሆኑን ከአሁን በፊት ተመልክተናል::[142] መላው የቡድን አባላት የደረሰባቸው ጉዳት ከአንድ ድርጊት የመነጨ ከሆነ ወይም ጥቃት የተሠነዘረባቸው ጥቅሞች እንዳይደፈሩ ጥበቃ የሚያደርግላቸው አንድ ዓይነት የሕግ ወይም የርትዕ ድንጋጌ ከሆነ በጥቅሞች መካከል አምሳልነት እንዳለ ግምት ይወሰዳል::[143] የጥቅም አምሳልነት፤ ወደ ውክልና ለሚወስደው መንገድ መግቢያ በር ነው:: ሆኖም ግን የውክልና ብቃትን ለመወሰን የሚያስችለን ብቸኛው ሁኔታ አይደለም:: እንዲያውም፤ የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ለጥቅም አምሳልነት ይሰጡት የነበረው

---

[138] ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 227::

[139] ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 18፤ በአሜሪካ አሠራር የተወካይ ጥቅም ከተወሰኑ የቡድን አባላት ጥቅም ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ከተወሰኑ ሌሎች አባላት ጥቅም ጋር የሚለያይ ከሆነ ቡድኑን በንዑስ ቡድኖች መከፋፈል ይቻላል፤ እንዲሁም ደግሞ "በአንጻራዊነት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የቡድን አባላት ጥቅም የትላልቅ ንዑስ ቡድኖች ጥቅም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል"፡- ዝኒ ከማሁ፥ በተጨማሪም ከላይ ገጽ 10-11 ይመልከቱ::

[140] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 18::

[141] ከላይ ገጽ 10-11 ይመልከቱ::

[142] ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 18፤ በተጨማሪም ከላይ ገጽ 11 ይመልከቱ::

[143] ከላይ ገጽ 11 ይመልከቱ::

የጎላ ሥፍራ በአሁኑ ወቅት እየቀነሰ መጥቷል:: ራሱን ችሎ እንደቆመ መስተገብር ሳይሆን የውክልና ብቃት መስተገብርን የሚያቅፍ የሚደግፍ መጣኔ አድርገው ነው የሚመለከቱት::[144]

ሁለተኛም፣ የተወካዩ ጥቅሞች ከልሕሳኑ የቡድን አባላት ጥቅሞች ጋር አምሳልነት ያላቸው የመሆኑ ሁኔታ አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ የውክልና ብቃት መኖሩን ለማረጋገጥ ብቻውን በቂ አይደለም:: ይህም የሆነበት ምክንያት የውክልና ብቃት መስተገብር፣ አንድ ፍርድ ቤት ያልቀረበ ግን የተሰጠው ፍርድ የሚፀናበት ተከራካሪ ወገን ጥቅሞች በበቂ ሁኔታ መወከል አለባቸው በሚለው *በውሳንያተ ሕግ አግባብ* መርህ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው:: ሆኖም፣ ተወካዩ አባል የልሕሳኑን አባላት ጥቅሞች ለማስከበር ብቃት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ በመብዝኀቱ (ባብላጫው) እንደቀረበው ጉዳይ ዝርዝር ሁኔታ እየታየ የሚወሰን የኩነት ጥያቄ እንጂ የሕግ ጥያቄ እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል::[145] ቢሆንም፣ ቡድኑን የሚወክሉት የአባላት ቁጥርም ሆነ እያንዳንዳቸው ያላቸው የጥቅም እስፍንት ወሳኝነት እንደሌለው በተጨማሪ መገንዘብ ያሻል:: ይበልጡኑ "ተወካዩ የሚያሳየው ሐዋርያዊ ህግርት እና የተወካዩ ጠበቃ በክሱ ቢረታ ሊያስገኝለት የሚችለው ከፍተኛ አበል ያለው የማበረታታት ኃይል ቁልፍ ነገሮች ናቸው::"[146] ስለዚህም፣ የተወካዩ ባሕርይና የጠበቃው ችሎታና ልምድ የውክልና ብቃትን በመወሰን ረገድ ዐቢይ መመዘኛዎች ናቸው:: እነዚህም መስተገብራት በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 ውስጥ ሊካተቱ ወይም አንቀጹ እነዚህን እንደሚያካትት ተደርጎ ሊተረጎም ይገባል::

3.4.2. <u>ስለማስታወቂያ</u>

የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 38 የቡድን ክስ ይቀርብ ዘንድ የመላ አባላቱን ስምምነት መኖር ስለሚጠይቅ ክስ መቅረቡን እንዲያውቁት ለአባላቱ ማስታወቂያ መስጠትን እንደ አስፈላጊ ሁኔታ አይቆጥረውም:: በተጻራሪው፣ የሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ እንደሚከተለው ይደነግጋል:-

> "በዚህ ደንብ በንዑስ ቁጥር (1) መሠረት ፈቃድ ወይም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በከሳሹ ወጭ መጥሪያ በግል እንዲሰጣቸው በማድረግ ወይም ከስ ዎቹ ብዛት የተነሳ ወይም በሌላ ምክንያት የግል መጥሪያ እንዲደርሳቸው ለማ ድረግ በሕሊና ግምት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በመሰለው አኳ ኋን በሕዝብ ማስታወቂያ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ክስ መቅረቡን እንዲያውቁት ያደርጋል::"[147]

ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ከአሁን በፊት እንደተመለከትነው፣ የቡድኑ ቁጥር "ብዙ" ሳይሆን "አያሌ" በመሆኑና ይልቁንም ደግሞ የቡድኑ ተወካይ የመላ አባላቱ ስምምነት መኖሩን ማስረዳት ስለማያስፈልገው ነው:: እንደገናም ከአሁን በፊት እንደተመለከትነው፣ የቡድኑ አባላት ስምምነት እንደ መስተገብር ሆኖ ያልተቆጠረበትም ምክንያት በቁጥር አያሌ የሆኑ ሰዎችን ስምምነት ማግኘት ሊሳካ የማይችል ተግባር ስለሆነ ነው:: "ስለዚህም፣ አንድ ሰው ክስ መቅረቡን እንኳን በማያውቀው ጉዳይ ሊፈጠም የሚችልበት ሁኔታ እንዳያጋጥም ለመከላከል ፍርዱ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው ተከራካሪ ወገኖች ሁሉ ክስ መቅረቡን ማሳወቅ አስፈላጊ ነው::"[148]

---

[144] ከላይ ገጽ 11 ይመልከቱ::

[145] ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 19፥ እንዲሁም ከላይ ገጽ 11-13 ይመልከቱ::

[146] ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 19::

[147] በሙላ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 429-1 እንደገና ታትሞ የወጣ::

[148] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 425::

ስለማስታወቂያ የሚያወሳውን የአሜሪካ የፌዴራል ደንብ ቁጥር 23ትን ስንመለከት ደግሞ፣ ምንም እንኳ ይህ አንቀጽ በመሠረቱ ተፈጻሚ የሚሆነው የጉዳት ካሣን በሚመለከቱ የቡድን ክሶች ላይ ብቻ ቢሆንም ብዙዎች ጠበብት በሌሎችም የቡድን ክሶች ላይ ጭምር ተፈጻሚ ሊሆን እንደሚገባ ምክር ይለግሳሉ።[149]

እዚህም ላይ የማስታወቂያው ወጭ የማይሞከር ሊሆን ከመቻሉ የተነሳ የቡድን ክሱን ዋጋ ቢስ ወደሆነ ደረጃ ሊያደርሰው እንደሚችል መዘንጋት የለበትም። ስለማስታወቂያ አሰጣጥ በሕንድ ደንብ ቁጥር 8 እና በፌዴራሉ ደንብ 23፣ ላይ የሠፈሩትን ጥብቅ ድንጋጌዎች ስናጤን ደግሞ ይህን አባባል የበለጠ እውን ያደርጉታል። በደንብ ቁጥር 8 መሠረት መደበኛው የማስታወቂያ አሰጣጥ ዘዴ የግል መጥሪያ ነው። ከሳሹ በሁለተኛው ዓይነት የማስታወቂያ አሰጣጥ ዘዴ፣ ማለትም ለሕዝብ ይፋ በሚደረግ ማስታወቂያ፣ ሊጠቀም የሚችለው በግል መጥሪያ መስጠቱ በሕሊና ግምት የማይሳካ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው። እኛን በመሰሉ አገሮች ይህን ዓይነቶቹ የማስታወቂያ አሰጣጥ ዘዴዎች ከፍተኛ ወጪን ሊያስከትሉ ይችላሉ። በፌዴራሉ ደንብ ቁጥር 23 ደግሞ የማስታወቂያ አሰጣጡ ሥርዓት ከዚህም የጠበቀ ነው።[150]

እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነገር በእኛ ሕግ አንቀጽ 38 እና በሕንድ ሕግ ደንብ ቁጥር 8 መሠረት ማስታወቂያ የመስጠቱ ዓላማ ልሕሳኑ አባላት በክሱ ውስጥ "በፈቃደኛነት እንዲገቡ"፣ በአሜሪካ ሕግና እንመት መሠረት ደግሞ ከክሱ "በፈቃደኛነት እንዲወጡ"፣ በማስቻል ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑ ነው። በእኛም ሆነ በሕንድ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ከክሱ "በፈቃደኛነት ለመውጣት" የሚያስችሉ፣ ከክሱ በፈቃደኛነት መገለልም ምን ውጤት እንደሚያስከትል የሚገልጹ ድንጋጌዎች የሉም። ከክሱ "በፈቃደኛነት መውጣት" የሚለው አነጋገር በክሱ በግል ለመቀጠል ዕድል እንዳለ የሚያመለክት ዘይቤ ከመሆኑም ባሻገር በውሳንያተ ሕግ አግባብ መርህ መስፈርቶችም የሚደገፍ ነው። ሆኖም ግን የግል ክስ ከሚያስከትለው ከፍተኛ ወጪ የተነሳ ከክሱ "በፈቃደኛነት የወጡ" አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር በግላቸው ክስ የሚያቀርቡበት ሁኔታ እምብዛም አያጋጥምም።[151] ጉዳዩ አነስተኛ የገንዘብ መጠን ያላቸውን የይገባኛል ጥያቄዎች የሚመለከት ከሆነ ደግሞ "አልፎ አልፎ" ማለቱም ማጋነን ይሆናል። በሌላም በኩል፣ በክሱ ውስጥ "በፈቃደኛነት የመግባት" መብት የውሳንያተ ሕግ መርህ መሠረታዊ ገጽታ ስለሆነ ብርቱ ጥረት ታክሎበት ሊገኙ ለቻሉት የቡድን አባላት በሙሉ መጥሪያ እንዲደርሳቸው በማድረግ መብቱ እንዲከበር መጣር ያስፈልጋል።

በተጨማሪም፣ ከዚሁ ሳንወጣ፣ ለቡድን ክሱ አባላት ማስታወቂያ መስጠት ሊያስገኝ የተፈለገውን ግብ የውክልና ብቃት መስተገብር በመብዘኑቱ የሚያስገኝ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ለዚህም ምክንያቱ፣ የቡድኑ ተወካይ ጥቅሞች ከእነሱ ጥቅሞች ጋር እዩይ በሚሆኑበት ጊዜና ተወካዩም ለውክልና የሚያበቁት ክትመቶች ያሉት ከሆነ ቀረቡም አልቀረቡ የቡድኑ አባላት ጥቅሞች እንደሚጠበቁ የተረጋገጠ ስለሆነ ነው። ክትመቶች ያልናቸውም፣ ሐቀኝነት፥ ህግርት፥ ተገቢው ሙያና ልምድ ያለው ጠበቃ መርጦ የማቆም ችሎታ፥ እና የመሳሰሉት ባሕርያት ናቸው።[152] ፍርድ ቤቱም የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት እነዚህ መመዘኛዎች በሚገባ መረጋገጣቸውን ሊያምንበት ይገባል። በዚህ ፀሐፊ አስተያየት፣ ሕጋችንም ቢሆን ግልጽና አመርቂ መሆን

---

[149] ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሉ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 231፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 63።

[150] ከላይ ገጽ 15-16፣ በተለይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 91 እና 92 ይመልከቱ።
[151] ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሉ፥ ገጽ 230፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 63 ገጽ 232፥ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6፣ ከላይ በገጽ 15-16 ስለማስታወቂያ ከተደረገው ማብራሪያ በተጨማሪ ይመልከቱ።
[152] ለምሳሌ ይዜል፥ ፍሮም ሚዲየቫል ግሩፕ ሊቲጌሽን ቱ ዘ ሞደርን ክላስ አክሽን፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108 ገጽ 15 ይመልከቱ።

ያለበት በዚህ ነጥብ ላይ ነው:: በአገራችን፤ የሥነ ሥርዓት ሕጉ የሚጠይቃቸውን የመጥሪያ አሰጣጥ ዘዴዎች በቡድን ክሶች ላይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞከር ከሚያስከትለው ከፍተኛ ወጪ የተነሳ ክስ ከማቅረቡ ይልቅ መተው ሊመረጥ ይችላል:: ይህ ማለት ግን ማስታወቂያ መስጠት ጨርሶ አያስፈልግም ማለት አይደለም:: ለጅምር ያህል፤ ማለትም የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት፤ የጋዜጣ ማስታወቂያ ማውጣት በቂ ነው::[153] ከዚህ በኋላ፤ የቡድኑ ተወካይ በክሱ በለስ ከቀናው የቡድኑ አባላት በነፍስ ወከፍ ቀርበው ይገባኛል የሚሉትን የጉዳት ካሣ ለመጠየቅና ለማግኘት ይችሉ ዘንድ የግል መጥሪያ እንዲደርሳቸው ለማድረግ፥ ወይም በተሻለ ሌላ አማራጭ ዘዴ ለመጠቀም ዐቅሙ ይኖረዋል:: ይህን ለማለት ነው::

## 3.5. <u>የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ለማግኘት ሊሟሉ ስለሚገባቸው "መስተገብራት"</u>

በዚህ ጽሑፍ ከ8 እስከ 15 ባሉት ገጾች እንደተመለከትነው፤[154] አንድ ክስ ያቡድን ክስ የሚል ስያሜ እንዲያገኝ ከአሁን በፊት የገለጽናቸውን አራቱን "ቅድመ-ግዴታዎች" ብቻ ማሟላቱ በቂ አይሆንም:: ሎሎችም ሊሟሉ የሚገባቸው ግዴታዎች አሉ:: እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ "መስተገብራት" በመባል የሚታወቁት ናቸው:: እነዚህም መስተገብራት ሊሟሉ የሚችሉት ክሱ ከአሁን በፊት ከተመለከትናቸው የቡድን ክሶች ከሚመደቡባቸው ከሶስቱ ዘርፎች ባንዱ ሥር ሊወድቅ የሚችል መሆኑን አሳማኝ በሆነ መልኩ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ሲቻል ብቻ ነው::

እነዚህ መስተገብራት በባሕርያቸው ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ እንዲገኝ የሚጣሉ ተጨማሪ ግዴታዎች በመሆናቸው የቡድን ክስ ዳኝነት ለማግኘት ሥነ ሥርዓታዊ መፍትሔ ሆኖ የሚያገለግልበትን ሁኔታ የሚያጠቡ ናቸው:: በፌዴራል ደንብ ቁጥር 23 ድንጋጌ ውስጥ እነዚህ መስተገብራት በግልጽ እንዲካተቱ አጥብቀው ይከራከሩ የነበሩት ማእምራን ይህን ያደረጉት በውሳንያተ ሕግ አግባብ የሚለው መርህ ሊጠብቃቸው የሚሻውን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ለማስከበር ካላቸው ጽኑ ፍላጎት ይመስላል:: በእርግጥም ደግሞ ይህ መርህ መሠረታዊ የፍትሕ ምርካብ እንደመሆኑ መጠን ከእርሱ የላቀ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ትሩፋት ለማስከበር ካልሆነ በቀር በሌላ ምክንያት ለድርድር የሚቀርብ እሴት መሆን የለበትም:: እንደ አጋጣሚም ቢባል፥ በእቅድም ቢባል፤ የቡድን ክስ ሥርዓትና የውሳንያተ ሕግ መርህ ዋስትናዎች ፍትሕን በማስገኘት ረገድ አንድ ዓይነት ዓላማ ስላላቸው እንደ ፈትልና እንደ ሰም፥ እንደ ፀምርና እንደ ቀለም ስምም ናቸው::

በአሜሪካ፤ ከሶስቱ ዘርፎች ባንዱ ሥር ሊወድቁ የማይችሉ የቡድን ክሶች ፍትሕን ሊያስገኙ እንደማይችሉና ይህን ዓይነቱ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜም ፍትሕን ለማስገኘት የተሻለው አማራጭ መደበኛው የክስ አቀራረብ ዘዴ እንደሆነ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ ዓመታት ተቆጥረዋል:: በሕንድ የሠፈነውን አሠራር ስንመለከት ደግሞ፤ የሕጉ ተቀዳሚ ትኩረት ያረፈው ክስ ለማቅረብ ሕጋዊ መብት ወይም አቋም የሚሰጡትን ደንቦች አፈጻጸም በማስፋት ያጡ የደኸዩ፥ ረዳት አጋር የሌላቸውን ዐቅመ ደካማ የኅብረተሰቡን ክፍሎች ሊወክሏቸው በሚችሉ ማኅበራዊ ቡድኖች አማካይነት ዳኝነት እንዲያገኙ በማስቻል ላይ ነው::[155] በውሳንያተ ሕግ አግባብ መርህ ዋስትና የተሰጣቸውን ግለሰባዊ መብቶች ከማስከበር ይልቅ፤ በደል የደረሰባቸውን፥ ሕግ ፊት ለመቅረብም ሌላው መንገድ ሁሉ የተዘጋባቸውን ደሀ ወገኖች መብት ማስከበር የበለጠ

---

[153] ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 232::

[154] ከላይ ገጽ 13-15 ይመልከቱ::

[155] ራጂንዳር ሳቻር፥ "ሶሻል አክሽን ሊቲጌሽን፥ አክቲቪስት ኤንድ ትራዲሽናሊስት ጃጅስ፥" <u>ዘ ሱፕሪም ኮርት ኬዝስ</u> ኢስተርን ቡክ ካምፓኒ፥ ኢንዲያ(1987 ዓ.ም.) ቅጽ 1፥ ገጽ 14-16::

ልዕልና የሚሰጠው ነው:: የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 ስለመስተገብራት አንጻችም የሚያወሳው ነገር ባለመኖሩ እንደ ሕንዱ ሕግ በኢትዮጵያም ሕግ መሠረት አንድ የቡድን ክስ በየትኛውም ዘርፍ መመደብ አለመመደቡ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት አይኖርም ማለት እንችላለን:: ከዚህም የተነሳ፤ በኢትዮጵያም ቢሆን ተቀዳሚ ትኩረት የተሰጠው ደሆችና ረዳት የሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕግ ፊት ቀርበው በደላቸውን ማሰማት እንዲችሉ አመቺ ሁኔታ የመፍጠሩ አስፈላጊነት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ብንደርስ ያስኬዳል:: ቢያንስ፥ ለጊዜውም ቢሆን ይህን መንገድ መከተሉ የተሻለ አማራጭ ነው::

ይህን ማለት ግን የቡድን ክስ መስተገብራትን የሚያቋቁማቸውን ነጥቦች የሕንድም ሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሳይፈሩ ሳይቸሩ በልበ ሙሉነት ወደ ጎን ገሸሽ ሊያደርጓቸው ይችላሉ ማለት አይደለም:: ለምሳሌም ያህል፤ የቡድኑ አባላት፣ በተናጠል ከሚያቀርቧቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ይልቅ በጋራ የሚያስተሳስሯቸው ጥያቄዎች ግዝፈት ከሌላቸው የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ መስጠቱ ፍትሐዊም ትክክልም አይሆንም::[156] በተናጠል የሚቀርቡት ጥያቄዎች በብዛትም ሆነ በውስብስብነት አመዝነው የሚገኙ ከሆነ የሚመረጠው እያንዳንዳቸው የግል ክስ እንዲያቀርቡ ማድረጉ ነው:: እንዲሁም፤ ሙግቱን ለመቋጨት የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ ከተናጠል ክሶች ይልቅ የቡድን ክስ ማቅረቡ የተሻለ ቅልጥፍና የሚያስገኝ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ካላመነበት በቀር የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ሊሰጥ አይገባውም:: ስለዚህም አንድ ፍርድ ቤት የቡድን ክስ ጥያቄ በሚቀርብለት ጊዜ ለመፍቀድም ሆነ ለመግል ሊመዝናቸው የሚገባው ይህን የመሰሉ መጣኔዎችን ነው::

በተመሳሳይ ሁኔታም፤ በተለይም በተግባር ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጥመው፤ "በተናጠል ክስ ማቅረቡ ተመሳሳይ የይገባኛል ጥያቄዎች ያሏቸውን የሌሎች ሰዎች መብት መሠረታዊ ይዘት ያለጥርጥር መለወጡ የማይቀር" መሆኑን አንድ ፍርድ ቤት ካመነበት የቡድን ክስ እንዲቀርብ ከመፍቀድ ሌላ የተሻለ አማራጭ አይኖረውም::[157] አያሌ ከሳሾች የሁላቸውንም ዕዳ ሊሸፍን በማይችል ንብረት ላይ የሚያቀርቡት የይገባኛል ጥያቄም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው::[158] ቀድሞ ያስፈረደ ከሳሽ በተፈረደለት ልክ ከላይ ከላዩ ቢወስድ ወደኋላ የቀሩት ባለመብቶች ባዶ እጃቸውን ሊቀሩ ይችላሉ:: እንደገናም በተመሳሳይ ሁኔታ፤ በተናጠል በሚቀርብ ክስ መነሻነት የሚሰጡ የተለያዩ ፍርዶች ባላንጣ ሆኖ የቀረበውን ወገን እርስ በርስ የሚቃረኑ የተለያዩ አቋሞች እንዲይዝ የሚያደርጉት በሚሆንበት ጊዜ የቡድን ክስ እንዲቀርብ መፍቀዱ እንዲሁ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው:: ይህ መስተገብር በግልጽ ተፈጻሚ የሚሆነው ደግሞ ባላንጣው ወገን የሁሉንም የቡድን አባላት መብት በእኩልነት መጠበቅ ማስጠበቅ ሲገባው ይህንኑ ሳያደርግ በሚቀርበት ጊዜ ነው::[159] በመጨረሻም፤ ከሳሾች ያቀረቧቸው ክሶች በዓይነታቸው የእግድ ወይም የመብት ማረጋገጫ ትእዛዞች እንዲሰጧቸው የሚጠይቁ በሚሆኑበት ጊዜ ክሶቹ በቡድን ክስ ሥርዓት እንዲመሩ ሊፈቀድ ይገባል:: ይህን የመሰሉ ሙግቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥሙት ተከሳሹ የፈጸመው ድርጊት በርከት ባሉ ሰዎች ላይ ጉዳት በማድረሱ አንድ ራሱን የቻለ የጥቃት ሰለባ ቡድን በሚፈጠርበት ጊዜ ሲሆን አዘውትረው ሥራ ላይ የሚውሉትም ብሔራዊ መብቶችን ለማስከበር በሚቀርቡ ክሶች ነው::

---

[156] ላንደርስና ሌሎች የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 560::

[157] ዝኒ ከማሁ፣ ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 20::

[158] ላንደርስና ሌሎች፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 558::

[159] ግሮስማን፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 20::

ስለዚህም፣ የቡድን ክስ እንዲፈቀድ ጥያቄዎች በሚቀርቡላቸው ጊዜ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶችም ቢሆኑ ማመዛዘን ያለባቸው ይህን የመሰሉትን ሁኔታዎች ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ከተፈለገ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያስፈልጋል ብሎ አፍን ሞልቶ ሐሳብ ለማቅረብ ያስቸግራል፡፡ ከአሁን በፊት የተመለከትናቸው አስፈላጊዎቹ ቅድመ ግዴታዎች ከተሟሉና ደህና ረዳት የሌላቸው ዐቅመ ደካሞች ሕግ ፊት ቀርበው ደረሰብን የሚሉትን በደል እንዲያሰሙ የተሻለ ዕድል የሚያስገኙ ከሆነ፣ በአንዱ ወይም በሌላው ዘርፍ ሊመደቡ መቻል አለመቻላቸው ልዩነት ሳያመጣ፣ ይህን የመሰለው ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሁሉ የቡድን ክስ እንዲቀርብ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡[160]

### 3.6. <u>የጉዳት ካሣ ክፍያ</u>

#### 3.6.1. <u>ወጪና ኪሣራን ስለመክፋፈል</u>

ከአሁን በፊት እንደተመለከትነው፣ የቡድን ክስ፣ የቡድኑ አባላት ተወካይ በራሱና በሌሎቹም በሚወክላቸው አባላት ስም የሚያቀርበው ክስ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ክስም በከሳሽነት የሚታወቀው ተወካዩ ሲሆን ሌሎቹ አባላት ከሳሽነታቸው በተወካዩ አማካይነት ብቻ ነው፡፡ የቡድኑም ተወካይ በራሱና በሌሎቹም አባላት ስም ክሱ የሚያስከትለውን አስፈላጊውን ሁሉ ክፍያ ለመፈጸምና የፍርድ ባለዕዳም ሆነ ባለገንዘብ ለመሆን፥ እንዲሁም ማናቸውንም አገልግሎት ነክ ወጪዎችን ለመፈጸም ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡ ሌሎቹ አባላት ቢያገኙም ቢያጡም የሚያገኙትና የሚያጡት ከቡድኑ ተወካይ ጋር የተካከለ የማይበላለጥ ነው፡፡

የቡድኑ ተወካይ ያቀረበው መከላከያ አጥጋቢ ባለመሆኑ ቡድኑ ኃላፊነት እንዳለበት ከተወሰነም በውጤቱ ተጎጂ የሚሆኑት መጥሪያ የደረሳቸው ስማቸው በክሱ መዝገብ ላይ የሠፈረው ተከሳሾች ብቻ ናቸው፡፡ በቡድኑ ላይ የሚጣል ፍርድ ቀርበው ባልተከራከሩት የቡድን አባላት ላይ የግል አላፊነትን ሊያስከትል አይችልም፡፡ ይህ በአመዛኙ ተቀባይነት ያገኘ ደንብ ነው፡፡ *በዋርሊና ኩባንያው እና በላንገር* መካከል በተነሳው ክርክር *ጆንሰን* የተባሉት ዳኛ እንደሚከተለው መወሰናቸው ይጠቀሳል፡-

> "አንድ ግለሰብ በሌላ አኳኋን ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ሳይደረግ በቡድን አባልነት ላይ ከተመሠረተ ውክልና በመነሳት ብቻ አንድ የፌዴራል ፍርድ ቤት በግለሰቡ ላይ ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ሊያስከትል የሚችል ፍርድ ሊፈረድበት ይችላል የሚል እምነት እስካሁን በማንም ሰው ላይ አድሮ አያውቅም፡፡"[161]

የዚህ ደንብ መሠረቱ፣ አንድ ሰው በሕግ አግባብ ፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩን የማሰማት ዕድል ሳይሰጠው ጥቅሞቹ ለአደጋ ሊጋለጡ አይችሉም የሚለው ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው፡፡[162] ስለዚህም፣ አንድ ሰው መጥሪያ ደርሶት እንዲቀርብ ካልተደረገ በስተቀር ባልተሳተፈበት ክስ የሚሰጠው ፍርድ አፈጻጸም የርሱን መብት በምንም መልኩ ሊጎዳ እንደማይችል እርግጠኛ መሆን ይችላል፡፡

ጥቂት ማሻሻያ የተደረገበት ቢሆንም በሕንድም ተፈጻሚ የሚሆነው ደንብ የዚህ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህንኑም ደንብ *ሙላ* የተባለው ጸሐፊ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡ "... አንድ ሰው ሌሎች ተከሳሾችን ወክሎ እንዲሟገት በሚፈቀድበት ጊዜ በክሱ ላይ

---

[160] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 19-20፡፡

[161] ሲምአኔ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 234፡፡

[162] ካፓሊ ኤንድ ኮንሰሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 234፡፡

የሚሰጠው ፍርድ በተወከሉት ሰዎች ንብረት ላይ ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን የተወከሉት ሰዎች ስማቸው በክሱ መዝገብ ላይ ያልሰፈረ ከሆነ ግን የግል ኃላፊነት የለባቸውም።"[163] ስለዚህም፣ በህንድ አንድ የቡድን አባል ፍርድ ቤት ያለመቅረቡ ፍርዱን በግል ንብረቱ ላይ ከመፈጸም አያግደውም። ይህም ማለት፣ ሳይቀርብ መቅረቱ የግል ኃላፊነት

ሊያስከትልበት የማይችል ከመሆኑ በስተቀር ሌሎች ንብረቶቹን በተመለከተ በሕገ መንግሥታዊ መብቱ ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ውጤት እንደሌለ ይቆጠራል።

አንድ የቡድን ተወካይ ባቀረበው ክስ ከረታ ሌሎቹ አባላት ያወጣውን ወጪ እንደየድርሻቸው የመተካት ግዴታ አለባቸው። ምንም እንኳ የቡድኑ ተወካይ እንደሌሎቹ አባላት በፍርዱ መሠረት የሚገባውን ካሣ የሚያገኝ ቢሆንም ለበለጠ ወጪ ተዳርጎ ሊሆን ይችላል። ለልዩ ልዩ ጉዳዮች በግሉ ከከፈለው ወጭ በተጨማሪ ሊከፍል የተስማማው የጠበቃ አበል የትየለሌ ሊሆን ይችላል። ፍጻሜው የሰመረ የቡድን ክስ አባላት ስላለባቸው ግዴታ *በትረስቲስ እና በግሪንፍ* (1881) መካከል በተነሳው ክርክር የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚከተለው ወስኗል፦

> "ክሱ የተከፈተው በአቤት ባዩ በራሱ ስም ብቻ ሳይሆን በሌሎችም እኩል ጥቅም ባላቸው የዕዳ ሰነድ ተጠቃሚዎች ስም ጭምር ከሆነና በአቤት ባዩም ላይ ከፍተኛ ወጪና ድካም ያስከተለበት ከሆነ፣ ሌሎችም የዕዳው ሰነድ ተጠቃሚዎች በስተኋላ መጥተው ያቀረበው ክስ ካስከተለው ጥቅም ተቋዳሽ ከሆኑ፣ ለዳኝነት የከፈለውን አነስተኛ ወጪ ብቻ እንደየድርሻቸው እንዲከፍሉት ወስኖ አቤት ባዩን ማስና በቱ በእጅጉ የሚከብድ ውሳኔ ነው። ይህንን ማድረጉም አቤት ባዩን መበደል ብቻ ሳይሆን ከጥቅሙ ለመካፈል መብት ላላቸውም ሌሎቹ ወገኖች የሚይገባቸውን ጥቅም መስጠት ነው።"[164]

ስለዚህም፣ አንድ ግለሰብ የቡድን አባል የሚፈለግበትን ድርሻ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ በቀር ከሚያስገኘው ውጤት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። የቡድን አባላት የሚጋሯቸው የሕግና የኩነት ጭብጦች ቢኖሩም የተለያዩ የይገባኛል ጥያቄዎች ሊኖሯቸውም ስለሚችሉ አብዛኛውን ጊዜ ወጪውን መከፋፈል ያለባቸው በይገባኛል ጥያቄዎቻቸው የገንዘብ መጠን ልክ ሊሆን ይገባል። ስለዚህ፣ ለጠበቆች የሚከፈለው አበል በፍርድ ቤቱ የሚወሰን ሆኖ በክሱ የተገኘው ጠቅላላ የጉዳት ካሣ በአንድ ቋት ከተካተተ በኋላ እያንዳንዱ አባል በተፈረደለት መጠን እንደየድርሻው ከቋቱ እየተቀነሰ ይከፈለዋል።[165] ለጠበቆች የሚከፈለው አበል ሲሰላም መታሰብ ያለበት ያበረከቱት አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ብዙውን ጊዜ የዳኝነቱንም ሆነ ሌሎቹን ወጪዎች ከኪሳቸው ስለሚሸፍኑና በክሱ ከተረቱም የሚደረግላቸው አንዳችም ክፍያ ስለማይኖር ለኪሣራ የተጋለጡ በመሆናቸው ይህም ከግምት ውስጥ መግባት አለበት።[166]

### 3.6.2. <u>የጉዳት ካሣ ልዩነቶች ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ (ምግብና)።</u>

በአሜሪካ በሰፈነው የቡድን ክስ አመራር ሥርዓት፣ ለእያንዳንዱ የቡድን አባል የሚገባው የካሣ መጠን አተማመን ላይ የሚከሰተው ልዩነት ክሱ በቡድን ክስ ሥርዓት

---

[163] ሙላ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 426-7።

[164] ሲምኦኔ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 951፣ እንደዚሁም ካፓሊ ኤንድ ኮንሶሎ፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 230 ይመልከቱ።

[165] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 229፥ ይዜል፥ <u>ሲቪል ፕሮሴጀር</u>፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፥ ገጽ 1001።

[166] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 229፥ ይመልከቱ፣ ይዜል፥ <u>ሲቪል ፕሮሲጀር</u>፥ ገጽ 1001።

ሊመራ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን መሠረት ሆነው ከሚያገለግሉት መጣኔዎች እንደ አንዱ የሚታይ ነው። በፌዴራል ድንብ ቁጥር 23 መሠረት ተከሳሹ የፈጸመው ድርጊት ወይም እዩይ ተከታታይ ድርጊቶች የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸው የቡድን አባላት በጋራ የሚያስተሳስሯቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች እስካሏቸው ድረስ በእያንዳንዳቸው ላይ የደረሰው ጉዳት በመጠን በእጅጉ የተለያየ ቢሆንም የቡድን ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ሁኔታ ስለተፈጠረ ከላይ የጠቀስነው ጭብጥ በአሁኑ ወቅት በቡድን ክሶች ላይ በተደጋጋሚ የሚነሳ ጭብጥ ለመሆን በቅቷል። ይህንንም ጭብጥ ለመፍታት ከሚሰጡት አስተያየቶች አንዱ፤ ተከሳሹ የፈጸመው ሕቅ ወጥ ድርጊት በግልጽ የሚታይ ከሆነ፤ በግለሰብ ቡድን አባላት ላይ የደረሰባቸውን የጉዳት ካሣ መጠን በመተመንና የሚገባቸውን ካሣ እንደ ድርሻቸው በማከፋፈል ረገድ በስተኋላ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች የቡድን ክስ እንዳይቀርብ ለመከልከል ምክንያት ሊሆኑ አይገባም የሚል ነው።[167] ተዘዋዋሪ የገንዘብ ሰነዶችን በሚመለከት በሚቀርቡ የቡድን ክሶች ይህ ደንብ ያስፈለገበት ምክንያት *በግራድ እና ሜምሬክስ ኩባንያ* (1973) መካከል በተነሳው ሙግት እንደሚከተለው ተገልጿል።

> "ኩባንያው ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳት የደረሰባቸው ባለአክሲዮኖች እንዲካሱ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት አያጠያይቅም። ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚገባውን የጉዳት ካሣ መተመኑ ለመግቦ ወይም ክሱን በሥራት ለማስኬድ አያመችም በሚል ምክንያት የቡድን ክስ እንዳይቀርብ መከልከሉ የአክሲዮን ኩባንያዎች አነስተኛ የማጭበርበር ተግባሮችን ከመፈጸም ይልቅ ከፍተኛ የማጭበርበር ተግባሮች መፈጸምን እንደተሻለ ምርጫ እንዲወስዱት ማበረታታት ይሆናል። ይህ ፍርድ ቤት ካሣውን የመተመኑ ሥራ ቀላል ይሆናል ብሎ ራሱን አያታልልም። ፍትሕ የተቻለው ሙከራ እንዲደረግ ያዛል ብሎ ግን ያምናል።"[168]

በግለሰብ የቡድን አባላት ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሣ መጠን ለመተመን የተቀየሱ በርካታ ዘዴዎች አሉ።[169] አንዳንድ ፍርድ ቤቶች በቡድን አባላት ላይ የሚጣሉትን ግዴታዎችና የሚገባቸውን የካሣ ክፍያዎች መጠን ለመወሰን ቋሚነት ባላቸው ቀመሮች ይጠቀማሉ። ለምሳሌም ያህል፤ *በአይሰን* በአንድ ወገን *በካርላይስልና ጃክሊን* በሌላው ወገን በተነሳው ክርክር (1968) አባላት በፈጸሙት ሕገ ወጥ ድርጊት መጠን ካሣውን እንዲከፍሉ ሲወሰን *በኤሌኖይ ግዛት እና በሀርጸርና ሮው አሳታሚዎች* መካከል በተነሳው ክርክር (1969) ደግሞ ከአሳታሚው ድርጅት መጻሕፍት የገዙ ሰዎች በሙሉ በመካከላቸው ልዩነት ሳይደረግ በእኩል መጠንና አኳኋን ጉዳት እንደደረሰባቸው ተወስኖአል። የሞኖፓል ንግድ ማካሄድንና ተዘዋዋሪ የገንዘብ ሰነዶችን በሚመለከቱ ክሶች ደግሞ ከሽያጭ የተገኘው ጠቅላላ ገቢና ሌሎችም ስታቲስቲካዊ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶች የደረሰውን ጉዳት ለመተመን ማስረጃ ሆነው እንዲቀርቡ ተደርጓል። ሌሎች ፍርድ ቤቶች ደግሞ፤ ተከሳሾች ኃላፊነት እንደሌለባቸው ከተወሰነ ውስብስብ በሆነው የካሣ አተማመን ሥራ ውስጥ መግባት ስለማያስፈልግ ፍርድ ቤቱን ከዚህ ችግር ለማዳን በማሰብ የኃላፊነቱን ጥያቄና የካሣውን ጥያቄ በመነጣጠል በየፈርጁ እንዲታዩ ያደርጋሉ። ይህ የካሣ አወሳሰኑ ጥያቄ የኃላፊነቱ ጥያቄ እስከሚወሰን ድረስ እንዲዘገይ የማድረጉ ዘዴ የቡድን ክሶችን በማስተናገድ ረገድ በእጅጉ አመርቂ ውጤት የሚያስገኝ ሥነ ሥርዓታዊ ዘዴ መሆኑ በአሁኑ ወቅት ዕውቅና እያገኘ መጥቷል። አንዳንድ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ኃላፊነትን በሚመለከተው ጭብጥ ላይ የሁሉም አባላት ጉዳይ በአንድነት እንዲታይ ሲያደርጉ ካሣን በሚመለከት ደግሞ ለናሙና ያህል የተመረጡ የጥቂት

---

[167] ሊ. ፍሪማን ጁኔር÷ "ማኔጀብሊቲ ኦፍ ዘ አክሽን÷ ዘ ሜን ባትልግራውንድ"÷ <u>ክላስ አክሽንስ 1975</u> ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 53÷ ገጽ 49።

[168] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 50።

[169] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 50-58፥ በተጨማሪም ካፓሊ ኤንድ ኮንሰሉ÷ የተጠቀሰው ሥራ÷ 2ጽ 233።

አባላት ጥያቄዎች ብቻ ከሌሎቹ ተነጥለው እንዲታዩ ያደረጋሉ:: ብዙ ፍርድ ቤቶችም ከሌሎቹ ዘዴዎች ይልቅ ይህኛውን ዘዴ ይመርጣሉ:: የሚመርጡበትም ምክንያት፤ በአንድ ወገን የኃላፊነትና የካሣ ጥያቄዎች በየፈርጃቸው ተነጥለው እንዲታዩ የሚያስችል አሠራር በመሆኑ ሲሆን በሌላው ወገን ደግሞ በናሙናነት የቀረቡት የጥቂት ከሳሾች የካሣ ጥያቄዎች በችሎት በሚሰሙበት ጊዜ የቀረቡት ማስረጃዎች ጠንካራ መሆናቸውን ተከሳሹ ስለሚረዳው ከዚሁ የተነሳ የሌሎቹንም ከሳሾች የካሣ ጉዳይ በዕርቅ ለመጨረስ ሊገፋፉ ስለሚችል ነው::

በክሱ ውስጥ ሊቀርቡ የሚችሉትን የሰነድ ማስረጃዎች ለቁጥር የሚያስቸግር ብዛትና ዝርዝር ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ በአንዳንድ አገሮች የካሣ አተማመኑን ተግባር የሚያከናውነው ፍርድ ቤቱ ራሱ ሳይሆን ለዚሁ ተግባር በተለይ የሚመደብ ሬጅስትራር ወይም ሂሳብ አጣሪ በመሆኑ ይህ ዓይነቱ አሠራር ደግሞ የኃላፊነቱን ጥያቄና የካሣውን ጥያቄ ነጥሎ የማየቱን ሥነ ሥርዓት ጠቀሜታ የበለጠ ጉልህ ያደርገዋል:: ይህን ዓይነቱም የአሠራር ዘዴ፤ የፍርድ ሥራ በእማኝ ዳኞች ሱታፌ ጭምር በማይከናወንበት፤ ከዚህም የተነሳ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች መጣስ ክርክር ሊከተል በማይችልበት፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ውጤታማ በሆነ መልኩ በቀላሉ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ነው::

በመጨረሻም፤ የደረሰው ጠቅላላ የጉዳት መጠን በፍርድ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ በአንጻሩ ግን ጉዳት የደረሰባቸውን ሁሉንም የቡድን አባላት ማንነት ለማወቅ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ፤ አብዛኛው ፍርድ ቤቶች "የአኃዝ አልባ ቡድን ካሣ አከፋፈል" በመባል በሚታወቀው ዘዴ ይጠቀማሉ::[170] አንዳንድ ጊዜ፤ ልሕሳን የቡድን አባላትን ለይቶ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን አንዳንዴም የቡድን አባላት ቁጥር በጣም ከፍተኛ የእያንዳንዱ የቡድን አባል የይገባኛል ጥያቄ ደግሞ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ካሣውን ለማከፋፈል የሚያስፈልገው ወጪ ለእያንዳንዱ አባል ከተወሰነለት ጠቅላላ የካሣ መጠን የሚበልጥ ሊሆን ይችላል:: ከላይ የጠቀስነው ዘዴ የተመሠረተው በእነዚህ መነሻ ሀሳቦች ላይ ሲሆን ይህን ለመሰሉ ጉዳዮች ጥሩ ምሳሌ የሚሆነንም ሸማቾች በአንድ ሐኖት ወይም አምራች ፋብሪካ ላይ የሚያቀርቡት የቡድን ክስ ነው:: እንግዲህ ይህ ንድፈ ሀሳብ ተጠቃሽ የሚሆነው ይህን የመሰሉ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ነው:: በዚህም ንድፈ ሀሳብ መሠረት ተከሳሾች አግባብ ባልሆነ መንገድ ባገኙት ንዋይ ሊበለጽጉ ስለማይገባ ቀሪው ዕዳ ወደፊት ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ የንግድ ግንኙነት የሚፈጥሩ ግለሰቦች ለሚደርስባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲውል ይደረጋል::

ከላይ ባጭሩ የገለጽነው እያንዳንዱ የካሣ አተማመንና አከፋፈል ዘዴ ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው የቀረበው ጉዳይ እየታየ ሥራ ላይ ሲውል ነው:: በሌላ አነጋገር፤ ለአንዱ ጉዳይ ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል ዘዴ ለሌላው ጉዳይ ጨርሶም የማይስማማ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህም ሁሉንም መዝኖ በተሻለው ዘዴ የመጠቀሙ ምርጫ ለፍርድ ቤቶች ሊተው ይገባል:: ሆኖም በእኛ እምነት፥ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ዘዴዎች የተሻሉ አማራጮች ይመስሉናል:: ስለዚህም፤ ካሣ ሊከፈላቸው የሚገባቸውን የቡድን አባላት ለይቶ ለማወቅ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ፤ የካሣ አተማመኑን ተግባር የሚያከናውኑና "ለአኃዝ አልባ የካሣ ክፍያዎች የተመደበውን ገንዘብ" የሚያስተዳድሩ

---

[170] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 57፥ በተጨማሪም ይዜል፥ <u>ሲቪል ፕሮሴጀር</u>፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፥ ገጽ 1002-3 ይመልከቱ፤ እንደዚሁም ጃናታን ኤም ላንደርስ፥ ጀምስ ኤ.. ማርቲን፥ እስቴፈን ሲ. ይዜል፥ <u>ሲቪል ፕሮሲጀር</u> (2ኛ እትም)፥ ሊትል ብራውንና ኩባንያው፥ ቦስተን፥ ቶሮንቶ (1988) ገጽ 565፥ 587-8 ይመልከቱ። የጉዳት መጠናቸውን ያስረዱ የቀድሞ ሰለባ የቡድን አባላት የተራፊው ገንዘብ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም:: ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ በኢዘን እና በካርላይልና ጃክሊን መካከል በነበረው ጉዳይ እንዳተተው፤ "ተጠቃሚ ቢሆኑ የካሣ ጥያቄያቸውን ለማስፈጸም ያልቀረቡ የቡድን አባላትን ገንዘብ መውረስና ጥያቄያቸውን ለማስፈጸም ለቀረቡት የቡድን አባላት ያላፈሩትን ገንዘብ እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል::" ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 582-3::

ሬጅስትራሮች ወይም ሂሳብ አጣሪዎች የመሾሙን ጉዳይ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ልዩ ትኩረት ቢሰጡት የተሻለ ይመስለናል።

## 4. የማጠቃለያ አስተያየቶች

የቡድን ክሶች አቀራረብ ሥርዓት ዓይነተኛ ጠቀሜታ አያሌ ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው ጠንካራ የከሳሽና የተከሳሽ አህዶች እንዲመሠርቱ የሚያስችል የሥነ ሥርዓት ዘዴ ከመሆኑ ላይ ነው። ስለዚህም የቡድን አባላት በብቸኝነት ሊመጥኑት የማይችሉትን ኃይለኛ ባላንጣ በኀብረት ኃይል እንዲቋቋሙት ያስችሏቸዋል። ይህ ዘዴ ባይኖር ኖሮ ዐቅሙም፥ ተስፋ በመቁረጥ ፍላጎቱም፥ ለሌላቸው የጥቃት ሰለባዎች ዐቅምና ብርታት ያስገኙላቸዋል። በሌላም በኩል ደግሞ፤ ለበርካታ ክሶች ሊጋለጡና ከዚህም የተነሳ ለከፍተኛ ወጭ ሊዳረጉ የሚችሉ ተከሳሾች ጉዳያቸው በአንድ የክስ መዝገብ ተጠቃሎ እንዲታይላቸው ለማድረግ ስለሚያስችላቸው ዘዴው ለተከሳሾችም ቢሆን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከተሰጠም በኋላ በፍርድ ያለቀ የደቀቀ ጉዳይ ስለሚሆን ግለሰብ የቡድን አባላት ወደፊት ሌላ ክስ ሊያቀርቡባቸው አይችሉም።

በተመሳሳይ ሁኔታም፤ ይኸው የክስ አቀራረብ ሥርዓት ባይኖር ኖሮ፤ ፍርድ ቤቶች በተናጠል የሚቀርቡ አንድ ዓይነት የሕግና የኩነት ጭብጦች ያሏቸውን አያሌ ክሶች ለማስተናገድ ስለሚገደዱ በዚሁ ምክንያት አላግባብ ሊባክን ይችል የነበረውን ጊዜና ጉልበት በእጅጉ ለመቀነስ ይረዳል። በተጨማሪም፤ ይኸው ዘዴ ከነዚህ ሁሉ የማይተናነስ ሌላም ዐቢይ ማኅበራዊ ጠቀሜታ አለው። ይህም ማኅበራዊ ጠቀሜታው ግዙፍ የንግድ ድርጅቶች፥ ራሱም መንግሥትና የተለያዩ የመንግሥት አካላት፥ ሕገ ወጥ ተግባሮችን እንዳይፈጽሙ ልጓም ሆኖ የማገልገል ባሕርይ ያለው መሆኑ ነው። ይህ የሥነ ሥርዓት ዘዴ ባይኖር ጠያቂም ስለማይኖር እነዚህ አካላት በንጹሐን ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶችን ቢፈጽሙም በቀላሉ ከቅጣት ሊያመልጡ ይችላሉ። ይህን ለመሰሉ ጉዳዮች መፍትሔ ለማስገኘት መደበኛዎቹ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ፍላጎቱ ቢኖራቸውም እንኳን እጅግ ውስብስብ በመሆናቸውና ከብዛታቸውም የተነሳ ዐቅሙ አይኖራቸውም። ግለሰብ የቡድን አባላትም ቢሆኑ የካሣ ጥያቄዎቻቸው አነስተኛ ሊሆኑ ስለሚችሉ በተናጠል ክስ ማቅረቡ አያዋጣቸውም። ስለዚህም፤ ይህን የመሰሉ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ሲያጋጥሙ ለመቋቋም ዓይነተኛና ቀልጣፋ የሆነው ዘዴ የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ነው።

የቡድን ክስ መጀመሪያውም መጨረሻውም ዓላማው ፍትሕን ማስገኘት ነው። ጥንት ለልደቱ ምክንያት አሁንም ለሕልውናው መሠረት የሆነው ይኸው ዓላማው ነው። በአሁኑ ወቅት በአሜሪካና በሕንድ የገንዘብ ዐቅሙ የሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕግ ፊት ቀርበው በደላቸውን እንዲያሰሙ ከሚያስችሏቸው የሥነ ሥርዓት ዘዴዎች የላቀውን ሥፍራ ይዞ የሚገኘው የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓት ነው። ኢንዱስትሪዎች፥ ሻጮች፥ ትምህርት ቤቶች፥ ኩባንያዎች፥ ወዘተ በሚፈጽሟቸው ሕገ ወጥ ተግባራት ጉዳት ከሚደርስባቸው አያሌ ዜጎች መካከል ጉዳት ያደረሰባቸው ሕገ ወጥ ድርጊት ከምን እንደመነጨ፥ ምክንያቱ ምን እንደሆነና ምንስ ውጤት እንዳስከተለ፥ እነርሱም በበዳዩ ላይ ምን መብት እንዳላቸው የሚያውቁት ጥቂቶች ብቻ ናቸው።[171] ስለዚህም፤ ከእነዚህ ከሚያውቁት ጥቂቶቹ መሀል የገንዘብ ዐቅሙ ያላቸው ፊታውራሪ በመሆን በራሳቸውና በሌሎቹም የጥቃቱ ሰለባዎች ስም ክስ ሊመሠርቱ ይችላሉ። ስለሆነም፤ የቡድን ክስ በተግባርም ቢሆን ዕለት ተዕለት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ክስተቶች ጋር የተቆራኘ ነው።

---

[171] ለምሳሌ ካፓሊ ኤንድ ኮንስሎ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 221-2 ይመልከቱ።

"ፍትሕን ሰዎች ወደ እሚኖሩበት፥ እሚሠሩበትና እሚያፈቅሩበት ሥፍራ፥ ወደ ደጃፋቸው ይወስደዋል::"

ከዚህ አንጻር ከተመለከትነው፣ "የቡድን ክስ ሥርዓት፣ ሕገ መንግሥቶችንና የቃል ኪዳን ስምምነቶችን በመሳሰሉት ክቡር ሰነዶች ላይ ልዕልና ተሰጥቶአቸው የሚሰበክላቸው፥ በተግባር ግን በወረቀት ላይ የሰፈሩ በጎ ሀሳቦች ከመሆን የማያልፉ መብቶችና ነጻነቶች በሥራ እንዲተረጎሙ ለማድረግ የሚያስችል ኃያል መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::"[172]

ፍትሕን ለማስገኘት ካለው ገጽታ አንጻር ሲታይ፣ የቡድን ክስ ሥነ ሥርዓት አብዛኛውን ጊዜ የሕዝብን መብት ለማስከበር ከሚቀርቡ ክሶች ጋር ይያያዛል:: በአሁኑ ወቅት አሜሪካን አገር በቡድን ክስ ሥርዓት አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት የሸማቾችን መብት ለማስከበር በሚቀርቡ ክሶች ሲሆን የአብዛኛው ሕዝብ ገቢ ከድኅነት መለኪያ ወለል በታች በሆነበት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የቡድን ክሶች ለዚህ ዓላማ እንዲውሉ ማሰቡ የማይመስል ነገር ነው:: "የእያንዳንዱ አገር ችግር የተለያየ እንደመሆኑ መፍትሔውም እንዲሁ የተለያየ ነው::... ስለዚህም እያንዳንዱ አገር እንደ ችግሩ የሚበጀውን ማኅበራዊ የመብት ማስከበሪያ ዘዴ መቀየስ ይኖርበታል::"[173] ይህም ማኅበራዊ ዘዴ ያጡና የነጡ የኅብረተሰቡን ክፍሎች ዓይነተኛ ችግሮች በመፍታት ላይ የሚያተኩር ሊሆን ይገባል::

ይህን ነጥብ አስመልክቶ የሕንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ የሆኑት *ባግዋቲ* የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል፦

> "በሕዝብ ላይ የተፈጸመ በደልን ወይም የደረሰ ጉዳትን ለማስካስ ጉዳዩ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ለማድረግ ሕጋዊ መብት ያለው ሰው ወይም አካል ከሌለ ለጥቃት የሚጋለጠው ራሱ ሕጋዊነት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ሌላ መሂጃ ስለሌለው ኅዳናውን በመምረጥ ሰልፍ መውጣቱና በሂደቱም ለአመጽ መነሳሳቱ አይቀርም:: ስለዚህም፣ የሕግ ልዕልና ለራሱ ሲል ሕግን በመራመድ የኅዳናውን ሕግ የመረጠው ሕዝብ ፊቱን ወደ ሕጋዊዎቹ ፍርድ ቤቶች እንዲመልስ ለመሳብ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ አለበት::"[174]

ምንዱባን በሕጋዊ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት ሊያድርባቸው የሚችለው ደግሞ በደል ቢደርስባቸው በአፋጣኝ ችሎት ቀርበው ጉዳያቸውን እንዲያሰሙ የሚያስችሏቸው ሥነ ሥርዓታዊ ዘዴዎች ተቀይሰው ከመሠረታዊው ሕጎች ጎን ለጎን በሥራ ላይ ሊውሉ ሲችሉ ነው:: የቡድን ክስ አቀራረብ ሥርዓትም ይህንን ግብ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችል የሥነ ሥርዓት ዘዴ ነው::

ስለዚህም፣ የሚከተለውን ሐሳብ በማቅረብ ጽሑፋችንን እንደመድማለን:: አሁን ባለው ይዘቱ፣ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 መሠረት የቡድን ክስ ለማቅረብ የሚፈቀደው በሚቀርበው ክስ ላይ *ብዙ* ሰዎች እዩይ ጥቅም ያላቸው እንደሆነ ብቻ ነው:: ይህ ገደብ ተነስቶ *አያሌ* ሰዎች በተናጠል የሚያቀርቧቸው የይገባኛል ጥያቄዎች ቢኖሯቸውም በጋራ የሚያስተሳስሯቸው የሕግና የኩነት ጥያቄዎች ካሉ የቡድን ክስ ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ተደርጎ ቢሻሻል ተገቢ ይመስለናል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የቡድን ክስ አባላት ፈቃደኛነት እንደ አስፈላጊ ሁኔታ ተደርጎ መወሰድ የለበትም:: ምክንያቱም፣ ይአዜል እንዳሉት፦

---

[172] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 224::
[173] ሳቻር፥ የተጠቀሰው ሥራ፥ ገጽ 15::

[174] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 14::

> "ጥቅም የስምምነት ወይም የፈቃደኝነት ተተኪ ወይም ምትክ ነው። በሌላ አነጋገር ጥቅም ባለበት ቦታ ሁሉ እርቅና ስምምነት መውረዱ አይቀርም። ስለዚህም፤ አንድ ሰው ጥቅሙን በሚያስከብርለት ክስ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አይሆንም ተብሎ ስለማይገመት ያለ ስምምነቱ የቀረበ ቢሆንም በቡድን ክሱ ላይ የሚሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ይፀናበታል።"[175]

በዚህም ምክንያት፥ ሕገ መንግሥቱን በምንተረጉምበት ጊዜ፤ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 38 ድንጋጌዎች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 37(2) (ለ) መሠረት በሚቀርቡ ክሶች ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆኑ ተደርጎ ሊተረጎም ይገባል።

## <u>የ ቃ ላ ት ፍ ቺ</u>

በዚህ ትርጉም ውስጥ እስካሁን ያልተለመዱ በርካታ አዳዲስ ቃላት ይገኛሉ። እነዚህ ቃላት ባብዛኛው ከምንጩ ከግዕዝ የተወሰዱ ናቸው። ምንም እንኳ የቃላቱን ትርጉም ከዓረፍተ ነገሩ አስካክ ለመረዳት የሚቻል ቢሆንም ለአንባቢዎች በበለጠ ግልጽ እንዲሆንና ለእንግሊዝኛውም ተስማሚ ትርጉም መሆን አለመሆኑን ሐሳብ እንዲሰጡበት በማሰብ የእያንዳንዱን ቃል ትርጉም ከዚህ በታች ባጭር ባጭሩ አቅርበናል። እንዲሁም፤ ቃሉ በጽሑፉ ውስጥ በተለያዩ ገጾች የሚገኝባቸውን ዐረፍተ ነገሮች እርስ በርሳቸው በማናበብ ተስማሚነቱን በተሻለ ለመረዳት ስለሚያስችል እያንዳንዱ ቃል በጽሑፉ ውስጥ የሚገኝበት ገጽ ከትርጉሙ መጨረሻ በቀርን ውስጥ ተመልክቷል። ከጥንት ጀምሮ በቆየ ስያሜው "ቀርን" የሚባለው (5,7,27) ይህ ምልክት ሲሆን፤ [ ] ይኸኛውን ደግሞ "ቅንፍ" ብንለው ይመረጣል። በቀርኑ ውስጥ የሚገኙት 5,7,27 የሚሉት ቁጥሮች የሚያመለክቱት "ቃሉ" በጽሑፉ ውስጥ የሚገኝባቸውን ገጾች ነው። የቃላቱ አቀማመጥ ቅደም ተከተል በ"አ፡በ፡ገ፡ደ፡" የፊደል ተርታ ነው።

ያብዛኛው ቃላት ትርጓሜ የተወሰደው ከሊቁ ከኪዳነ ወልድ ክፍሌ "መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ" (1862-1936) ነው።

አሀድ። ኅብረት፤ አንድነት። የተዋሐደ ኅቡር፤ አንድነቱ በራሱ ቅሉ ብቻ ያይደለ፤ ብዙ ነት ያለው አንድ፤ እንደ ሰው ባሕርይ የተቀመመ የተጠራቀመ። በእንግሊዝኛው "unit" የሚለውን ነው። (81, 94, 105)

አኃዝ አልባ።አኃዝ ማለት በቁሙ፤ ቁጥር ሒሳብ፤ የቁጥር ፊደል ወይም ምልክት። የሕዝብ የገንዘብ የስፍር የሚዛን፤ የሰዓት የዕለት የወርኅ የዓመት የሥራ ኹሉ ልክ፤ ማነስ መብዛቱ ክፍሉና ዐይነቱ በየስሙ በየነገዱ ተዘርዝሮና ተዳምሮ ተለይቶ የሚታወቅበት። አኃዝ ቢስ፤ አኃዝ የሌለው ወይም አኃዝ አልባ ነገር እንዲሉ። አኃዝ አልባ ያልነው በዚህ ጽሑፍ በእንግሊዝኛው "fluid" የሚለውን ነው። (104, 105)

እሩይ። የተመሳሰለ፤ የተካከለ፤ የተነጻጸረ፤ ልኩና መልኩ አንድ የሆነ፤ ብልጫ ልዩ ነት የሌለው። እንግሊዝኛው "same" የሚለውን ነው። በተጨማሪ ከታች "ዕሩይ" የሚለውን ይመልከቱ። (73,88,89,98,102,106, ወዘተ)

---

[175] ይዜል፥ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108፥ ገጽ 15።

አምሳልነት:: መልኮች፥ ዐይነቶች፥ ባንድ አካልና ባንድ ገላ ያሉ የብዙ ሕዋሳት አርአያዎች:: አኪል ወይም ለሌላው እኩያ አምሳያ መሆን:: በእንግሊዝኛው "typicality" የሚለውን ነው:: (76,77,93,96)

እሙር:: የታወቀ፤ ዕውቅ፤ ግልጥ:: በዓላት እሙራት እንዲሉ:: በተለዋጩ፤ ንኡድ በሚለው ቃል መጠቀም ይቻላል:: "ንኢድ፤ ንኢዶት"፤ ማለት ማክበር ማመስገን፤ ማላቅ ማድነቅ፤ ከፍ ከፍ ማድረግ፤ ማለት ነው:: በእንግሊዝኛው "important" የሚለውን ነው:: "እምረት" ወይም "ንእደት" ማለት ደግሞ "importance" ማለት ይሆናል:: (90,91,96)

እንመት:: መሥራት፤ መሠራት፤ አሠራር:: በተለይ የልብስ ሥራን የሚገልጽ ቃል ነው:: ልብስ ግሩም ዘቀጢን ፍትለቱ ወሠናይ እንመቱ እንዲሉ:: በእንግሊዝኛው "practice" የሚለውን ነው:: አንዳንድ ጊዜ እንደ ሁኔታው፥ በተለምዶ አሠራር"፥ "በዘወትር ልማድ" ወይም "በልማድ ዘወትር"፥ "በፍርድ ቤቶች አሠራር"፥ በሚሉት ቃላት በተለዋጭ ተጠቅመናል:: (83,86,92,94, 95,98,99)

እስፍንት:: ስንት፤ ምን ያህል:: ስፌን ስፈነ ስፍን ከሚለው የመጣ ነው:: በእንግሊዝኛው "size" የሚለውን ነው:: (87,97)

ኃርዮሽነት:: የጋራ፥ የወል መሆን:: በእንግሊዝኛው "commonality" የተባለውን ነው:: (73,88,93, ወዘተ)

ብሄሞት:: በቁሙ፤ የየብስ ዐንበሪ ከባሕር ተፈጥሮ በየብስ የሚኖር፤ ግሩማን አራዊት የሚፈሩትና የሚገዙለት ከአራዊት ሁሉ የሚበልጥ መጨረሻ ግዙፍ፥ የእንስሳት ራስ የአራዊት ንጉሥ ቀዳማያቸው:: እንግሊዝኛው "monster" የሚለውን ነው:: በጽሑፉ ውስጥ "monstrosities" የሚለው ደግሞ "ብሄሞቶች" ተብሏል:: ቃሉ "dinosaur" የሚለውንም ለመተርጎም ተስማሚ ነው:: "ሌዋታን" የሚለውም ቃል ተመሳሳይ ነው:: (83)

በሐውርታዊ:: በሐውርት ማለት፤ መላይቱ ምድር፤ የብስ ዓለመ ሰብዕ፤ ሰማይ ከነግሡ ምድር ከነልብሱ፤ መላው ዓለም ላዩም ታቹም፤ ማለት ነው:: በእንግሊዝኛው "universe" የሚለውን ሲሆን "በሐውርታዊ" ሲሆን "universal" ማለት ይሆናል:: (86)

ብቁዐት ቀዳማይ:: ብቁዐት ወይም ብቁዔት ማለት፤ መብቃት፤ ብቃት:: መጥቀም፤ መጠቀም፤ አጠቃቀም፤ ጥቅም ትርፍ፤ ረብ ርባታ ጠቀሜታ፤ ማለት ነው:: ቀዳማይ ማለት ደግሞ በቁሙ፤ ፊተኛ፤ የፊት፤

የጁር፤ መዠመሪያ፤ ተቀዳሚ፤ ማለት ነው:: ብቁዐት ቀዳማይ ያልነው፤ በላቲኑ "prima facie" የተሰኘውን ዕውቅ ቃል ነው:: (82)

ህጹእ:: ዝም ጸጥ ያለ፤ ያረፈ የረጋ፤ ሁከት የሌለው:: "ዝጉን" የሚለው ቃልም የዚሁ ተመሳሳይ ነው:: እንግሊዝኛው "silent" የሚለውን ነው:: "silence" ሲሆን ደግሞ "ህድአት" ወይም "ዛጎን" ይሆናል:: "አርምሞ" የሚለውም ለ "silence" ተስማሚ ቃል ነው:: ቅጽል ሲሆን "ርሙም" ይሆናል:: (88,90)

ህግርት:: ትጋት ሐሳብ፤ ትጉህነት ዐባቢነት:: በእንግሊዝኛው "zeal" የሚለውን ነው:: ቅጽል ሲሆን "ህግሩት" (zealous) ይሆናል:: (97,98)::

ዝንቅ:: ግሱ÷ ዘነቀ ይዘንቅ:: መዘነቅ፤ መቀየጥ:: መዠነቅ አብዝቶ መጨመር፤ የግ ብር የነገር:: ቅይጥ ውጥንቅጥ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በእንግሊዝኛው "hybrid" የተባለውን ነው:: (69,70,89)

ሕፀፅ:: በቁሙ፤ ጉዳይ ጉድለት፤ ቅሬታ፤ ያነሰ የጎደለ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በእንግሊዝኛው "limitations" የሚለውን ነው:: (69,85,93)

ውልብኝ:: (ወልብ):: የእሸት ፍሬ ታሽቶ ተፈልፍሎ የሚቃም የሚጠረጠር:: የአዕዋፍ ዘር ዕንቁላል፤ ከዚያውም ውስጡ ፍሬው አስኳሉ:: በእን ግሊዝኛው "merit" (of the case) የሚለውን ነው:: "ወልብ" ታሽቶ ተፈልፍሎ እንደሚወጣ ሁሉ የአንድ ጉዳይ "merit"ም እንዲሁ ነው:: (95)

በውሳንያተ ሕግ አግባብ:: መጻሕፍት፤ ውሳንያተ ሕግ÷ ውሳንያተ አበው÷ ውሳንያት እንተ ወሰንዋ አበው ቀደምት፤ ይላሉ:: በሕግ የተወሰነ፤ ቀደምት አባ ቶቻችን የወሰኑት፤ ለማለት ነው:: "በውሳንያተ ሕግ አግባብ" ያልነው በእንግሊዝኛው "due process of law" በመባል የሚታወቀውን መርህ ነው:: ይህንን የመረጥንበትም ምክንያት ሐረጉ እንደ "due process" ሕገ መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን ሕገ ጠባይዕን (ፍጡር ሁሉ በባሕርዩ ዐውቆ የሚፈጽመው የተፈጥሮ ሕግ) ጭምር ሊያመለ ክት ይችላል ወይም ይህንኑ የሚያቅፍ አንድምታ አለው ብለን በማሰብ ነው:: ከዚህ በማያያዝም "due process guarantees" የሚለውን "የውሳንያተ ሕግ ዋስትናዎች፤ "due process clause" የሚለውን ደግሞ "በውሳንያተ ሕግ አንድምታ" በማለት ተርጉመነዋል:: (64,67,79,81,86,91,97,99,101, ወዘተ)

ሐኖት:: መደብር፤ የንግድ የገበያ ቤት:: ሲበዛ "ሐንዋት" ይሆናል:: በእንግ ሊዝኛው "supermarket" ወይም "department store" የሚለውን ነው:: (92,104)

የይገባኛል ጥያቄዎች:: በእንግሊዝኛው "claims" የሚባለውን ነው:: (70,76,78,82,94, 96,100,102 ወዘተ)

ኩነት:: መሆን፤ አኳኋን ኹነታ፤ አኗኗር:: ፍጥረት፤ ሥነ ፍጥረት፤ ለይኩን በማ ለት የተገኘ:: ሲበዛ "ኩነታት" ይሆናል:: ሆኖም ለአማርኛ በሚስማማ

መለኩ "ኩነቶች" ብንለው ይቀላል። በእንግሊዝኛው "facts" የሚባለውን ነው። (69,71,73,80,88,90,97,100,102,105, ወዘተ)

ክትመት። ምልክት፣ መለዮ። መጻሕፍት፣ ትሕትና ውእቱ ክትመተ ሐራዊ ክርስቶስ፣ ይላሉ። ትሕትና መለያ ጠባያቸው፥ ምልክታቸው ነው ለማለት ነው። ሲበዛ "ክትመቶች" ብንለው ይስማማዋል። በእንግሊዝኛው "qualities" የሚለውን ነው። (79,97,98)

ለባዊ። ልባም፥ ልብ አድራጊ፣ ተመልካች አስተዋይ፣ ብልኅ ዐዋቂ ጠንቃቂ። ፍጥረት ለባዊት ወሥጋዊት። ኩሉ ለባዊ ይረክባ ለጥበብ እንዲሉ። ሲበዛ "ለባውያን" ወይም "ለባውያት" ይሆናል። ሕገ ልቡና (reason) የሚለውም ከዚሁ የወጣ ነው። "ለባዊ" ያልነው በእንግሊዝኛው "reasonable" ወይም "reasonable man" የሚለውን ነው። አባቶቻችን "reasonable man" ለማለት በለባዊ ፈንታ "አዕምሮ ግዕዝ" ያለው፣ በሚሉት ቃላትም ይጠቀማሉ። ሀ ግእዝ ለ ግእዝ ብለን ትምህርት እንደምንጀምር ሁሉ የመጀመሪያው ደረጃ እውቀት ያለው፣ ምራቁን የዋጠ አንደበቱን የገዛ፣ እንደ ማለት ነው። በእንግሊዝኛው "common sense" ከሚለው ጋር ይቀርባል። (65,94)

ልሕስ። ሄደ ተጠረገ፣ ጠፋ ታጣ። ልሕሳን፣ የሌሉ፥ የጠፉ፥ ያልተገኙ ያልቀረቡ። በእንግሊዝኛው "absent" የሚለውን ነው። "absence" የሚለውን "ልሕሰት" ልንለው እንችላለን። (76,81,86,92,94,95,96,104, ወዘተ.)

መብእ። የሚያገባ፣ አግቢ፣ መላሽ። ሰጭ አቅራቢ። በእንግሊዝኛው "inspiration" ወይም "source" የሚለውን ነው። ሲበዛ "መብአት" ይሆናል። (83)

መብዝኅት። የተከፍሎ ብዛት፣ ላቂያ፣ ብልጫ። መብዝኅተ ሕዝብ። የሚበዛው የሚልቀው የሚበልጠው፣ ብዙው ያሰኛል። በእንግሊዝኛው "largely" የሚለውን ወይም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ነው። (94,97,98)

መግቦ። መምራት ማስተማር፣ በሥራት ማስኬድ። ምግብና፣ መጋቢነት፥ ጥበቃ ሹመት። ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው "በእንተ ምግብና" የሚለውን አርዕስት 32 ይመልከቱ። በእንግሊዝኛው "manage" እና "management" የሚለውን ነው። (102,103)

መግረምት። ማስፈሪያ፣ ማስፈራሪያ፣ መስፈራርቾ። "መግረምት" አመጣጡ ግርማ ግሩም ከሚለው እንደመሆኑ መደነቅን፥ ውስጥ አዋቂነትን ያመለክታል። ስለዚህም "blackmail" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል "ማስፈራሪያ" ከሚለው ይልቅ የተሻለ ይገልጸዋል። (83)

መጻልው። እብነ መጻልው ማለት፣ የሚዛን ደንጊያ፣ ልክነት ያለው፣ ሌላውን በርሱ መለኪያ ማስተካከያ፣ ማለት ነው። "መጻልው" ብቻውንም ቢሆን ያስኬዳል። በእንግሊዝኛው "standard" የሚለውን ነው። (84)

መጣኔ:: መመጠኛ፣ የልክ የስፍር የቁጥር ሚዛን ገመድ:: በእንግሊዝኛው "factor" የሚለውን ነው:: (77,79,96,100,102)

መሌሊት:: ሕዋስ፥ ብልት፥ አባል፥ ልዩ ልዩነት ያለው ዐጽቅ፣ በየስሙና በየክፍሉ:: ሲበዛ "መለያልይ" ይሆናል:: በእንግሊዝኛው "component" የተሰኘውን ነው:: (89)

መፍቅድ:: ግብር፣ ነገር፣ ጉዳይ፣ ባሕርያዊ ሥራ፣ በግድ የሚፈለግ፣ በባሕርይ የሚያሻ፣ ጋብቻ ምግብ ልብስ የመሰለው ሁሉ:: ቀዳሚ ኩሉ መፍ ቀዱ ለሰብእ ማይ ወእሳት እንዲሉ:: ፍትሐ ነገሥቱም ዝንቱ ሳዕለ ክልኤቱ መፍቅዳት ይላል(ፍ:ነ:24):: ሲበዛ "መፍቅዳት" ይሆናል:: በእንግሊዝኛው "necessity" የሚለውን ነው:: (67,87,89)

መስተገብር:: አግባሪ አገባሪ፣ የሚያስገድድ አስገዳጅ ማለት ነው:: ፍትሐ ነገሥት 35ትን ይመለከቷል:: ሲበዛ "መስተገብራት" ይሆናል:: "መስተገብሮች" የሚለውም አፍ ስለማይዝ ይስማማል:: በእንግሊዝኛው "requirement" የሚለውን ነው:: (9,79,93,94,96,99,100, ወዘተ)

ማእምር:: የሚያውቅ ዐዋቂ:: ሲበዛ "ማእምራን"፥ "ማእምራት" ይሆናል:: በእንግሊ ዝኛው "authority" የሚለውን ነው:: (99)

ምርካብ:: ሐሳብ፣ ጥበብ፣ ነገር፣ ምስጢር፣ ከልብ የሚገኝ:: ሲበዛ "ምርካባት" ይሆ ናል:: በእንግሊዝኛው "tenet" የሚለውን ነው:: (99)

ንቱግ(ሕሙግ):: ንቱግ የሚያገለግለው ለዕቃ ለመሣሪያ ሲሆን ሕሙግ ደግሞ ለምግብ ለመጠጥና ለመሳሰሉት ነው:: ትርጉሙም፣ "ንቱግ"፣ ያነሰ የጎደለ፣ ጎዶሎ፣ "ሕሙግ"፣ የታመገ ዕምግ፣ ክፉ ጥፉ፣ ብልሹ፣ ድፍርስ:: ዐይን ሕሙግ፣ መብልዕ ሕሙግ እንዲሉ:: ወደ ስም ሲለወጡ "ንትገት"፣ "ሕምገት" ይሆናሉ:: ሲበዙ ደግሞ "ንቱጋን" ወይም "ንትግት"፣ "ሕሙ ጋን" ወይም "ሕምግት" ይሆናሉ:: በእንግሊዝኛው "defect" የሚለውን ነው:: (90,92)

ዕሩይ:: የተካከለ፣ የተመሳሰለ፣ ትክክል፣ አንድ ዐይነት:: ሲበዛ፣ ዕሩያን፥ ዕሩያት ይሆናል:: ስም ሲሆን ዕሪና ይሆናል:: መተካከል፣ አንድነት፣ ትክክልነት፣ አለመበላለጥ፣ ማለት ነው:: መጋቢት ወርኀ ዕሪና ይባላል:: እንደ መስከ ረም የቀንና የሌሊት ምግብና ትክክል የሚሆኑበት ወር ለማለት ነው:: በእንግሊዝኛው "identical" የሚለውን ነው:: "እዩይ" እና "ዕሩይ" እንደ እንግሊዝኛው "same" እና "identical" በጣም ተቀራራቢ ናቸው:: ብላ ክስ ሎው የተባለው ታዋቂው የሕግ መዝገበ ቃላት "same" የሚለውን "ዕሩይ (identical)፣ አኪል (equal)፣ አቻ (equivalent)፣ በማለት ሲተረጉ መው ሆኖም "same" ሁልጊዜም "identical" ማለት እንዳልሆነና አብዛ ኛውንም ጊዜ "አንድ ዓይነት ወይም ዝርያ" የሚል ትርጉም እንዳለው ይገልጻል:: "similar" የሚለውን ደግሞ "በእጅጉ አምሳያ የሆነ፣ በብዙ መልኩ የሚመሳሰል፣ በሁሉም ገጽታው ተመሳሳይነት ያለው" በማለት ይገልጸዋል:: (73,88,89,90,91)

**ቆሎ::** ቀደም ባሉት ዘመናት በተለይ ለጭቃሹሞች ደሞዝ የማይከፈል ስለነበር ለአገልግሎታቸው የአካባቢው (የጭቃው) ገበሬ ከሚያመርተው ሰብል እንደ ዐቅሙ እያዋጣ ይሰጥ ነበር:: ይህም በዘልማድ "ቆሎ" ይባል ነበር:: ጭቃ ሹሙም መዋጮውን ያልሰጠውን ገበሬ ሲያገኝ "ምነው ቆሎዬን ከለከልከኝ?" በማለት በዋዛ ነበር የሚጠይቀው:: ሥራቱ እንደ ማበረታቻ እንጂ እውን ለአገልግሎቱ የሚመጥን ክፍያ ወይም ምንዳ ሆኖ አይደ ለም:: ስለዚህም "incentive" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የተሻለ ይገል ጸው ይሆናል:: "incentive" ን ቆሎ በማለት ፈንታ "ትዕሲት" ልንለውም እንችላለን:: "ትዕሲት" ማለት፤ ስጦታ ጉርሻ፤ ማለት ነው:: (92,97)

**ርቱዕ::** የቀና፤ ቅን፤ እውነተኛ:: ሲበዛ "ርቱዓን" ወይም "ርትዕት" ይሆናል:: በእንግሊዝኛው "true" የሚለውን ነው:: "ኢርቱዕ" የርቱዕ ተቃራኒ ነው:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በእንግሊዝኛው "spurious' የሚለውን ነው:: (69,70,77,80,89)

**ተሰናን::** ፍርድ፤ ቋንቋ፤ የነገር ዐይነት ርስ በርሱ የማይመሳሰል ተጣይ:: ሲበዛ "ተሰናናት" ይሆናል:: ግሱ፤ ተሳነነ ነው:: በእንግሊዝኛው "exception" የሚ ለውን ነው:: (64,67)

**ትውክልት::** በቁሙ፤ መታመን እምነት፤ ጽኑ ተስፋ አልኝታ፤ የማይታበል የማይጠ ረጠር የሃይማኖት ፍሬ:: ባጭሩ፤ ውክልናንና ባሕርዩን የሚያመለክት ነው:: (92)

**ኅቡር::** ያበረ፤ የተባበረ አንድ የሆነ፤ እኩያ ዐብሮ አደግ ባልንጀራ፤ ቡድን ስብስብ:: ሲበዛ "ኅቡራን፤ ኅብርት" ይሆናል:: በእንግሊዝኛው "group" የሚለውን ነው:: (90)

ስለ ዝግጅት ክፍሉ::

ዮሐንስ ኅሩይ::